


ጎሬ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል




ገዘሬ ቴዎፍሎስ ት/ቤት

# ራዕየ ቴዎፍሎስ




www.ethiopianorthodox.org

D/N SOLOMON YOHANNES







የካቴድራሉ አስተዳዳሪ ከካቴድራሉ መዓለ ሕፃናት አስተማሪዎችና ተማሪዎች ጋር



ስማዕቱ አባ ቴዎፍሎስ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስና ከብፁዕ ወቅዱስ ቄርሎስ ስደስተኛ ጋር

ይቅርታ!

[illegible]



"...ለሀገራቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው የሠሩት ሥራ በዓለም አቀፍ ደረጃም ያበረከቱት ክፍተኛ አስተዋፅኦ ሁሉ እንዲሁም በግፍ መታሰራቸውና መገደላቸው ሊተረክ ይገባል።" ገጽ ፬

አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት! የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት! የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት



ዘመን ተሻጋሪ አባት

"ምድራዊ ኑሮአቸውን በምግባረ ሃይማኖት አድምቀው የኖሩት ግን ዘሞት ወደ ሕይወት የሺጋገሩበት! የበለጠ ደምቀው እንደ መስከረም አበባ ፈክተው የሚታዩበት እንጂ የሚረሱበት አይደለም" ገጽ ፬

ሊቀ ማዕምራን ፋንታሁን ሙጬ

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ



"የባለ ታሪኩን ታሪክ ማጉላትም ታሪክ መሥራት ነው" ገጽ ፮

መልአከ ፀሐይ ቀሞስ አባ ኃይለ መስቀል ደሳለኝ

የንፋስ መውጫ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል አስተዳዳሪ

## ታሪክ ወትውልድ ያስተበዕዕም

"...በአካል ሙተው ቢቀበሩም መቃብራቸው በነ የሠሩለት የሕዝብ ልብ ስለሆነ በተቀረጹበት የሕዝብ ልቡና ውስጥ አድረው ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ" ገጽ ፮

ዶ/ር ሐዲስ የሻነው

## አካባቢያዊ ልማትና ቤተ ክርስቲያን

"የቤተ ክርስቲያን ስም የሚነሣው ካለፈው ዘመን ወርቃማ ታሪክ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመጪው ዘመን ብሔራዊ ልማትም ጋር ነው።" ገጽ ፲፫

ኤርምያስ ዘመን

የንፋስ መውጫ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ሰንበት ት/ቤት

ሊቀመንበር



የማይረሳ ታሪክ

"...እብር በመሥራት እጅግ የአስተዳደር ብልሐትን ያስተዋልኩበትና የተርከብኩበት ከመሆኑም ባሻገር በአባቶቹ ምክንያት በሀገሩ ላይ የማይረሳ ጥሩ ትዝታ እንዲያድርብኝ አድርጓል።" ገጽ ፲፰

ሊቀ ሥዩማን ፍቅሩ መሰፍን

የካቴድራሉ ዋና ጸሐፊ

## ሀልዎተ እግዚአብሔር

"ብዙ ማስረጃዎች ያሉትን እውነታ ምንም ማስረጃ በሌለው ሐሰት መለወጥ ወደር የማይገኝለት እልከኝነት ነው"

ገጽ ፱

በመምህር አእመረ አሸብር

በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ የሊቃውንት ጉባኤ አባል



## የማይደከም ጉልበት የማይሰለች አንደበት

"...ክፉቱ ዓለማችን የማያውቁትን በሚናገሩ፣ ያላዩትን በሚመሰክሩ እልፍ አዕላፋት የተሞላች መሆኗ ነው።" ገጽ ፲፱


ከመጽሔት ዝግጅት ክፍሉ



ዝክረ ቴዎፍሎስ ትቤት አመሠራረት

"ሕይወታቸው ለሰው ልጅ ክብር ግድ ባልነበራቸው ገፈኞች እጅ ቢታለፍ ኖሮ በዚሁ ቦታ ላይ ዋነኛ የሚሆን መንፈሳዊ ትቤትም ለመክፈት ራዕይ ነበራቸው" ገጽ ፲፱

ታምራት አበራ



የን/መ/ሕ/ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል አመሠራረት

"አንገትዋ ወዳህ የቤተ ክርስቲያን አደራ ለእናንተው ነው..." ገጽ ፮

ቀኝ ጌታ ስብሐት ዘሾ



በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ

"በሥራ ችሎታቸውና በእውቀታቸው ከመምህርነት የሊቀ ሥልጣናት ማዕረግ ያገኙት መልዕክቱ በመንገድ ሲሄዱ ከያዩት እና ከማንኛውም በሰው ጋር ሲነጋገሩ ይማሩበት ነበር።" ገጽ ፲፩

በአዳም መልአኩ



ፓትርያርክ ቴዎፍሎስና የውጭ ግንኙነት

"ወያይተው የሚያሳምኑ! ተከራክረው የሚረቱ! የነገረ መለኮት አስተምህሮን በሚመለከት ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ፈጥነው የማያዳግም መልስ የሲጡ በዘመናቸው ተወዳዳሪ ያልነበራቸው አባት ነበሩ።" ገጽ ፳፩

ዓለየሁ ዓለምነህ



ራዕየ ቴዎፍሎስ

"...የአበው ሐዋርያትን ቀኖና እና የአንድ አብያተ ክርስቲያናትን የተከተለ ነበር።" ገጽ ፲፩

ሊቀ ካህናት ክንፈ ገብርኤል አልታዬ

በመምሪያ ኃላፊ ማዕረግ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ አባል



ግብረ ቴዎፍሎስ...

"...ዘመንን ተሻጋሪ! ቤተ ክርስቲያንን አኩሪ! ስደቶችን አስፋፊ! ህያው ምስለ ሕያዋን መንቀሳቀሻ መቃን መሆኑን የተሰየ ቅንነቱ ካለበት በቀር በግልጽ ይታያል።" ገጽ ፲፯

መምህር ደጉ ዓለም

የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ መምህር

ቢሃለ ቴዎፍሎስ

"በሰንበት አይታረምም..." ገጽ ፳፬

በታምራት አበራ

ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ለትምህርት መስፋፋት...

"...ወደ ውጪ እየላኩ እንዲማሩ አድርገዋል" ገጽ ፳፫

ሊቀ ህሩያን ጌታቸው ኀይሌ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት

በንፋስ መውጫ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል

ሐምሌ ፳፻፪ ዓ.ም. ተዘጋጀ

## መታሰቢያነቱ

ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ወላጅ አባት ለሊቀ ቾምብሬ ውቤ እንግዳ (አባ ወልደ ማርያም) ነው።

የሊቀ ቾምብሬ ልጃቸው ዓለምን ንቀው ሲመነኩሱ እስከው በጉጃም ጠቅላይ ግዛት! በብፁና እውሪጽ በሚገኘው ሥር ኢየሱስ ገዳም ገብተው ቀሪውን ሕይወታቸውን በምንኩስና አሳልፈዋል፡ በመሆኑም "ለልጅ ያልሆነ ዓለም ለኔ ምን ሊሆን" ብለው ይህን ማድረጋቸው ይህ መጽሔት መታሰቢያነቱ ለሳቸው እንዲሆን አሳልፈዋል።

ይህ መጽሔት "ራዕየ ቴዎፍሎስ" ተብሎ የተሰየመበት ምክንያት ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋዮች በጥር! በእውቀት እንዲበለጽጉና ቤተ ክርስቲያኒቱም በልማት ሥራ ራሷን ችላ ሌሎችን መርዳት እንድትችል የነበራቸውን ራዕይ በዚሁ ስለሚያበረታና ስለሚያስረዳ ነው።

www.ethiopianorthodox.org



**"ኦ አበው መሀርምሙ ለውሉድክሙ..ኪናተ ዘይደልምሙ ከመ ኢያስተሐምሙ ለግብረ ፅርዐት፤ ወላጆች ሆይ ለሥራ ፈትነት እንዳ ይጋለጡ ለልጆቻችሁ ተግባረ እድን አስተምሩአቸው።" /ድስቅ. 22/**

ይህ የአባቶቻችን የቅዱሳን ሐዋርያት ትእዛዝ ነው። ወላጆች ለልጆቻቸው ከሚያደርጉት ሁለንተናዊ እንክብካቤ ጋር እግዚአብሔርን በማወቅና በመፍራት በመልካም ሥነ ምግባር ማሳደግ፤ ቃለ እግዚአብሔርንና የሚጠቅማቸውን ተግባረ እድ ማስተማር እንደሚገባቸው አባቶቻችን ቅዱሳን ሐዋርያትና የእነርሱ ተከታዮች ሁሉ በአጽንዖት አዝዘዋል። በጎረ ቤተ ክርስቲያን የሚሠሩ አብያተ ትምህርት ሁሉ የዚህ ሐዋርያዊ ትእዛዝ ምልዐትና ፍጻሜ ናቸው።

በመሆኑም ከቅዱሳን አባቶቻችን ሐዋርያት ተከታዮች አንዱ ሰማዕቱ አባታችን ቅዱስ ቴዎፍሎስ ባሳነጹት በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በቅዱስነታቸው ስም የተሠራውን ይህን ትምህርት ቤት ባዛሬው ዕለት መርቀን ስንከፍት እጅግ ከፍያ ያለ ደስታ ይሰማናል። ለቅዱስ ሰማዕት አቡነ ቴዎፍሎስ ከተሠራውና ከቆመው መታሰቢያ ሐውልት ሌላ ይህ ት/ቤት ተፈጽሞ እንድናይ ለአበቃን አምላካችን ክብር ምስጋና ይሁን።

የሰማዕቱ ቅዱስ ቴዎፍሎስ ልደታቸው በሚከበርበት መቶኛ ዓመት ዐጽማቸውም በተቀደሰው ቦታ ያረፈበት 18ኛ ዓመት በሚታሰብበት ዕለት ይህ ትምህርት ቤት መመረቁ በስንበት ላይ ደብረ ዘይት እንዲሉ ለእኛም ለአካባቢው ማኅበረሰብም ሁሉ እጥፍ ድርብ ደስታ ነው። "በዘነአምር ንነግር ወበዘርኢነ ሰማዕተ ንከውን።" "የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን" /ዮሐ.3፥11/ ተብሎ እንደተጻፈ ብፁዕ ወቅዱስ ሰማዕት አቡነ ቴዎፍሎስ በኢትዮጵያ ውስጥ ከነበሩት ታላላቅ ስመ ጥር ምሁራን አንዱ ምናልባትም ዘየዐቢ ምሁር ስለነበሩ ትምህርትንና የተማረ ሰውን ይወዱ እንደነበር መናገርና መመስከር እንችላለን።





ሰማዕቱ ቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለትምህርትና ለዕውቀት ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጡ ታላቅ አባት ነበሩ። ብዙ ቋንቋ የሚናገሩ ሌላውንም ሰው ቋንቋ እንዲማር የሚመክሩ አርቆ አሳቢና ጥበብን የተሞሉ ነበሩ። ለመማር ፍላጐት ያለውን ሰው ያጠኑ ነበር። ወዲያውም እንዲማር ሁኔታዎችን ያመቻቹለት ነበር።

ሰማዕቱ ቅዱስ ቴዎፍሎስ ወደፊትም ስለሚኖረው የቤተ ክርስቲያንንና የልጆቿን ሁኔታ ያውቁ ነበር። ወደፊት የቤተ ክርስቲያን ልጆች ዘመናዊ የዕውቀትና የአመለካከት ልዩነት እንደሚፈጠር በሚገባ ይረዱ ነበር። መለያየት ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ጠላት እንደመሆኑ ልዩነት እንዳይኖር ለማድረግ በወጣቶችና በካህናት መካከል እንደ ድልድይ በመሆን የሚያገለግሉ ዘመናዊውንና ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የቀሰሙ ወጣቶች ሊታወንት የሚፈልቁበትን መንፈሳዊ ኮሌጅ እንዲቋቋም አድርገዋል። እንግሊዝኛ የሚናገር የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ፤ እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን ልጅ አይደለም በሚባልበት ዘመን የነበረውን ተፅዕኖ ሁሉ አሸንፈው ካህናት ዘመናዊ ትምህርትን ከቋንቋው ጋር አውቀው "አይዞህ የኔ ልጅ" በማለት ብቻ የማይመለሰውን ትውልድ እንዲጠብቁ ያደረጉ "ረድኤተ ወመምህር" ነበሩ።

ብፁዕ ወቅዱስ ሰማዕት ቴዎፍሎስ ወጣቶች በዐጸደ ቤተ ክርስቲያን እየተሰበሰቡ መማራቸውንና መንፈሳዊ እንቅስቃሴያቸውን ይደግፉ ነበር። በመሆኑም ወጣቱ ቤተ ክርስቲያኑን እያወቀና ሊያገለግላትም ቃል እየገባ በመሄዱ ቤተ ክርስቲያናችን የኢትዮጵያ ትምህርት ሚኒስቴር ሆና ነበር።

ከዚህም ሌላ ቅዱስ አባታችን ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ "የውጭ ሀገር የቤተሰብ ጉብኝት" የሚል መርሐግብር አዘጋጅተው ነበር። በመርሐ ግብሩ መሠረትም በየስንበት ት/ቤቱ በሚቀርቡ ዝግጅቶች ላይ ብልጫ ያላቸው ወጣቶች ወደውጭ ሀገር ሄደው ት/ት እንዲቀስሙ ይደረግ ነበር። በዚህ ዓይነት መንገድ በርካታ ወጣቶች ተምረው ቤተ ክርስቲያናቸውንና ሀገራቸውን በከፍተኛ ደረጃ ለማገልገል በቅተዋል።

እኒህ ታላቅ ቅዱስ አባት ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸው የሠሩት ሥራ እጅግ ብዙ ነው። በአጭሩ የቤተ ክርስቲያኗን ሁለንታዊ እድገት አጠናክረዋል። ዓለም አቀፍ ክርስቲያናዊ እንቅስቃሴ እንዲጠናከር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። ይልቁንም የዓለም አብያተ ክርስቲያናትንና የመላው አፍሪቃ አብያተ ክርስቲያናትን ምክር ቤት ለመመሥረት በተደረገው ጥረት ከፍተኛ ድርሻ አበርክተዋል። ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት የተቀዳጀችው ከፍተኛ የመሪነት ደረጃ እርሳቸው በጀመሩትና በደከሙበት ጥረት የተገኘ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በክርስቲያኖች መካከል መግባባት፣ መከባበርና መተባበር እንዲመሠረት ያደረጉት አስተዋጽኦም እጅግ ታላቅ ነው። መልካም ውጤትንም አስገኝቷል።

ነገር ግን ይህን ሁሉ ላደረጉት ታላቅ አባት የተከፈላቸው ዋጋ ሌላ ነው ይኸውም በግፍ መታሠር፣ ጭካኔ የተመላበት ስቃይና በመጨረሻም በአሰቃቂ ሁኔታ መገደል ነው። ይሁን እንጂ ይህም ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር የከበረ ዋጋ የተቀበሉበት ነው። ዛሬ እንዲህ እንድንዘክራቸውና የተለያዩ መታሰቢያቸውን እንድናቆምላቸው ያደረገ የሰማዕትነት ሞት ነው።

ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ብዙዎች ራዕያት ነበሯቸው። አንደኛውና ዋናው ሁሉ እንዲማርና እንዲያውቅ ነው። ይህ ራዕያቸው በዚህ ት/ቤት ፍጻሜ እውን ሆኗል፤ እግዚአብሔር ይመስገን። ሌላውንም እግዚአብሔር በፈቀደልን ጊዜ እንተረጉመዋለን።

በዚህ ት/ቤት የእኒህ ቅዱስ አባት ማንነት ለትውልድ እንዲገለጥ ያስፈልጋል። በማንኛውም ት/ቤት የኢትዮጵያ ታሪክ አንዳኛው የትምህርት ዓይነት ነው። የቅዱስ ሰማዕት ቴዎፍሎስ ታሪክም የኢትዮጵያ ታሪክ ነው። ስለሆነም "መሀርምሙ ለውሉድክሙ፤ ለልጆቻችሁ አስተምሯቸው" እንደተባለ ግፍና አመፅ በተመላበት ዘመን በሀገራችን ላይ የተፈጸመው ድርጊት ሁሉ በሚተረክበት ጊዜ እኒህ ቅዱስ አባት ለሀገራቸውና ለቤተ ክርስቲያናቸው የሠሩት ሥራ በዓለም አቀፍ ደረጃም ያበረከቱት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ሁሉ እንዲሁም በግፍ መታሰራቸውና መገደላቸው ሊተረክ ይገባል።

ይህ ት/ቤት ከተመሠረተ ጀምሮ እስከዚህ ያደረሳችሁና በዛሬው ዕለት ሕንጻውን ያስመረቃችሁ የካቴድራሉ አስተዳዳሪ፣ የካቴድራሉ የሰበካ ጉባኤ አስተዳደር ጽ/ቤትና ማኅበረ ካህናቱ ሁሉ የቅዱስነታቸው በረከት በእናንተ ላይ ይደር። የእኛም ቡራኬና ምስጋና ይድረሳችሁ፤ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

አባ ጳውሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት፣
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንት፣
የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት

ሐምሌ 4 ቀን 2002 ዓ.ም
አዲስ አበባ



www.ethiopianorthodox.org



## ዘመን ተሻጋሪ አባት

**በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን!**

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ጥበብ ወደዚህ ዓለም ከመጣበት ጊዜ አንስቶ የሚቆይበትም ጊዜ የተወሰነ ነው። በእርግጥ ቅዱስ መጽሐፍ፣ "ዘየዐምን በወልድ ቦ ሕይወት ዘለዓለም፤ በወልድ ያመነ የዘላለም ሕይወት አለው" (የዮሐንስ ወንጌል 3፥36) ቢልም አምላካችን ከመረጣቸው እንደነ ዕዝራ፣ ሄኖክ፣ ኤልያስ ካሉት በስተቀር ፈራሽና በስባሽ ሥጋን ይዞ የሚኖር የለም። በመሆኑም አብዛኛው የአዳም ዘር በምድር ላይ መኖር የሚገባውን የኮንትራት ጊዜ ካጠናቀቀ በኋላ የሞት ጥሪ ሲደርሰው ማንነቱ በዚያው ይረሳል። ይህ የሚሆነው ግን ለሃይማኖት ብሎም ለትውልድ ጠቃሚ የሆነ ሥራ ያልሠሩ እንደሆነ ነው።

ምድራዊ ኑሮአቸውን በምግባረ ሃይማኖት አድምቀው የኖሩት ግን ከሞት ወደ ሕይወት የሚሸጋገሩ በት፣ የበለጠ ደምቀው እንደ መስከረም አበባ ፈክተው የሚታዩበት እንጂ የሚረሱበት አይደለም። በዓለም ላይ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም ታሪካቸው ዘመን ሳይገድበው፤ እህጉራት ሳይከልሉት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲሸጋገር ይኖራል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ካፈራቻቸው አባቶች መካከል ለቤተ ክርስቲያኒቱ እና ለሀገሪቱ የጎላ ሥራ ሠርተው ካለፉት ውስጥ ደግሞ ቀዳሚው ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ናቸው። ለዛሬዋ ቤተ ክርስቲያናችን ሕልውና የነዚህ ቅዱስ አባት ሥራ መሠረት ሆኗታል።

ቅዱስ አባታችን በዘመናቸው ቤተ ክርስቲያኒቱን በጽኑ የሃይማኖት እና የልማት መሠረት ላይ በመመሥረታቸው ከእሳርቸው በኋላ የተነሣው የእግዚአብሔር የለሽ መንግሥት እውሎ ንፋስ ሊያናውጻት/ ሊያነዋውጣት/ አልቻለም። የቅዱስ አባታችንን መሠረትነት በዚች አነስተኛ መልዕክት ለማውሳት መሞከር ዓባይን በጭልፋ እንደሚሉት ይሆናል። ሆኖም ግን ያቅምን ያህል ማውሳት የልጅነት ግዴታ ነውና እጅግ በጣም ጥቂቱን እናውሳ።

ቅዱስ አባታችንን ልዩ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል በዚች መልዕክት ቀዳሚውን ሥፍራ የሚይዘዉ ነቢይነታቸዉ ነው። ነቢይነታቸው የሚገለጥባቸው ሥራዎች ደግሞ የቤተ ክርስቲያኒቱ ንብረት በእግዚአብሔር የለም ባይ መንግሥት እንደሚወረስ ዘመን ተሻግረው በማየታቸው ሰበካ ጉባኤን እንዲቋቋም ማድረጋቸው ነው።

የታሪክ ድርሳናት እንደሚያስረዱት ቅዱስ አባታችን ሰበካ ጉባኤን ለማቋቋም ሲወጡ ሲወርዱ ነቢይነታቸውን ያልተረዱና በተንኮል የተነሡ የውስጥ ተከላዎች ያደርሱባቸው የነበረው ፈተና ቀላል አልነበረም። ከአባቶቻቸው በወረሱት የትዕግሥት ጸጋ ሁሉንም ችለው ለቤተ ክርስቲያናችን ሕይወት የማዕዘን ድንጋይ የሆነውን ሰበካ ጉባኤ መሠረቱ።

የሚገርመው ግን ሰበካ ጉባኤ እንዳይቋቋም ያለስማቸው ስም በመስጠት ሲዘባበቱባቸው የነበሩት የውስጥ አርበኞች ዛሬ ላይ ሰበካ ጉባኤ ሰፍቶና ደምቆ ሲያዩት ታሪክ ለመሻማት በተለመደ ቅጥፈታቸው "ሰበካ ጉባኤን የመሠረትን እኛ ነን" ሲሉ ይደመጣሉ። እውነታው ግን ሃሳቡን በመጠንሰስ፤ ሕግ በማውጣት፤ አባታዊ አመራር በመስጠት ሰበካ ጉባኤን በኢትዮጵያ ያመጡ ብፁዕ ወቅዱስ አባታችን ናቸው። ሰበካ ጉባኤን ከቴዎፍሎስ፣ ቴዎፍሎስን ከሰበካ ጉባኤ ነጥሎ ማለትም አይቻልም።

ሌላው ቅዱስ አባታችንን ልዩ የሚያደርጋቸው ለትምህርት የነበራቸው አመለካከት ነው። ዛሬ በሕይወት ያሉ ልጆቻቸው እንደሚናገሩት ሥራ ስጡኝ ከሚሏቸው ይልቅ ትምህርት እንድማር እርዱኝ ለሚሏቸው ቅዲሚያ ይሰጡ ነበር። የዚህ ምስክሩ ደግሞ አሁን ቤተ ክርስቲያኒቱን በማገልገል ላይ ያሉ ሊቃውንት ከቴዎፍሎስ የትምህርት ምንጭ የተቀዱ መሆናቸው ነው። ዘር፣ ወገን ሳይለዩ ካህናትን እንዲማሩ አድርገዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ባለ ራዕይ አባትም ነበሩ። የቤተ ክርስቲያኒቱ እድገት አስቀድሞ ይታያቸው ስለነበር ራዕያቸውን እውን የሚያደርጉ አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስን ኮትኩተው አሳድገዋል። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በተደጋጋሚ እንደሚናገሩት "የነገዋን ቤተ ክርስቲያን የምትመራው አንተ ነህና ጠንክር" እያሉ ያበረታቷቸው ነበር። የተናገሩት አልቀረምና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ፈቃድ አምስተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሆነው ሲሾሙ የቴዎፍሎስ ራዕይ ዕውን መሆን ጀመረ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ልማት ኮሚሽንን፣ የሰንበት ት/ቤትን አቋቁመዋል። ቤተ ክርስቲያኒቱ ከእኅት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ግንኙነት እንዲኖራት ከማድረጋቸውም በላይ የመጀመሪያውን የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ በአዲስ አበባ እንዲካሄድ አድርገዋል። ቤተ ክርስቲያናችን በገቢ እራስዋን እንድትችል ያሠሯቸው ታላላቅ ሕንፃዎች፣ ማተሚያ ቤቶች፣ ት/ቤቶችና ልዩ ልዩ ተቋማት ቴዎፍሎስን ሲሰብኩ ይኖረሉ።

እኒህ ዘመን ተሻጋሪ የቤተ ክርስቲያን ባለውለታ አባት ባልፈጸሙት ጥፋት ባሳደጓቸው፣ ባስተማሯቸውና ለሹመት፣ ለሽልማት ባበቋቸው ልጆቻቸው ቆስቋሽነት የመከራው የመጀመሪያ ገፈት ቀማሽ እንዲሆኑ ተደረገ። ከውስጥ ቤተ ክርስቲያኒቱን ለማፍረስ በተነሣ ጊዜያዊ ጉባኤ/የተሐድሶ ኮሚቴ/ ከውጭ ደግሞ ያለ እጥማቂ እራሱን በማርክሲስት ሌኒኒስት አይዲዮሎጂ ባጠመቀ ከሃዲ መንግሥት እጅ ለሰማዕትነት በቁ።

ኢትዮጵያ የማንንም ሐዋርያ ደም ሳታፈስ ክርስትናን ብትቀበልም ዘግይታ ግን የልጅዋን የቴዎፍሎስን ደም በልጆቿ እጅ አፈሰሰች። መጽሐፍ "ፈደዩኒ እኪተ ህየንተ ሰናይት" እንዲል ለቤተ ክርስቲያን ዕድገት መላ ጊዜያቸውን የሰጡ ቅዱስ አባት በሰማዕትነት ማለፋቸው ሳይበቃ አፅማቸው የወደቀበት ሳይታወቅ ለብዙ ዓመታት ኖረ።

ተባርዮን የማያስቀር አምላክ ያ በኢትዮጵያ ሰፍኖ የነበረው ዘመነ ዲዮቅልጥያኖስ ሲወገድ በኢሕአዴግ የሽግግር መንግሥት ወቅት ከወደቀበት ተነሥቶ በግል ገንዘባቸው ባሠሩት በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በክብር እንዲያርፍ ተደረገ። ቅዱስ ሲኖዶሱም የሰማዕትነት ክብር ሰጣቸው። ሆኖም ግን እስከ አሁን ድረስ ስማቸው የሚጠራበት ተቋም ባለመሠራቱ ብዙዎችን ሲያስቆጭ ኑሯዋል።

ቅዱስ አባታችን እንደ ቤተ ክርስቲያን ባለውለታነታቸው በስማቸው በየአህጉረ ስብከቱ ልዩ ልዩ ተቋማት በተሠሩ ነበር። "ጊዜ ገቢር ለእግዚአብሔር" ነውና የብዙዎቻችን ሕልም እውን ሆኖ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የቅርብ ክትትል እና አመራር ይህ ት/ቤት በስማቸው ተሠርቶ ለምርቃት በመብቃቱ ካቴድራሉን ያሰመስግነዋል። ሁላችንንም አስደስቷል።

ከዚህ ት/ቤት ብዙ ቴዎፍሎሶች እንደሚወጡ ጥርጥር የለኝም። የብዙዎቻችንን ምኞት እውን ያደረጋችሁትን የካቴድራሉን አስተዳዳሪ፤ የሰበካ ጉባኤ አባላትን እና ጽ/ቤት ሠራተኞችን በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ስም ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ። ይህ ት/ቤት አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ ብሎ ኮሌጅ ዩኒቨርሲቲ እንዲሆን የሁላችንን እርብርቦሽ ይጠይቃል። አሁን ያለው የካቴድራሉ አስተዳደርና ሰበካ ጉባኤም ይህንን እንደሚያደርግ ጽኑ እምነት አለኝ።

የሰማዕቱ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መታሰቢያ አንድ ት/ቤት በመገንባት ብቻ በቃ ሊባል የሚችል አይደለም። የሰማዕትነት ክብርን ያጎናጸፋቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ልጆቹን አስተባብሮ በስማቸው ቤተ ክርስቲያን አሳንፆ ማየት የሁላችንም ኦርቶዶክሳውያን ጽኑ ምኞት ነው። ይህም ከልብ በሚወዷቸው ልጃቸው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ዘመነ ፕትርክና ተግባራዊ እንደሚሆን ከልብ እናምናለን። በስማቸው ጽላት ተቀርፆ፣ ቤተ ክርስቲያን ታንፆ ማየት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ኩራት ነውና!

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ሊቀማዕምራን ፋንታሁን ሙጬ
የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዋና ሥራ አስኪያጅ



www.ethiopianorthodox.org



መልአከ ፀሐይ ቆሞስ አባ ኃይለ መስቀል ይሄይስ የካቴድራሉ አስተዳዳሪ

## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ።

"ለሕዝቤ እረፍቴ በማደርግባት በቤቴ ስም የሚያስጠራ ቦታ እሰጣቸዋለሁ፤ ለዘለዓለምም የማይልፍ ስም እሰጣቸዋለሁ" ትርጓሜ ት.ኢሳ.56፥4 እንዳለ ነቢዩ በጥ ሰው ቢሞትም ሥራው ግን አይሞትም። እኛም ትንሽም ብትሆን ስንሠራ ይህን ማመን አለብን። በእኛ ትንሽ ሥራ ነገ ብዙ የሚሠራ ትውልድ ይፈጠራል፤ አሁን በትንሹም ቢሆን እየተዘከርን/እየፈጸምን/ ያለነው ይህንኑ ነው። የባለ ታሪኩን ታሪክ ማጉላትም ታሪክ መሥራት ነው። ምክንያቱም ዛሬ የምንሠራው ሥራ እኛ ያቀድነውና የጀመርነው ሳይሆን ጥልቅና እሩቅ የሆነ አስተሳሰብ የነበራቸው "መልካም እረኛ ነፍሱን ስለ በጎቹ አሳልፎ ይሰጣል" ዮሐ.10፥11 ብሎ ጌታ በቅዱስ ወንጌል እንደነገረን የሀገርና የሕዝብ ፍቅርም እስከ ሞት እንዲታመኑ ያደረጋቸው ድንቅና ብርቅ ኢትዮጵያዊ አባት 2ኛ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሰማዕት ያቀዱትን ነው። ዛሬ ክብሩው ዕቅዳቸው እንዱን ቦታውን ገዝተው ጠፍ የነበረውን አቅንተው አሁን ይህ ግዙፍ ሕንፃ ት/ቤት የቆመበትን /የታነፀበትን/ ሥፍራም አስጠርገው አስደልድለው ዙሪያውንም በድንጋይ ግንብ አሳጥረውታል። የቀረ ቢኖር ቤቱን መገንባት ብቻ ነው። እሱን ለማድረግ ቤቱን /ሕንፃውን/ ለመገንባት የሀገርና የሕዝብ ፍቅር የማይገባው የሥልጣኔና የምሁራን ጠላት የነበረው አፋኝና ጨቋኝ ሥርዓት መንግሥት ቢገድባቸውና በግፍ ቢገድላቸውም የማይሞተው ሕያው ሥራቸው በልጆቻቸው ጉልቶና ሰፍቶ ይቀጥላል።

የዛሬው የሕንፃ ት/ቤት ምረቃ ጅምር ነው። የቅዱስነታቸው የበጐ ዓላማ/ሥራ/ ራዕይ ለዘመናት የሚቀጥልና መጠነ ሰፊ ነው። በመሆኑም በየዘርፉ ይቀጥላል፤ አባቢታም ገና ነው። ትልቁ በጐ ሥራ ደግሞ ተአምር መሥራት የሚችለውን የሰው ልጅ ሀገር ተረካቢውን ትውልድ በቀለም በሥነ ጥበብና በሥነ ምግባር አንጾ ማሳደግ ነው። ፍላጐት ላለው በሩን መክፈት የመማር ዕድል ላልገጠመውና ዕድሉ ለጠበበት ዕድሉን ማመቻቸት።

ሰማዕቱ አባታችን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ይህን በማድረጋቸው የዛሬውን/የአሁኑን/ ዓለም አቀፋዊ አባት 5ኛውን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የጋራ ፕሬዝዳንትን አሳክለውና አስመስለው በነበሩበት ክብርና መንበር መተካት ችለዋል።

በእኔ አመለካከት ከዚህ የበለጠ ትውልድ የሚቀሰቅስ ጉልህ ተግባር የለም። ስለዚህ ሰማዕቱ ታላቁ አባታችን ዛሬ ላለነው ልጆቻቸው አንድም ዓመት፤ አንድም ዕለት ምንም ደቂቃና ሰዓት ሳናባክን ነገ የማይሞት ሥራ ለመሥራት ያለ እረፍትና ያለመታከት ለበጐ ሥራ እንድንሮጥና እንድንተጋ ላሳቅ የትጉሀነት ሐውልት አቁመውልናል ማለት ነው። ስለዚህ እኛም ትላንት የነበሩትን ዛሬም የሚሠሩትን አባቶቻችንን ፈለግ ተከትለን በረቀቀው ቴክኖሎጂ እያታገዝን ከመንፈሳዊው ጉን ለጉን ዘመናዊውን ጥበብ በመቅሰም በተለይም ትውልድ በመቅረጽና በመማር ማስተማሩ ሂደት በተመቻቸው የትምህርት ፖሊሲ እየተደገፍን ልንተጋ ይገባል በማለት መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

በመቀጠልም እኒህ በጐ ዓላማ የነበራቸው ታላቅ አስተዋይና እርቆ አሳቢ ልማታዊ፣ ዓለም አቀፋዊ ትጉህ እረኛ የሆኑት ሃይማኖታዊ አባት ያቀዱትን ለመተግበር በበጐ ሐሳብ፣ በምክር፣ በሙያ፣ በገንዘብና በአስተዳደሩም ዘርፍ እገዛ ላደረጋችሁና ከጐናችን በመሆን ላበረታታ ከሀገር ውጭም በሀገር ውስጥም ላሉት ሁሉ በሰማዕቱ በቴዎፍሎስ ስም የከበረ ምስጋና እናቀርባለን። ዋጋ ከፋዩ ጌታም ዋጋችሁን እንዲከፍልልን ዘወትር እንጸልያለን።✦

የቅዱሱ አባታችን በረከት አይለየን አሜን።
ከመልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መስቀል ይሄይስ
የካቴድራሉ አስተዳዳሪ





ርዕሰ አንቀጽ

# ታሪክ ወትውልድ ያስተበፅዕዎ

የሰው ልጅ ዘለዓለማዊ የሚሆንበት ሁኔታ አለ፤ ለዚህ የሚያበቃው መንገድ መልካም ሥራው ነው። የሰው ልጅ በሥራው ዘለዓለማዊ መሆን ይችላል። አዲስ ነገር በመፍጠር የሰውን ልጅ ከችግርና ከመከራ የታደጉ በአካል ሙተው ቢቀበሩም መቃብራቸው በጎ የሠሩለት የሕዝብ ልብ ስለሆነ በተቀረጹበት የሕዝብ ልቡና ውስጥ አድረው ከትውልድ ወደ ትውልድ ይተላለፋሉ። በዚህ ሁኔታ የታሪክ ባለቤቶች ስለሚሆኑ በተወሰነ ጊዜና ቦታ የሠሩት መልካም ሥራ በአካል የሞቱትን ሰዎች ዘለዓለማዊ ያደርጋቸዋል።

ይህን ከመሰሉት ጠንካራ ሰዎች መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሁለተኛው ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት/ፓትርያርክ/ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አንዱ ነበሩ።

ቅዱስነታቸው አሁን በአካል ባይኖሩም በሕይወት ዘመናቸው ለቤተ ክርስቲያኒቱ ባከናወኗቸው በርካታ በጎ ተግባራት ሲታወሱ ይኖራሉ። ቅዱስነታቸው ከሠሯቸው ዐበይት ተግባራት መካከል ጥቂቶቹን ብንጠቅስ ትምህርት፣ ስብከተ ወንጌል፣ የውጭ ግንኙነት፣ የወጣቶች የሰንበት ት/ቤት ማደራጃ መምሪያ፣ ቅርስ አጠባበቅ፣ ልማት፣ ሰበካ ጉባኤ አደረጃጀት ወዘተ ይገኛሉ።

ትምህርት ለመንፈሳዊም ሆነ ለሥጋዊ ዕድገት አቻ የሌለው መሣሪያ መሆኑን የሚረዱ በመሆናቸው የሀገሪቱ የትምህርት ሚኒስቴር የቦርድ አባል በመሆን ከማገልገላቸውም በላይ መንፈሳዊ ኮሌጅን በመመሥረትና በቅርብ በመከታተል ብዙ ምሁራን አባቶችን አስገኝተዋል። በመሆኑም በዘመኑ "ሹመት ያለ ከባስልዮስ ትምህርት ያለ ከቴዎፍሎስ" የሚል አባባል ይሰማ ነበር።

ስብከተ ወንጌል ለቤተ ክርስቲያን መስፋፋትና ጥንካሬ አስፈላጊ በመሆኑ በመላ ሀገረ ስብከቱ በአካል እየተገኙ እንዲቋቋም አድርገዋል። ቤተ ክርስቲያኒቱ ከውጪው ዓለም ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖራት ቤተ ክርስቲያኗን ወክለው ብዙ ጉባዔዎችን ተሳትፈዋል። የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ሲመሠረትም መሥራች አባል በመሆን ፈርመዋል።

ስለሆነም በቅዱስነታቸው የተፈረመው የማኅበሩ አባል መሆን በዘመናችን ከፍተኛ ደረጃ በመድረሱ የመንፈስ ልጃቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የምክር ቤቱ ፕሬዝዳንት ለመሆን በቅተዋል።

ወጣቱ ትውልድ ለቤተ ክርስቲያንም ሆነ ለሀገሪቱ ተተኪና አደራ ተረካቢ በመሆኑ ከቤተ ክርስቲያን እንዳይርቅ ለማድረግ በዋናው ጽ/ቤት በመምሪያ ደረጃ እንዲደራጅ አድርገው በየአጥቢያው ሰበካ የሰንበት ት/ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲቋቋም አድርገዋል።

ከዚሁ ጋር የቤተ ክርስቲያኗን ቅርስ በመጠበቅ በኩልም አሜሪካ ከሚገኝ ቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርሲቲ በጎ አድራጊ ድርጅት የገንዘብና የመሣሪያ ዕርዳታ በመጠየቅ የብራና መጻሕፍትን በማይክሮ-ፊልም አስቀርጸው ለተመራማሪዎች በሚመች ቦታ እንዲቀመጥ አድርገዋል።

ልማትን በተመለከተ ቤተ ክርስቲያን ከመንግሥት ጎን ተሰልፋ ርሐብን፣ በሽታንና ድንቁርናን ለማጥፋት በተደረገው ዘመቻ ተሳታፊ እንድትሆን አድርገዋል።

ቅዱስነታቸው ቤተ ክርስቲያኗ በወቅቱ የምታገኘው መተዳደሪያ ዘለቄታ የሌለው መሆኑን አስቀድመው በመገንዘባቸው እራሷን በራሷ ገቢ የምታስተዳድርበትን ሰበካ ጉባኤ በማቋቋም በቃለ ዓዋዲ እንድትመራ አድርገዋል።

ቅዱስነታቸው በአርቆ አስተዋይነታቸው ይህንን ተቅዋም ባያደራጁ ኖሮ የቤተክርስቲያን የመተዳደሪያ ንብረት የሆነው ሕንፃና ርስት በተወረሰ ወቅትና ከዚያም ወዲህ በቤተ ክርስቲያኗ በአገልጋዮቿም ላይ ይደርስ የነበረውን ችግር ለመገመት አያዳግትም። ይህንም ሰበካ ጉባኤ ማደራጀታቸው የሥራዎቻቸው ክንውኖች ሁሉ የድል አክሊል ነው።

ቅዱስነታቸው ሁሉም ሰው እንደሚመሰክረው ከመንፈሳዊ ሥራዎቻቸው በተጨማሪ በሰብእናቸው በትዕግሥት በችሎታና በአርቆ አስተዋይነት የተሞሉ ነበሩ። ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው የእስክንድርያው ፓትርያርክ አቡነ ሺኖዳ 3ኛ የተናገሩትን መጥቀስ ይቻላል። ይህም በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መነኮሳትን በእንግድነት ተቀብለው ባነጋገሩበት ወቅት "አባ ቴዎፍሎስ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አባቷ ብቻ ሳይሆን እናቷም ጭምር ነበር። ለቤተ ክርስቲያኗ ዕድገት ያልሆነው ያላደረገው የማያደርገውም ነገር አልነበረውም" በማለት መስክረውላቸዋል።

በአጠቃላይ ቅዱስነታቸው ለቤተ ክርስቲያኒቱ መንፈሳዊ ዕድገት በሁሉም ዘርፍ ከፍተኛ ተግባራትን አከናውነዋል። በመሆኑም ሥራቸውን ታሪክና ትውልድ ሲያስታውሱትና ሲያደንቁት ይኖራሉ። ይህም መልካም ሥራቸው ለአሁኑ ትውልድ አርዓያነታቸውን ተከትሎ መልካም ሥራ ለመሥራት እንዲችል ከፍተኛ መነሣሣትን ፈጥረውለታል።✦

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ዶ/ር ሐዲስ የሻነው



www.ethiopianorthodox.org

# የመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል አመሠራረት

የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል የተመሠረተው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 2ኛው ፓትርያርክ ሲሆን "ጎፋ ሠፈር" ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በ1946 ዓ.ም ከባሻ አብዬ ወራሾች ስፋቱ 72966 ካ.ሜ የሆነውን ቦታ በግል ገንዘባቸው ከገዙ በኋላ በ1955 ዓ.ም መቃኞ ውን አሠሩ።

በመቀጠል ወዲያውኑ አዲስ የሚሠራውን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ለማስጀመር በቂ ገንዘብ ስላልነበራቸው ለዚሁ ሥራ የሚጠቅም ሌላ የገንዘብ ምንጭ በመፈለግ በካሳንችስ አካባቢ ሁለት ቪላ ቤቶችና እንዲሁም በእስታዲየም አጠገብ በራስ ደስታ ዳምጠው መንገድ አቅራቢያ የሚገኘውን ባለ 4 ፎቅ ሕንፃ ከባንክ በተገኘው ብድር አሠርተው የባንኩ እዳ ተከፍሎ ሲያልቅ ከሕንፃው ኪራይ በተገኘው ገቢ በመጀመሪያ ዐፄ ዮሐንስ 4ኛ ያሠሩትን ታላቁን ደብር ደብረ ኤልያስን በ32,000.00/በሠላሳ ሁለት ሺህ ብር/ ካሳደሱ በኋላ ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን አዲስ የቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ሥራ በማስጀመር ከ4 ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አሰርተው በአካባቢው ለሚገኙ ምዕመናን አምልኮተ እግዚአብሔር ማካሄጃ እንዲሆናቸው በስጦታ አበርክተዋል።

የገቢ ምንጭ እንዲሆን የተሠራው ባለ 4 ፎቅ ሕንፃም ለዚሁ ለመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያንና ለደብረ ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ እንዲሆን ታኅሣሥ 1 ቀን 1959 ዓ.ም በቃል ኑዛዜ ሰጥተዋል።

በዚሁ በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን በስተግርጌ በቤተ ክርስቲያኑ ይዞታ ላይ የካህናት ማሰልጠኛ ጥበበ ዕድ አቋቁመው በሰልጣኞች የተሠሩት የምርት ውጤቶች አሁን ተሠርቶ በመጠናቀቅ ላይ ካለው መንፈሳዊና ዘመናዊ ት/ቤት በስተቀኝ በኩል ከቤተክርስቲያኑ አጥር ጋር ከተያያዘው ግንብ ላይ በጥርብ ድንጋይ 24 መስኮት ያለው የምርት ውጤቶች መሸጫ ሱቅ ተሠርቶ በዝግጅት ላይ እንዳለ አምባገነኑ የደርግ መንግሥት ሕግ አልባ በሆነው ሥርዓቱ ቅዱስነታቸውን ይዞ በማሰሩና በኋላም በመግደሉ ያ ሁሉ ጅምርና እቅድ ሳይሳካ ቀርቷል።

ከቤተ ክርስቲያኑ ጽ/ቤት በስተጀርባ ባለው ቦታ ላይ እናት አባት ለሞቱባቸው 200 ሕፃናት ማሳደጊያ የሚሆን የዕጓለማውታ ት/ቤት ፕላን ተዘጋጅቶ ሥራው በቅርብ ቀን ይጀመራል ተብሎ ሲጠበቅ እሱም እንዲሁ ተግባራዊ ሳይሆን ቀርቷል። በቅዱስነታቸውም እጅ የተጣለው የመሠረት ድንጋይ እስካሁን ድረስ የታሪክ ማስታወሻ ሆኖ አለ።

በቤተ ልሔም በስተጀርባ በኩል የሊቃነ ጳጳሳት ማረፊያ የሚሆን ሕንፃ ሊሠራ ቦታው ተጠርጎ በዝግጅት ላይ እንዳለ ሳይሠራ መቅረቱን አሁን በቦታው ላይ ያሉና በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ያስረዳሉ።

አዲስ የተሠራውን ሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ጥቅምት 17 ቀን 1967 ዓ.ም አስመርቀው ከመቃኞው ወደ አዲሱ ቤተ ክርስቲያን ታቦተ ሕጉን ካስገቡ በኋላ ጥቅምት 24 ቀን 1967 ዓ.ም በአካባቢው ያሉትን ምዕመናን በመሰብሰብ የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ ተሠርቶ አለቀ ባይባልም ከእንግዲህ ወዲህ "የቤተ ክርስቲያኑ አደራ ወይም ኃላፊነት ለእናንተ ነው" በማለት ጥብቅ አባታዊ የአደራ መልዕክታቸውን በአፅንኦት አስተላልፈዋል።

በቅዱስነታቸው የግል ገንዘብ የታነፀው ይህ ቤተ ክርስቲያንም በ1983 ዓ.ም . ካቴድራል ተብሎ ተሰይሟል።

ለማጠቃለልም ያህል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ነጥቦች ከፈጸሟቸውና ሳይፈጸሙ ከቀሩት መካከል በአካባቢው የሚኖሩ የምዕመናን ልጆች የሚማሩበት ት/ቤት ከቤተ ክርስቲያኑ ጐን ለጐን እንዲሠራ ቀደም ሲል ታቅዶ የነበረ ቢሆንም በነበረው እኩይ ሥርዓት ሳይሳካ ብዙ ዓመታትን ካስቆጠረ በኋላ በአሁኑ ወቅት መንግሥት በሰጠው ነፃነት ት/ቤቱ ተሠርቶ ትምህርት ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል። ይህም የሚያመለክተው የቅዱስነታቸው ጅምር ወይም እቅድ ተፈጻሚ መሆኑን ነው።

በሌላ በኩልም ቅዱስነታቸው ይህን ሰፊ ቦታ በግል ገንዘባቸው ገዝተው ቤተ ክርስቲያኑን ሲሠሩ የአካባቢው ምዕመናንና ልጆቻቸው በዚህ ሰፊ ቦታ ላይ ብዙ የልማት አውታሮች ተዘርግተው እራሳቸውንና ቤተ ክርስቲያኗን እንዲረዱ ነበር ዕቅዳቸው።

አሁንም ቢሆን የአካባቢው ምዕመናን ቅዱስነታቸው በግል ገንዘባቸው ቤተክርስቲያኑን አሳንፀው የአምልኮተ እግዚአብሔር ማካሄጃ እንዲሆን ማበርከታቸውን ከግምት ውስጥ በማስገባት በቤተ ክርስቲያኑ ፊት ለፊት ያለው አደባባይ በቅዱስነታቸው ስም እንዲሰየም አሁን ባሉት በካቴድራሉ አስተዳዳሪ በመልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መለኮት ይሄይስ ሐሳብ አመንጭነት ከአካባቢው ምዕመናን በተሰበሰበው ፊርማ ጉዳዩ የሚመለከተው ክፍል ተጠይቆና ተፈቅዶ የአደባባዩ ሥራ በአጥር ተከልሎና የውሃ መስመር ተዘርግቶለት የልማቱ ሥራ በመካሄድ ላይ ይገኛል። ይህም አንዱ የቅዱስነታቸው ትልቁ የታሪክ መዘክር ነው።

በመጨረሻም ቅዱስነታቸው ባሳነጹት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አሁን በሥራ ላይ ያሉ ካህናትና እንዲሁም በድጎማ የሚረዱትን ካህናት ጨምሮ በድምሩ 109 ሠራተኞች ያሉ ሲሆን ቤተ ክርስቲያኑ ከተመሠረተ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአስተዳዳሪነት የተመደቡት አለቆች አሁን አደባባዩን የሚያሠሩትንና በብዙ ጥረትና ድካም ት/ቤቱን ለማስመረቅ የበቁትን መልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መለኮት ይሄይስን ጨምሮ 24 ናቸው። የቤተ ክርስቲያኑ አመሠራረት ታሪክ ከብዙ ባጭሩ ይህንን ይመስላል።♦

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
በቀኝ ጌታ ስብሐት ዘዞ





# ትምህርተ ሃይማኖት

## ህልዎተ እግዚአብሔር

ህልዎተ እግዚአብሔር ማለት የእግዚአብሔር መኖር ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቱን ሲጀምር የእግዚአብሔርን መኖር መሠረት በማድረግ ነው እንጂ መኖሩን ለማረጋገጥ ምንም ዓይነት ሙከራ አያደርግም። /ዘፍ.1÷1/ የእግዚአብሔር ሰውም በእምነት እንደሚኖር ያስተምራል ዕብ.11÷6። ሳይንስና ቴክኖሎጂ በበዛበት፣ ፍልስፍና በተስፋፋበት በዚህ ዘመን ስለ ህልዎተ እግዚአብሔር ያሉት አመለካከቶች በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈሉ ናቸው። እነዚህም:-

- ❖እግዚአብሔር የለም ባይነት (Atheism)
- ❖መኖሩም አለመኖሩም አይታወቅም ባይነት (Agnostism)
- ❖እግዚአብሔር በእርግጥ አለ ብሎ ማመን /Theism/

እግዚአብሔር አለን? ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄም የሚመለሱ መልሶች እነዚህ ሦስቱ ናቸው። እነዚህን ሐሳቦች አጠር ባለ መልኩ አንድ በአንድ እንመልከታቸው።

1. **እግዚአብሔር የለም ባዮች** /Atheists/

ስለ እግዚአብሔር መኖር ማስረጃ ባይጠፋም የለም ብለው የሚከራከሩ አሉ። እግዚአብሔር የለም ባይነት በሌላ አገላለጽ እልከኝነት ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ምክንያቱም ብዙ ማስረጃዎች ያሉትን እውነታ ምንም ማስረጃ በሌለው ሐሰት መለወጥ ወደር የማይገኝለት እልከኝነት ነውና የዚህ ሀሳብ ተከታዮች የሆኑት ሰዎች አለመኖሩን ለማስረዳት ሲሞክሩ የሚገልጹት አለመኖሩን ሳይሆን እልከኝነታቸውን ነው።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ዓይነቱን አቋም በሮሜ 1÷18-32 ላይ የእግዚአብሔርን መገለጥ /እስተርእዮ/ አለመቀበል ብሎ ገልጾታል። ይህም በእመጻ የሚደረግ መሆኑን ገልጿል። ስለዚህ እግዚአብሔር የለም ባዮች የእግዚአብሔርን መገለጥ በተለያየ መንገድ እያወቁ የማይቀበሉ ናቸው። በዚህ አመለካከት /ክህደት/ ተይዘው ያሉ ሰዎች በሁለት ይከፈላሉ እነዚህም:-

- ሀ. የማይታየውን አምላክ በሚታዩ ጣዖታት የለወጡ፤
- ለ. የማይጨበጥ ሐሳባቸውን የሚያመልኩ ናቸው።

ሁለቱም በተመሳሳይ ክህደት ያሉ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ አምላክ አለን ብለው ያስባሉ ነገር ግን አምላክ ያልሆነው ጣዖት ተለውጦ አምላክ ስለማይሆን አምላክ የለሾች ናቸው። የእውነተኛ አምላክ ማንነትም ከእነርሱ የተሰወረ አይደለም። ምክንያቱም እውነተኛው አምላክ በተለያዩ መንገዶች እራሱ ራሱን ገልጾላቸዋልና። እነዚህ ሰዎች እውነትን በእመጻ የሚከለሉ /የሚሸፍኑ/ ናቸው። /ሮሜ 1÷20-25/ እያወቁ በእመጻ ስለካዱት እግዚአብሔርም ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው። /ሮሜ 1÷24-27/ ባለማወቅ የጠፉትን ግን እግዚአብሔር ወደ ማወቅ ብርሃን ያመጣቸዋል እንጂ እነርሱም የማይጨበጠውን ሐሳባቸውን ያመልካሉ። እነዚህ ሰዎች ለማይጨበጠው ሐሳባቸው ከማደር ይልቅ ለምን ለእውነተኛው አምላክ ማደር እንደከበደባቸው አይገባኝም። ለነገሩ የዚህ ዓለም ገዥ /ሰይጣን/ ሀሳባቸውን ስለአሳወረባቸው ነው /2ኛ ቆሮ.4÷4/።

2. **መኖሩም አለመኖሩም አይታወቅም ባይነት** (Agnostism)

ይህን ጽንሰ ሀሳብ ሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ "ኢ-ታዋቂነት" በሚል አንድ ቃል ተክተውታል። መኖሩም ኢ-ታዋቂ ነው። አለመኖሩም ኢ-ታዋቂ ነው ለማለት ነው። (Agnostism is the view to state that the evidence for God's existence is balanced by the evidence against)። ይህ ወደ አማርኛ ሲተረጎም አግኖስቲዝም ማለት እግዚአብሔር አለ በማለት የሚቀርበው ማስረጃና የለም በማለት የሚቀርበው ማስረጃ እኩል ናቸው የሚል ነው። አግኖስቲዝም ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባው በ2ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቢሆንም በእብዛኛው መስፋፋት የጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን /በ1825-1895/ ነው። የዚህ ሐሳብ ቀንደኛ አስፋፊ የነበረው ፈላስፋ ቤርትራንድ ራስል (Bertrand Russell) ነበር።

ትምህርተ ሃይማኖትና ክርስቲያናዊ ሕይወት /በሊቀ ጉባኤ አባ አበራ በቀለ 1996 ገጽ. 35 እና 36 ተመልከት/። ራስል (መጀመሪያ ሃይማኖትን ቢቃወምም በመጨረሻ ግን አምኖ እንደሞተ ተመራማሪዎች ይናገራሉ)።

የዚህ ሐሳብ አራማጆች መሀል ስፋሪዎች መስለው ቢታዩም ከሃይማኖት አንጻር ፍጹም ከሃድያን ናቸው። እነዚህን ክህዶቶች የቤተ ክርስቲያን አባቶች በብዙ መንገድ ተቃውመዋቸዋል።

ለምሳሌ:- አንስል የተባለ አባት የሊቁን የአውግስጢኖስን ሀሳብ በመደገፍ "ሰው እግዚአብሔር አለ ከሚለው ሃሳብ የበለጠ ማሰብ አይችልም" ሲል ተከራከረ። በእርግጥም እግዚአብሔር አለ ብሎ ማመንና ማስተማር "የለም" ወይም "መኖሩም አለመኖሩም አይታወቅም" ብሎ ከማስተማርና ከማመን እጅግ በጣም የበለጠ ስለሆነ ከዚህ የበለጠ ነገር ማሰብ አይቻልም። በእግዚአብሔር የማያምኑ ፈላስፋዎች ግን "መኖር መገኘት ነው እንደ ነገር ካልተገኘ የለም ማለት ነው" ብለው ያስተምሩ ነበር። ይህም ከንቱ ሀሳብ ነው። ያላገኘነው ሁሉ የለም ብሎ ማሰብ ሞኝነት ነውና።

**ሊቁ ቶማስ አኲናስ:-** ይህ ሊቅ ዓለምን በማየትና በመመርመር ስለ ዓለም በማስላሰል /በጥልቀት በማሰብ/ ፈጣሪ እንደ አለ ማወቅ ይቻላል ብሎ ይከራከር ነበር። ይህ ዓይነቱ ክርክር ደግሞ "The cosmological argument" በመባል ይታወቃል። ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ ይከራከራቸው ነበር።

**ለምሳሌ:-**

ሀ. **የሰው ግብረገባዊነት:-** ሰው ሁሉ በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃል። ሁሉም ሰው ኅሊና አለው። በህሊናውም ይወቀሳል። ስለዚህ ህሊና እንደ እግዚአብሔር ድምጽ ሆኖ ያገለግላል። እግዚአብሔር ባይኖር ኖሮ ይህ አንድነት ከየት መጣ ብለን እናምን ነበር? ብሎ ይከራከር ነበር። ይህ ዓይነት ክርክር ደግሞ "The moral Argument" በመባል ይታወቃል።

ለ. ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ አማልክት የሰዎች ስምምነት:- ሰዎች ሁሉ አንድ ነገር ሲያደርጉ ከበስተጀርባቸው ምክንያት አለ። ሰዎች ሁሉ ስለላይኛው ኃይል መኖር ግንዛቤ አላቸው። ይህም ከሆነ ስለፈጣሪ መኖር ማሰብና ማመን ተገቢ ነው። በዚህና በመሳሰሉት መንገዶች የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች የክህደት ሐሳቦች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ ሲከራከሩ ኖረዋል። በበለጠ እግዚአብሔር በእርግጥ አለ ብለው የሚያምኑ ሰዎች በሚለው ሦስተኛ ርዕስ ተብራርቶ ቀርቧል።

3. **የእግዚአብሔርን መኖር ማመን!**

እግዚአብሔር አለን? በሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ከተመለሱት ሦስት መልሶች መካከል አንዱና ብዙ ያስኬደው ምክንያታዊ መልስ አዎ አለ የሚለው ነው። ሁለቱ መልሶች ከአንዱ ቃል ወይም ከአንድ ዓረፍተ ነገር በላይ የማያናግሩ ቀራጣ ሀሳቦች ናቸው። ይህም "የለም" ወይም "መኖሩም አለመኖሩም አይታወቅም" የሚሉ መልሶች ከዚህ በላይ አያናግ



www.ethiopianorthodox.org

ሩም። ተስፋ የሰነቁ ቃላት ሳይሆኑ ሞት ያዘሉ ናቸው።

3.1. እግዚአብሔር አለ ካልን እን ዴት እናገኘዋለን?

የልዑል እግዚአብሔርን ህላዌ /አኗኗር/ በጠቅላላው የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ለመረዳት፣ አውቆ እንዲ ሀ ነው ብሎ ለማስረዳት እንደማይቻል ነቢያት፣ሐዋርያትና ከኋላ የተነሡ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በአንድ ድምጽ አረጋግጠዋል። ኤሊሁ የተባለ የኢዮብ ወዳጅ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስፈራ ግርማ አለ። ሁሉን የሚ ችል አምላክን እናገኝ ዘንድ አንች ልም። /ኢዮ.37÷22-23/

**ሐዋርያት፡-** ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ውእቱ ባሕቲቱ ዘኢ ይመውት ወቦቱ ብርሃን ዘኢይጠፍእ እምቅድመ ዓለም አልቦ ዘርዕዮ ሰብእ። ወአልቦ ዘይክል ርእዮቶ፤ እርሱ ብቻ የማይሞት ነው። ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራ ል። አንድ ሰው እንኳን አላየውም፤ ሊ ያየውም አይቻለውም" ብሏል። /1ኛ ጢሞ.6÷16/

**ጎርጎርዮስ ገባሬ መንክራት፡-** "እፎኑመ ነአምር ምሥጢሮ ለፈጣሪ ዘኢተፈጥረ ዘይትሌዐል ኵሎ ኀሊ ናተ፤ ያልተፈጠረና ከሐሳቦች ሁሉ በላይ ከፍ ያለውን ፈጣሪ እኛ ምሥ ጢሩን እንዴት ልናውቅ እንችላለን?" ብሏል። /ሃይማኖተ አበው ገፅ 41 ክፍል 2 ቁጥር 16/

3.2 እግዚአብሔርን ፈልገንና ተመ ራምረን ማግኘት ያልቻልነው ለምን ድነው?

ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት እግዚአብሔር ከፍጡራን አቅም በላይ ስለሆነ ወይም የፍጡራን አቅም ውሱን በመሆኑ ነው። ከላይ እንደተገለጠው ሰው በምርምር የሚያውቀው ቢሆን ኖሮ ጌትነቱና ክብሩ ጉድለት እንዳ ለበት ሊያስገምትም ይችል ነበር። ለዚህም ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ያሉትን እንመልከት።

**ዮሐንስ አፈ ወርቅ፡-** "እስመ ኢ ይትከሀል ለልሳን ይንብብ በእንቲአሁ ከመ ድልወቱ ወኀሊናሂ ኢይክል ሰሚአቶ ኀድግሰ ልሳነ ሕሊና ልብነ ዘይከብር እምኔሁ ኢይጤይቅ ምንተኒ እምኔሁ እስመ ንሕሊ በእንቲአሁ በብ ዙኅ ሐተታ ሎቱ ስብሐት ወንስእን ፈክሮ፤ "ስለ እርሱ /የእግዚአብሔር ኀላዌ/ እንደበት ሊናገር አይችልም። የልብ ኀሊናም ሊሰማ እንኳን አይቻ ለውም። የአንደበትን /ልሳንን/ ሁኔታ ተወውና ከእርሱ /ልሳን/ የከበረ የልብ ኀሊና እንኳን ከእርሱ ለመረዳት ያቅተዋል። ክብር ምስጋና ይግባውና ስለ እርሱ ብዙ እንመረምራለን። ዳሩ ግን መተርጎሙ ያቅተናል። /ድርሳነ ዘዮሐንስ አፈወርቅ ገጽ 24 ቁጥር 2/

<u>ቴዎዶጦስ ዘዕንቆራ፡-</u> "እስመ እግዚአብሔር ኢይትረከብ በህሊና እጓለ እመህያው፤ ወህሊና እጓለ ህያው ኢይረክብ መለኮተ፤ ወህላዌ መለኮት ርኑቅ እምኀሊና እጓለ መህያው፤ ወይትሌዐል ኵሎ ሕሊናተ ፈድፋደ፤ "እግዚአብሔር በሰው ልጅ ሐ ሳብ አይገኝም። የሰው ሐሳብም መለኮ ትንና የመለኮትን አኗኗር ሊያገኝ አይችልም። የመለኮት አኗኗር ከሰው ልጅ አስተሳሰብ የራቀ ነውና። ከሐሳቦችም ሁሉ ይልቅ በጣም ከፍ ያለ ነው። /ሃይማኖተ አበው ገጽ 171፡ ክፍል 1 ቁጥር 2/።

ከዚህ በላይ በአጭሩ እንዳየነው እግዚአብሔር በሰዎች ምርምር የማይ ገኘው ልዑል በመሆኑና የሰው ልጅ ኀሊና /ዕውቀት/ ሊደርስበት ባለመቻ ሉ እንጂ ሞኞች እንደሚሉት ስለ ሌለ አይደለም። አለመገኘት አለመኖር አይደለምና።

3.3 <u>ይህ ከሆነ እግዚአብሔርን</u> <u>እንዴት ማወቅ እንችላለን?</u>

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ምንም እንኳን እግዚአብሔር የማይ ታይ አምላክ ቢሆንም ለመኖሩ ራሱን ያለምስክር አልተወም። በልስጥራን ይኖሩ ለነበሩት ሰዎች ሐዋርያው ቅዱ ስ ጳውሎስና በርናባስ እንደመሰከሩላ ቸው፡- "መልካም ሥራ ሊሠራ ከሰማይ ዝናምን ፍሬ የሚሆንበትን ወራት ሲሰ ጠን ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲ ሞላው ራሱን ያለምስክር አልተወም" /የሐዋ.14÷17/ ብለዋልና። ይህም ማለ ት እግዚአብሔር መኖሩን በሥራ ይገልጻል ወይም ሥራው መኖሩን ይመሰክራል ማለት ነው። ባለቤት የሌለው ሥራ የለምና። በሌላ ቦታም እግዚአብሔር እርሱን መፈለግን በውስ ጣችን እንዳኖረ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለአቴና ሰዎች ተናግሯል /የሐዋ.17÷26/። ለዚህም ፍለጋ መነሻ እንዲሆን ሰዎች "ይህን ያደረገ ማነው?" ብለው እንዲጠይቁ የሚኖሩ ባቸውን የተወሰኑ ዘመናት ለሚኖሩ በት ሥፍራ ዳርቻ መደበላቸው። /የሐ ዋ.17÷27/

የእግዚአብሔር መኖርና ኃይል ለመረዳት የሚጠቅሙን ነገሮች

ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው እግዚአብሔር ራሱን ያለ ምስክር ስላልተወ እግዚአብሔርን ለማወቅ የሚረዱን ብዙ ነገሮች በዚህ ዓለም አሉ። እነዚህም፡-

ሀ. እግዚአብሔር በውስጣችን ያስ ቀመጠው ዕውቀት አንዱ ነው። ሰሎ ሞን በምሳሌው እንደገለጠው "የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው።" /ምሳሌ.20÷27/ ይህም በአን ዳንድ መምህራን "ተመርሆ ልቡናዊ" ይባላል።

ለ. ሥነ-ፍጥረት፡- እግዚአብሔር ራሱን ከገለጠባቸው ወይም መኖሩን ከሚመሰክሩ ነገሮች አንዱ ሥነ-ፍጥረት ነው። /ሮሜ.1÷20 መዝ.18/ 19÷1/ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባ ው ነገር ቢኖር በሐሰት አምላክ ነኝ ከማለት ወይም አምላክ ከመባል አልፎ አማልክት የተባሉት ሁሉ የአምላክነትን ሥራ አለመሥራታቸው ከዚያም አልፎ አለመሞከራቸው ነው።

እግዚአብሔር በነቢዩ በኢሳይያስ በኩል ከተናገረው ጠቅሰን ይህን ማረ ጋገጥ እንችላለን። "እኔ ፊተኛ ነኝ፤ እኔም ኋለኛ ነኝ፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም፤ እንደ እኔ ያለ ማነው? ይነሳና እኔ ነኝ ይበል፤ ይናገርም ከጥንት ጀምሮ የፈጠርሁትን ሕዝብ ያዘጋጅ ልኝ /ይመግብልኝ/ /ኢሳ.44÷6-7/ በማለት እግዚአብሔር ራሱን በሥራ ገለጠ። ጣዖታት /የሐሰት አማልክት/ ግን ያለ ሥራ እኛ ነን በማለት ብቻ ወይም እናንተ አማልክት ናችሁ በመባል ብቻ ተገለጡ።

ሐ. በአሁኑ ሰዓት ለፍጥረታት እየተደረገ ያለው መግቦት፡- ይህ መግቦት ሁሉን ቻይ በሆነ አምላክ ካልሆነ በቀር ሊገኝ የማይችል ነው።

መ. ፍጡርነትን መካድ አለመቻ ል፡- ፈጣሪ የለም ባዮች ሳይቀሩ እነርሱ ፍጡራን መሆናቸውን መካድ አይችሉም። ምክንያቱም የፈለጋቸውን ማድረግ እንዳይችሉ በፈጣሪ ተወስኖባ ቸዋልና።

ሠ. የማይመለሱ ጥያቄዎች በዓለ ም መኖራቸው፡- ከፍጥረት የሚነሡ ብዙ የማይመለሱ ጥያቄዎች አሉ። እነዚህንም ጥያቄዎች መመለስ የሚች ለው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ለምሳሌ፡- በዓለም ላይ ያለው ጦር ነት የሚቆመው መቼ ነው? መቆምስ ይችላልን? ለሚለው ጥያቄ ዓለም እር ግጠኛ መልስ መስጠት አትችልም። እግዚአብሔር ግን በቃሉ "ሞት ከእን ግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ ሐዘንም ቢ ሆን ወይም ጩኸት ወይም ስቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፤ የቀደ መው ሥርዓት አልፏልና" በማለት የሞት፣ የሐዘን፣ የጩኸትንና የስቃ ይን ሥርዓት እንደሚሽር በእርግጠ ኝነት ተናግሯል። /ራዕ.21÷4/ ነቢዩ ዳዊትም "እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ጦርነትን ይሽራል" በማለት እምነቱን ገልጿል። /መዝ.45/46÷9/

ስለዚህ ለዚህ ሥርዓት መፍረስ በእርግጠኝነት መናገር የሚችል እግዚ አብሔር ብቻ ነው። በዚህም መሠረት

ትምህርተ... ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org



# ራዕየ ቴዎፍሎስ ቀዳማዊ ሰማዕተ ጽድቅ ዘኢትዮጵያ

ራዕይ ዕቅድ ነው፣ ዕቅድም ራዕይ ነው፣ አንድ ሰው በሚማርበት ጊዜ ትምህርቴን ስጨርስ ይህን እሠራለሁ ብሎ ይመኛል ምኞቱ ራዕይ ነው። አንድ ሰው ሲሾም ይህን እሠራለሁ ብሎ ያስባል፣ ሐሳቡ እቅድ ነው እቅ ዱም ራዕይ ነው። አንድ ሰው በተሾ መ ጊዜ እሠራለሁ ብሎ ያሰበውንና ያቀደውን ራዕዩን በሥራ ለመተርጎም በቂ ጊዜ ያስፈልገዋል። ጊዜ ካገኘ በሥራ ላይ ያውለዋል፣ በሥራ ላይ ለመዋል ግን ረጅም ጊዜ ያስፈልገ ዋል። እንደ ራዕዩና እንደ እቅዱ ስፋትና ጥበት ብዛትና ማነስ የተመ ጣጠነ ዘመን ይጠይቃል፤ እቅዱ ወቅ ትና ጊዜ የሚጠይቅ ከሆነ እንደ ሁኔ ታው ለአፈጻጸሙ አመቺና ረዘም ያለ ዘመን ይጠይቃል። ባለሥልጣኑ ረጅ ም ጊዜ ካገኘ ያቀደውንና ያሰመውን በሙሉ ወይም በከፊል ሊፈጽመው ይችላል። ጊዜ ካላገኘ ግን ራዕይና ዕቅ ዱ ብዙና ሰፊ ቢሆንም በሥራ የሚተ ረጎመው በጣም አነስተኛውን ብቻ ነው ማለት ነው።

በዚህም ዓይነት አሁን ሊገለጥ የተፈለገው ረጅም ራዕይና ሰፊ ዕቅድ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እድገት አቅደው ሥዕለ ራዕያቸውንና ሰፊ ዕቅዳቸውን ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ሳያውሉት በግፍ ስለተገደሉት ስለ 2ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ስለ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ራዕይና ሰፊ የሥራ ዕቅድ ነው።

ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት በፓትር ያርክ እንደራሴነት 12 ዓመት በፓትር ያርክነት 5 ዓመት በድምሩ 17 ዓመ ት ያህል የኢትዮጵያን ቤተ ክርስ ቲያን የመሩ ሲሆን ለቤተ ክርስቲያኗ መልካ ም አስተዳደር እድገትና ልማት ብዙ እቅድና ሠፊ ራዕይ ነበራቸው። ከራዕያቸውም ውስጥ ብዙ ሥራዎች በዘመናቸው ተፈጽመዋል።

### ከነዚህም ጥቂቶቹ፡-

1. የሰበካ ጉባኤ መቋቋም
2. የሰንበት ት/ቤቶች መደራጀት
3. የልማት ኮሚሽን መቋቋም
4. ቤተክርስቲያናችን የዓለም አብ ያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥ ራች አባል እንድትሆን ማድረ ጋቸው፤
5. የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት እንዲመ ሠረቱና እንዲጠናከሩ ማድረጋ ቸው ይጠቀሳሉ።

ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከአቀዷቸው ሰፊ ዕቅዶችና በአህዝ የሚቆጠሩ ራዕያት ከፊሎቹ በ3ኛና በ5ኛው ፓትርያርኮች በሥራ ቢገለጡም አብዛኞቹ ገና በሥራ አልተ ተረጐሙም። የቅዱስነታቸው ራዕያት በዚህ አጭር ጽሑፍ ሊጠቃለሉ ስለማይችሉ ዋና ዋናዎቹ ብቻ ቀጥሎ ተጽፈዋል።

**ትምህርትን በተመለከተ!** ለቤተ ክህነት መንፈሳዊም ሆነ ማኅበራዊ አገልግሎት መክፈቻው ትምህርት ስለሆነ ቅዱስነታቸው በመንፈሳዊውም ሆነ በዘመናዊው ትምህርት ስላለፉበት ስለትምህርት ያላቸው ግንዛቤ ከፍተኛ ነበር። ስለሆነም በዲቁናም ሆነ በቅስና

በመንበራቸው የተቀመጡት ፓትርያ ርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ከነዚህ በከፍተኛ ደረጃ ከተመረቁት ምሁራን አንዱ ናቸው። ብፁዕ ወቅዱ ስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሥራ ይሰጡኝ ከሚሏቸው ያስተምሩኝ የሚሏቸውን ይወዱ ነበር። ቅዱስነታቸው የሰበካ ጉባኤን ሲያቋቁሙ ከሰበካ ጉባኤ አላማዎች አንዱ በርካታ ካህናት በእውቀትና በኑሮ ደረጃቸው እንዲሻ ሻሉ ብለው ነው። ከዚህም በመነሳት የካህናት ማሰልጠኛዎችንም እንዲከፈ ቱ አድርገዋል።

**የቤተ ክርስቲያንንና የካህናት አስተዳደርን በተመለከተ፡-** ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የሰበካ ጉባኤን በቃለ ዐዋዲ ደንብ ሲያቋቁሙ የቤተ ክርስቲያንንና የካህናትን አስተዳ ደር ለማስተካከልና በምጣኔ ሀብት



አቡነ ቴዎፍሎስ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት ቃለ ወንጌል ሲያሰሙ

በእልቅናም ሆነ በጵጵስና ደረጃ የሚሾሙ ካህናት በመንፈሳዊውም ሆነ በዘመናዊው ትምህርት ከፍተኛ ደረጃ የደረሱና የተማሩ እንዲሆኑ ራዕይ ነበራቸው። ከዚህም ራዕያቸው የተነሳ ብዙዎችን ወደ ሐረር ራስ መኮንን ት/ቤት እየላኩ 1ኛ ደረጃን፣ አያሌዎቹንም ወደ ቅድስት ሥላሴ ት/ ቤት እያስገቡ 1ኛ ደረጃን፣ 2ኛ ደረጃን፣ ከፍተኛ ዘመናዊና መንፈሳዊ ትምህርትን እንዲማሩ አድርገዋል።

በተጨማሪም አያሌ ደቀመዛሙር ትንም ወደ ውጭ ሀገር እየላኩ በማስ ተማር በዲፕሎማ፣ በዲግሪ፣ በማስት ሬትና በዶክትሬት የተመረቁ ሊቃውን ትንና ካህናትን አፍርተዋል። አሁንም

ለማዳበር መሆኑ እሙን ነው። አሁን በአዲስ አበባም ሆነ በመሠል ከተሞች ባሉ አብያተ ክርስቲያናት እንደምና የው ሳይሆን በዕውቀት ምሁራን ሆነው በቁጥር ግን ከ10ና ከ15 በማይበልጡ ካህናትና ዲያቆናት እንዲ ሁም መዘምራን እያንዳንዷ ቤተ ክርስቲያን እየተገለገለች ሀብቷ ለልማ ትና ለዕድገት፣ ለስብከተ ወንጌልና ለት/ቤት ማስፋፊያ እንዲውል ነበር። ይህም ራዕያቸው በቀኖና ቤተ ክርስቲ ያን "ወኢይብዙኑ ካህናት እለ ቤተ ክርስቲያን ከመ ኢይኅዕዕ ሲሳየ ለቤተ ክርስቲያን የቤተ ክርስቲያኗ ሀብት እንዳይሳሳና እንዳያንስ የቤተ ክርስቲ ያን ካህናት አይብዙ" ተብሎ የተጻፈ ውን መሠረት በማድረግ የታለመ ነው።

**መንፈሳዊ አገልግሎትን በተመለከተ፡-** የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ራዕይ እጅግ ድንቅና ሊከተሉት የሚገባ ራዕይ ነበር። የአበው ሐዋርያትን ቀኖና እና የአንድት አብያተ ክርስቲያናትን አሠራር የተከተለ ነበር። ለምሳሌ በምሥራቅ ኢትዮጵያ፣ በምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያና በሰሜን ኢትዮጵያ የካህናት እጥረት ስላለ በዕለተ ሰንበትና በበዓላት ቀናት ምዕመናን እንዳይቆርቡ ለጥምቀተ ክርስትና የሚመጡ ሕፃናትና ንዑስ ክርስቲያን ክርስትና እንዳይነሱ "ቀዳሾች አምስት አልሞሉም" እየተባለ ቅዳሴ ስለሚታጎል ከሁለትና ከሦስት ባላነሱ ቄስና ዲያቆን እንዲቀደስ በዘመናቸው በሲኖዶስ ተወስኖ ለየሀገረ ስብከቱ ውሳኔውን አስተላልፈው ነበር።

ነገር ግን ጎጂ ባህልና ልማድ የተቆራኛቸው ግለሰቦች በሚያካሂዱት እንቅፋት ራዕዩ በአብዛኛው በሥራ ላይ አልዋለም። በአስፈጻሚዎች ባለ ሥልጣናትም በኩል ድክመት ይታይ ነበር። አለማስተዋል በዝቶ እንጂ በውጭ ባሉ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት እየሄድን በሁለት አይደለም አሁንስ የምንቀድሰው?

**የገዳማት መነኮሳት አስተዳደርን በተመለከተ፡-** የቅዱስነታቸው ራዕይ እጅግ በጣም ተፈላጊ ነበር። እያንዳንዱ መነኩሴ በመነከሰበት ገዳም ፀንቶ በመማር ማስተማር፣ በጸሎትና በአስተብቁዖት እየኖረ በልማት ሥራ ግንባር ቀደም ሆኖ እየሠራ ገዳሙንም እንዲያገለግል ለአስተማሪነትና ለሌላ ሥራ ካልተፈለገና ካልተጠራ በስተቀር ገዳሙን ለቆ እንዳይሄድ በዘመናቸው በሲኖዶስ አስወስነው በየሀገረ ስብከቱና በየገዳማቱ ውሳኔውን አስተላልፈው ነበር።

**የካህናትን ዝውውር በተመለከተ፡-** ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የነበራቸው ሐሳብና ዓላማ መነኩሴ ገዳሙን ጥሎ ወደ ሌላ ገዳም፣ ቄስና ዲያቆን ደብሩን ጥሎ ወደ ሌላ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ወይም ከገጠር ወደ ከተማ ሄዶ በክህነት ሥራ መድቡኝ ብሎ ቢጠይቅ ከመጣበት ገዳም ወይም ደብር የገጠር ቤተ ክርስቲያን መሸኛና መታወቂያ ሳይኖረው ወይም ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሳይጻፍለት ባዶውን ከቀረበ ተቀባይነት እንዳይኖረው በሲኖዶስ አስወስነው አስተላልፈው ነበር።

**ስብከተ ወንጌልን በተመለከተ፡-** የቅዱስነታቸው ራዕይ ሰፊ ነበር። ገና በእንደራሴነት ሥልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ በሸዋ አውራጃዎች እየተዘዋወሩ የስብከተ ወንጌል ድርጅት አቋቁመው ነበር። በኋላም በቃለ አዋዲ የሰበካ ጉባኤን ሲያቋቁሙ ከሰበካ ጉባኤ አላማዎች አንዱና ዋናው ስብከተ ወንጌልን በክርስቶስ አምላክነትና መድኃኒትነት ላላመኑ አሕዛብ በማዳረስ ከኢትዮጵያ አልፈው የአፍሪካን አህጉር ለማስተማርና ለማጥመቅ ነበር።



በቅዳሴ ጊዜ ህዕበተ ዕድ ሲያድርጉ

**የሰንበት ት/ቤትን በተመለከተ፡-** የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ራዕይ ለሃይማኖቱ፣ ለሀገሩ፣ ለወገኑ የሚበጅ ትውልድ ለማፍራት እንደ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾ ማስተማሪያ መጻሕፍ ተዘጋጅቶ በሥርዓተ ትምህርቱ መሰረት ከ1ኛ እስከ 12ኛ ክፍል በአብያተ ክርስቲያናት የመማሪያ ክፍሎች ተዘጋጅተው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የቅዳሴ ዜማ፣ ትምህርተ ሃይማኖት፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና የምግባረ ሰናይ ትምህርት እየተማሩ እንዲያድጉ ነበር።

የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ራዕይ እጅግ በጣም ለቤተ ክርስቲያን እድገት የማያጠራጥር መፍትሄ ነበር። ይኸውም ራሳቸው በአቋቋሙት ደብረ ሊባኖስችም እንተበልም ባሉት በጎፋው ቅዱስ ገብርኤል የጥበበ ዕድ ማሰልጠኛ ት/ቤት ካህናት በተግባረ ዕድ ሙያ እየሰለጠኑ በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው በየገዳማቱ የተግባረ ዕድና ጥበብ ሥራዎችን እያቋቋሙ ከእንጨት ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ መንበር፣ መስቀል፣ መቋሚያ፣ ሌሎችንም ቅርጻቅርፆች ጨርቅ በመሳሰለውም ጥበበ ዕድ ልዩ ልዩ ምርቶችን በማምረት የምርት ውጤቶችን እያቀረቡ በሺያጩ የምጣኔ ሀብት ለቤተ ክርስቲያናቸውና ለገዳሞቻቸው ገቢ በውጤቱ ለቤተ ክርስቲያን የምጣኔ ሀብት እድገት እንዲገኝ ነበር። ይሁን እንጂ ይህ የልማት ሥራ የተጠበቀውን ያህል በየገዳማቱና በየአድባራቱ ባይስፋፋም በአንዳንዱ ገዳማትና አድባራት በመጠኑም ቢሆን ተቋቁሞ እንደ ትጥቅጥ መብራት ብልጭ ድርግም ሲል ይታያል።

**የምጣኔ ሀብትን በተመለከተ፡-** ቅዱስነታቸው የነበራቸው ራዕይ ያለ ገንዘብ ምንም ሥራ ለመሥራት እንደ ማይቻል ስለሚያውቁ ገንዘብ እንዳይባክን ብክነትን አጥብቀው እየተዋጉ ገንዘብ እንዲቆጠብ ወይም እንዳይባክን ያደርጉ ነበር። ገንዘብ እንዲቆጠብ የሚያደርጉትም ልማት ለማልማትና የቤተ ክርስቲያንን ምጣኔ ሀብት ለማሳደግ ባላቸው ራዕይ ነበር። በየአት ጣሚው ገቢ ከተገኘ ቤተ ክርስቲያኗ ከልመና እንድትላቀቅ ራዕይ ነበራቸው። ከልማት ከሚገኘው ገቢ ጋር በሰበካ ጉባኤ አስተዋጽኦ በሙዳየ ምጽዋት (መባዕ) የሚገኘው ገንዘብ ተጻም ሮ በማዕከላዊነት ከገባ በኋላ የካህናት ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ በአንድ ዓይነት ሚዛን እንዲሄድም ራዕይ ነበራቸው።

**ምግባረ ሰናይንና ክርስቲያናዊ ተራድኦን በተመለከተ፡-** የቅዱስነታቸው ራዕይ በቃለ ዓዋዲው ደንብ እንደተገለጠው በቤተ ክርስቲያን ሁለት ዓይነት የሙዳዩ ሳጥን ማለትም አንዱ ሙዳዩ መባዕ ሁለተኛው ሙዳየ

ራዕየ... ወደ ገጽ ፴ ዞሯል





# አካባቢያዊ ልማት እና ቤተ ክርስቲያን


ሀገራችን ኢትዮጵያ በበርካታ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጥያቄዎች የተከበበች ናት። እነዚህን ጥያቄዎች በአስተማማኝ ሁኔታ ለመመለስ ጥረት በተደረገባቸው ባለፉት ሺዎች ዓመታት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች ባለ ድርሻ አካላት ጋር ዋነኛ ተዋናይ በመሆን ስትንተሳተስ ኖራለች።

ለሀገር ድንበር መከበር ካበረከተችው አስተዋፅዖ ጎን ለጎን እንደ ሥነ ጽሑፍ፣ ኪነ ጥበብ እና ሥነ ሕንፃ ያሉ የሀገራዊ እሴቶች ምንጭ እና ባለአደራነቷም ከቶ የሚዘነጋ አይደለም። ከዚህ የተነሣ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የሚመለከት ዜጋ ኹሉ አስፋልት በማሠራት ቀጥተኛ ተሳትፎ ሲያደርግ ቆይቶአል። አሁንም እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አዳጊ አገሮች ወሳኝ በሆነው በሰው ኃይል ልማት ተሳትፎዋን ለማሳደግ በከፍተኛ ወጪ የትምህርት ቤት ግንባታ እያካሄደች ነው። የዚህ የማያቋርጠው መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልጋይነቱ ዛሬ ላይ ደርሶ ወደ አዲስ ምዕራፍ ተሸጋግሯል። ይህም በቅርቡ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በተደረገ ስምምነት መሠረት ከካቴድራሉ 300 ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውን የቅዱስ ገብርኤል አደባባይ በልማት ስም ተረክቦ ዘመናዊ አደባባይ በመገንባት ላይ ይገኛል።

መስጠታቸው ለምእመናኑ እና ለሰበካ ጉባኤው ከፍተኛ ደስታ እና መነቃቃትን ፈጥሮአል።

እንደሚታወቀው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በዘመናቸው ለቤተ ክርስቲያናችን ከፍተኛ አገልግሎት ያበረከቱ ሲሆን፤ በተለይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደርንና የሰንበት ትምህርት ቤትን በማቋቋም እንዲሁም ቤተ ክርስቲያኒቱ የውጭ ግንኙነት እንዲኖራት በማድረግ ባለ ውለታነታቸውን አስመስክረዋል። ለቤተ ክርስቲያንም ባላቸው ቅናት እና ተቆርቋሪነት እስከ ሰማዕትነት ደርሰዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ



ከቤተ ክርስቲያን ነጥሎ ማየት አይቻለውም። ነገር ግን የቤተ ክርስቲያን ስም የሚነሣው ካለፈው ዘመን ወርቃማ ታሪክ ጋር ብቻ ሳይሆን ከመጪው ዘመን ብሔራዊ ልማትም ጋር ነው። ከዚህ የተነሣ ከሀገር አቀፍ እስከ አካባቢያዊ ማኅበራዊ ጉዳዮች በጎ ጣልቃ ገብነቷን የማይሻ እና የማይጠብቅ የለም። እርሷም ብትሆን ይህን በሚገባ ስለምተገነዘብ ይሁንታዋ እና ድጋፏ በሚፈለግበት ቦታና ጊዜ ሁሉ አለሁ እያለች ትገኛለች።

በዚህ አተያይ ካቴድራላችንም ከቀድሞ ጀምሮ የአካባቢያችንን የጽዳት እና የጸጥታ መርሐግብሮች በመደገፍ፤ ድልድይ በመገንባት እና

## የአደባባይ ስያሜ

ይህ አደባባይ ለሀገራቸውና ለሕዝባቸው ከፍተኛ አስተዋጽዖ ላበረከቱ እንዲሁም ካቴድራላችንን ላሳነጹ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን 2ኛ ፓትርያርክ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ መታሰቢያ እንዲሆን እና ሐውልታቸ ውም በስፍራው እንዲቆም ከፍተኛ ፍላጎት አለ። ይህንም እውን ለማድረግ የአጥቢያው ምእመናን እና የካቴድራሉ ሰበካ ጉባኤ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ጥያቄ አቅርበዋል። ከዚህም በተጨማሪ ጥያቄው በቅዱስ ሲኖዶስ ደረጃ ተመክሮበት የጸደቀ ሲሆን፤ ቅዱስ ፓትርያርኩም ለጉዳዩ ትኩረት ከእነዚህ እና መሰል ተጋድሎዎች በተጨማሪ ከካቴድራላችን ጋር የሚያስተሳስራቸውን ደማቅ ታሪክም መጻፍ ችለዋል። ይኸውም በግል ገንዘባቸው ካቴድራላችንን ማሳነፃ ቸው፤ እንዲሁም ለካቴድራሉ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚውሉ በርካታ ልማቶችን እና የልማት እቅዶችን ማዘጋጀታቸው ይጠቀሳሉ። ከዚህ የተነሣ አደባባዩ በስማቸው እንዲሰየም በስፍራው ሁሉ ያሉ ምእመናን ያሳዩት ከፍተኛ መነሣሣት ቢያንስ ባቸው እንጂ የሚበዛባቸው አይሆንም።

## የአደባባዩ ሥራ ሌላ ገጽታ

የአደባባይ ሥራው ቤተ ክርስቲያናችን ለአካባቢያዊ ልማት ያላት

አካባቢያዊ..ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የማይደክም ጉልበት የማይሰለች አንደበት

"በዘነአምር ንነግር ወበዘ ርኢነ ሰማዕተ ንከውን፤ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውን እንመሰክራለን።" ዮሐ.3፥11

የሰው ልጅ ክቡር እንደ መሆኑ የሚያውቀውን ቢናገር ያየውን ቢመሰክር እንዴት መልካም ነበር። ክፋቱ ዓለማችን የማያውቁትን በሚናገሩ፤ ያላዩትን በሚመሰክሩ አልፍ አዕላፋት የተሞላች መሆኑ ነው። የምናውቀውን በመናገራችን ያየነውን በመመስከራችን ከሳሽ ወቃሽ ይነሣብናል ብለን ስጋት ውስጥ አልገባንም፤ መግባትም አስፈላጊ አልነበረም። ወደ ጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል በዋና አስተዳዳሪነት የተላኩት ሐምሌ 2000 ዓ.ም. ነበር። ዕድሜያቸው በ30ዎቹ የዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኛል።

ካቴድራሉን እየተሾሙ እስከ ዛሬ ድረስ ካስተዳደሩት 23(ሃያ ሦስት) አስተዳደሪዎች በዕድሜ ለጋውና 24ኛው አስተዳዳሪ ናቸው። ያለማጋነን ሲቀድሱ ሲያስተምሩ አምላክ ጸጋውን አብዝቶላቸዋል። እሱ ሲሰጥ መች ስስት ያውቅና! ቦታውንና አካባቢውን በልማት ለማሳደግ በሚያደርጉት የማያቋርጥ እንቅስቃሴ ከእንቅልፍ ጋር የተለያዩ ይመስላሉ።

ወደ ካቴድራሉ ከተላኩበት ጊዜ ጀምሮ የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን በማስፈጸምና የነበረውን ዕቅድ በፍጥነት ወደ ተግባር በመለወጥ እስከ አሁን ድረስ በቦታው ላይ ታይቶ የማይታወቅ የልማት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

ሙሉ ስማቸው ቆሞስ መልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መስኮት ይሄይስ ይባላሉ። ከካቴድራሉ የአስተዳደር ሠራተኞች፤ ከማኅበረ ካህናቱና ልዩ ልዩ ሠራተኞች ጋር በመመካከር፤ የአካባቢውን ኅብረተሰብ፤ ሰንበት ት/ቤቱንና ወጣቱን በማስተባበርና በማግባባት ያለ ዕረፍት ቀንና ሌሊት ይሠራሉ። ለአቀዱት ዕቅድ ይጠትማል ይበጃል ተብሎ የታመነበት ሰው በአካባቢው ካለ አያመልጣቸውም። በሚያሳዩት አባታዊ የአቀራረብ ስልት የእሳቸው ዋና አማካሪ ይሆንላቸዋል። በቅርብ ሆኖ የሚያያቸው በሩቅ ሆኖ የሚሰማቸው ሁሉ ዕድሜንና ጤናን ይመኝላቸዋል።

ቆሞስ መልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መስኮት ይሄይስ ቤተ ክርስቲያኗ ከመንግሥት ጎን ተሰልፋ የአካባቢውን ልማትና ውበት በመጠበቅ ረገድ የበኩሏን አስተዋጽኦ ለማበርከት እንድትችል ቀደም ሲል በተለምዶ "ገብርኤል ማዞሪያ" ተብሎ ይጠራ የነበረው መስቀለኛ መንገድ አሁን በአዲስ መልክ ተሠርቶ አደባባይ በመሆኑ ይህንኑ አደባባይ ለማስዋብ ቤተ ክርስቲያኗ በባለቤትነት እንድትረከብ የአካባቢውን ኅብረተሰብ፤ የሰንበት ት/ቤቱንና ወጣቱን በማስተ ባበርና በማግባባት ለመንግሥት ጥያቄ አቅርበው መንግሥትም ጥያቄውን ተቀብሎ በመፍቀዱ ሚያዝያ 17/2002 ዓ.ም. የአደባባይ ርክክብ እንዲፈጸም አድርገዋል።

ከርክክቡም በኋላ ከምዕመናንና ከወጣቶች የተውጣጣ ኮሚቴ በማዋቀር የአደባባዩን የማስዋብ ሥራ ለማስጀመር ቀን ከሌት በመሯሯጥ ላይ ይገኛሉ። አደባባዩም በታቀደለትና በጥላኑ መሠረት ተሠርቶ ሲጠናቀቅ በደርግ መንግሥት በግፍ በተገደሉት ለሀገርና ለወገን በርካታ ትሩፋትን በአስገኙት በ2ኛው የኢትዮጵያ ፓትርያርክ በሰማዕቱ በቴዎፍሎስ ስም እንዲሰየም ብሎም ሐውልታቸው እንዲቆም በቅዱስ ሲኖዶስ በኩል ለመንግሥት ጥያቄ ቀርቧል። ተግባ ራዊ ይሆን ዘንድም መልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መስኮት ይሄይስ አኩሪና ታሪካዊ የሥራ ክንውን በማካሄድ ላይ ይገኛሉ።

እኒህ አባት በአጭር ጊዜ ውስጥ አካባቢው ለምቶ በተለይም የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል በልማት በልጽጎና አድጎ ማየት የሚፈልጉ ባለ ብሩህ ተስፋ አባት ናቸው። ከዚሁ ጋር የካቴድራሉን የገቢ ምንጭ ከፍ ለማድረግ በካቴድራሉ በስተሰሜን በር በኩል በርካታ ሱቆችን እንዲሠሩ አድርገዋል።

በተጨማሪም በካቴድራሉ አካባቢ ያለውን መንገድ ለመቆፈር አንድ የውጭ ድርጅት ኮንትራት ወስዶ የቁፋሮ ሥራውን ሲያከናውን በወቅቱ እየተፈለጠ የወጣውን ድንጋይ ለካቴድራሉ የልማት ሥራ መዋል እንዳለበት በማሳመን ድንጋዩን ወደ ካቴድራሉ ግቢ ውስጥ በማስገባት የት/ቤቱ ቀሪ ሥራ፤ በስተ ሰሜን በኩል የተሠሩት የገቢ ማስገኛ ሱቆች ግንባታ ሥራ እንዲከናወን ከማድረ ጋቸውም በላይ አሁን በመልማት ላይ ያለው አደባባይም እየተሠራ ያለው በዚሁ መልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መስኮት ይሄይስ ታግለው ባስገኙት ድንጋይ ነው። ይህም በገንዘብ ሲተመን ከካቴድራሉ የገቢ አቅም በላይ በመሆኑ ጥረታቸው ባይታከል ልበት ኖሮ ይህ ሁሉ ሥራ ባልተሠራም ነበር።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በብዙ ሚልዮን የሚቆጠሩ የእምነቷ ተከታዮች ያሏትና አብያተ ክርስቲያናቱ የተተከሉበት ቦታም ሰፋፊ እንደመሆኑ መጠን ሁሉም በሥራ ኃላፊነት የተቀመጡ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ሰበካ ጉባኤውን፣ ካህናቱንና የአካባቢውን ሕዝበ ክርስቲያን በማስተባበር የልማት እንቅስቃሴ ቢያደርጉ ቤተክርስቲያኒቱ ከራስዋ ሠራተኞች አልፋ ተርፋ ለብዙ ሥራ አጥ ወጣቶች የሥራ ዕድል መክፈት የምትችል መሆኗን መልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መስኮት ይሄይስ በእርግጠኝነት የሚናገሩ፤ በልማት ዙሪያ የማይደክም ጉልበት፤ በስብከተ ወንጌል ዙሪያ የማይሰለች አንደበት ያላቸው ትጉህ አባት ናቸው።

የግል ጉዳያቸውን ወደ ጐን በመተው ለሀገርና ለወገን ጠቃሚ የልማት ሥራ በመሥራት ላይ ካሉት ከኒህ ጠንካራ አባት ጐን መሰለፍ በሰማይም በምድርም የከበረ ዋጋን የሚያስገኝ ነውና ቀርበን ልናበረታታቸው ልንደግፋቸውና ልናጠናክራቸው ይገባል እያልን በጽሑፉ መግቢያ ላይ የጠቀስነውን እውነተኛ ቃል ደግመን በመጥቀስ ምስክርነታችንን በዚሁ እንቋጫለን። "የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውን እንመሰክራለን።" ዮሐ.3፥11

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
በመጽሔቱ የዝግጅት ክፍል

"መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን ያከብሩት ዘንድ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ" ማቴ 5፥16



www.ethiopianorthodox.org



# በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ

አባ መልዕክቱ የተወለዱት በ1902 ዓ.ም ነው። በተወለዱበት ደብረ ገነት ኤልያስ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ጊዜ አስተዋይ፣ ረጋ ያሉ፣ ትሑት እና ራዕይ ያላቸው ስለ መሆናቸው የቀለም አባታቸው /መምህራቸው/ የንታ ገብረ ሥላሴ ብቻ ሳይሆኑ የደብሩ ካህናትም መስክረውላቸዋል።


በጽ/ቤታቸው

የተፈጥሮ አስተዋይነት የሚጻብረው በሰፊ ዕውቀት ሲደገፍ መሆኑን በመቀበል ትርጓሜ መጻሕፍትን ለመቀጸል /ለመማር/ በ1920 ዓ.ም ያቀኑት/የመጡት/ ወደ አዲስ አበባ ነበር። አዲስ ዓለም ገዳም ከነበረ ዕድ ሐዲስ ተክሌ /በኋላ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ/ ትርጓሜ ሐዲሳትን፣ ፍትሐ ነገሥትን፣ መዝሙረ ዳዊትን፣ ቀለሚንጦስን፣ አቡሻህርን፣ ወዘተ... ተምረዋል። አባ መልዕክቱ በተጨማሪ የመምህራቸው መልዕክተኛ በመሆን ከአዲስ ዓለም አዲስ አበባ እየተመላለሱ ጉዳያቸውን ያስፈጽሙላቸው ነበር። 65 ኪሎ ሜትር ያህሉን ርቀት የሚመላለሱትም በቢስክሌት ነበር። ከዛሬ 70 ዓመታት በፊት አንድ የቆሎ ተማሪ በብስክሌት ረጅም ጉዞ መሄድ የሚጠይቀውን ቁርጠኝነት፣ ታማኝነት፣ ጽናትና ትሕትና ዛሬ ላይ ሁነን መለስ ብለን ብናስበው አገልግሎታቸውን ብናደንቅላቸውም አእምሮአችን ለመቀበል ሊገድደው ይችል ይሆናል።

አባ መልዕክቱ ከጅምሩ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ የሚሄዱበትን ጎዳና አስልተው የሚራመዱ፣ ዓላማቸውን ለማስፈጸም የተጉ፣ ለሚጠስዱት እርምጃ ያልተጣደፉ ስለነበሩ በንጉሡ ዘንድ ክብርና ሞገስ ያገኙት በዚህ ችሎታቸው እንጂ በደጅ ጥናት አልነበረም።

አባ መልዕክቱ ለዕውቀት በነበራቸው አክብሮት መንግሥት ለቤተ ክርስቲያን የወደፊት እርምጃ ዘመናዊ ዕውቀትን እንዲቀስሙ ከተመረጡት መነኮሳት መካከል አንዱ በመሆን በዚሁ የተዘጋጀውን ትምህርት በሚገባ ያጠናቀቁ እሳቸው ነበሩ። ይህ አንዱ ጉብታ ላይ ሲደርሱ በቃኝ ሳይሉ ወደ ቀጣዩ አቀበት፣ ከዚያም ወደ ሌላው ተራራ፣ ያደረጉት ጉዞ ለዚህች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ዕድገት የምትፈልጋቸውን ሐዋርያዊ አገልግሎት ለማበርከት የነበራቸውን ምኞትና ጽናት ይመሰክራል።

በሥራ ችሎታቸውና በእውቀታቸው ከመምህርነት የሊቀ ሥልጣናት ማዕረግ ያገኙት መልዕክቱ በመንገድ ሲሄዱ ከሚያዩት እና ከማንኛውም ሰው ጋር ሲነጋገሩ ይማሩበት ነበር። እንደ አንድ መደበኛ ተማሪ ሂሳብ፣ ሳይንስ፣ ቋንቋዎችና የዓለም ታሪክን ከመጻሕፍት ይማሩ እንደነበረ በቤተ መጻሕፍት ቤታቸው ከነበረው የመጽሐፍ ክምችት ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሊቃውንት ጋር ያደርጓቸው የነበሩ ክርክሮች አፍ አውጥተው ይናገራሉ።

ሊቀ ሥልጣናት መልዕክቱ እስከዛሬ ድረስም አምሳያ እንዳልተገኘላቸው በወቅቱ በፈጸሙት ሐዋርያዊ ተግባር የራስ ወርቅ፣ የወርቅ ካባና የወርቅ መስቀሚያ የተሸለሙት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ታሪክ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ናቸው። ጳጳስ ከሆኑም በኋላ የካቴድራሉን አስተዳዳሪነት /ሊቀ ሥልጣናትነት/፣ ያቋቋሙትን መንፈሳዊ ኮሌጅን በተጨማሪ በበላይነት፣ ከ1942 ዓ.ም እንደራሴ ከሆኑበት ጊዜ ጀምረውም ቤተ ክርስቲያኒቱን ለ26 ዓመታት መርተዋል። ይህን ሁሉ ኃላፊነት በብቃት በመወጣታቸው ተወዳዳሪ አልተገኘላቸውም።

አቡነ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ እስከሆኑበት 1963 ዓ.ም. ድረስ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጎን በነበረው መኖሪያ ቤታቸው የአትክልት ቦታ በነበራቸው የሰውነት ማፍታቻ የስፖርት መገልገያዎችን እዘውትረው ይጠቀሙባቸው ነበር። ፓትርያርክ ከሆኑም በኋላ በእግራቸው የረዥም ሰዓት እንቅስቃሴ ያደርጉ እንደ ነበር ይታወቃል።

ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ በቤተ ክርስቲያን ዓውደ ምሕረት ላይ ዘመናዊውን ትምህርት ጭምር የቀሰሙ ብዙ ሊቃውንት እንደሚያስፈልጓት መገንዘባቸውን ያስመሰከሩት ገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት በተዘጋጀው ልዩ የትምህርት ፕሮግራም እንዲሳተፉ ሲመረጡ ነው። ለዚህም የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት እንዲከፈትና ቀጥሎም ወደ ኮሌጅ ደረጃ እንዲያድግ አደረጉ። የሀገሬ ስብከቶች አቅም እንደፈቀደ ሌሎችም ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱ ጥረት አድርገዋል።

## ታዲያ ቴዎፍሎስ በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ፣

*ቤተ ክርስቲያን ስንት ዩኒቨርሲቲዎች ይኖሯት ነበር? ስንት የቤተ ክርስቲያን እና የሀገር አገልጋዮች ይፈሩባቸው ነበር? ቤተ ክርስቲያኒቱ በዘመናዊ ትምህርት የላቁ ልጆች ሲኖሯት ምንኛ የሀገርና የአፍሪካ ኩራት ትሆን ነበር?*

ቤተ ክርስቲያን ወቅቱ በጠየቀው እና ጊዜው በፈቀደው ሥርዓት እንድትመራ የሚያስችል የተማረ የሰው ኃይል እጥረት በመኖሩ ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ የለውጥን ጎዳና ለመምራት ሲነሱ ከጎናቸው የሚቆም አጋዥ ባለመኖሩ አንገብጋቢነቱን ይገነዘቡ ነበር። አንድ ለእናቱ ከሆነው መንፈሳዊ ኮሌጅ ተምረው በሚወጡ ጥቂት ወጣቶች ለዚህች ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ተፈላጊውን አገልግሎት በአጭር ጊዜ ውስጥ በጥራት ለማዳረስ እንደማይቻል ስጋቱ ነበራቸው።

በሌላ በኩል ደግሞ ተጨማሪ መንፈሳዊ ኮሌጆችን ለመክፈት →

የአቅም ጉዳይ እንደሚገድባቸው ያውቁ ታል:: አማራጮችን መፈለግ የምሁርና የአርቆ አሳቢ ገንዘብ በመሆኑ እሳቸውም ከተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ፓትርያርኮች፣ ከታላላቅ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንቶችና ከሀገር መሪዎች ጋር በነበራቸው ግንኙነት ሁሉ የቤተ ክርስቲያኒቱን ችግር በማስረ ዳትግሪክ፣ ሩሲያ፣ ሩማንያ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይ፣ ጀርመን፣ የተባበሩት አሜሪካ፣ ካናዳ... በቲዎሎጂ፣ በሕግ በህክምና፣ በፍልስፍና.... ዘርፎች ብዙ ወጣቶችን እየላኩ አስተ ምረዋል:: ይህ የተቀደሰ ጥረታቸውም ቤተ ክርስቲያን በአዲስ ትውልድ ፍላጎትና በነበረው አሮጌ ሥርዓት መካከል በማዕበል እንደምትንገላታ መርከብ ችግር ቢገጥማትም እርሾ ሆነው ለማጠንከር የሚችሉ አባቶችን ለመተካት ባደረጉት ጥረት ዛሬም ምኞታቸውንና ዕቅዳቸውን ለማስፈጸም አምሳያቸውን ለማስቀመጥ ታድለ ዋል::

## ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ እስከ ዛሬ ቢኖሩ ኖሮ፣

በልዩ ልዩ የትምህርት ዘርፎች ብዙ የተማሩ ወጣቶች ተፈርተው ቤተ ክርስቲያን ለምዕመናን ልትሰጠው የሚገባት አገልግሎት የተሟላ ይሆን ነበር:: ቤተ ክርስቲያን ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለምዕመናን ልትሰጠው የሚገባት አገልግሎት የተሟላ ይሆን ነበር:: ቤተ ክርስቲያን ለራሷ ብቻ ሳይሆን የተማሩ ወጣቶችን ለሀገሪቱ ልማት ለማካፈል የነበራቸው ራዕይ እውን ይሆን ነበር:: እምነትን ከማይጠቅም ባህል፣ ልማድና ተረት በመለየት በነበራቸው ጥብብና ድፍረት የቤተ ክርስቲያኒቱን አንድ ጠጥ የእምነት ሥርዓት እንዲዳብር ያደርጉ ነበር::

ኢትዮጵያ የሊግ ኦፍ ኔሽንስ (League of Nations) አባል የሆነ ችው ስለዓለም ሰላም የምታበረክ ተውና እሷም በተራዋ የምታገኘው ድጋፍ እንዳለ በማመን ነው:: በኢጣሊያ ፋሽሽት ስትወረር በቻርተሩ የተዘ ረዘሩት መብቶቿ ባይከበሩላትም እየቆየች ግን በተለይ የአፍሪካ ነፃነት ብርሃን፣ በዓለም የፖለቲካ መድረክ ተሰሚና ሽምጋይ በመሆን ከበሬታ አግኝታ ነበር::

እንደዚሁም አባ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዓለም የምታበረክተው ሰፊ ትውፊት እንዳላት በመገንዘብ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር መሥራች አባል እንድትሆን በማድረግ በዓለም መድረክ ላይ ይዘዋት ብቅ አሉ:: ያላትን የተከበተ ባህልና ሥነ ጥበብ፣ ሥነ ኪን፣ ትርስ ለምስክርነት ለማቅረብ ቊጥር የተለያዩ ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች በኢትዮጵያ እንዲካሄዱ በማድረግ የቤተ ክርስቲያናቸውን ትልቅነት አሳይተዋል::

ለዚህም ዶር. ኢዩጅን ካርሰን ብሌክ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ዋና ጸሐፊ የነበሩ ስለ ቅዱስነታቸው ሲናገሩ ምሁርነታቸው፣ ለንጉሡ ያላቸው ቅርበትና ለቤተ ክርስቲያናቸው ያላቸው ራዕይ በአንድነት ተጣምሮ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ታላላቅ ሰዎች አንዱ ያደርጋቸዋል /የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ አጭር የሕይወት ታሪክ በፓትርያርክ ጳውሎስ ገጽ 46/ በማለት የቅዱስ የሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ዩኒቨርሲ ጉባኤዎችን በሊቀመንበርነት የመሩ ሲሆን ንግግር በሚያደርጉበትና በተለ ይም ነገረ መለኮትን ፈትፍቶ በማስረዳት በኩል ለነበራቸው ብቃት በየጉባ ኤው ላይ የሚገኙ ሊቃውንት እንደ ትምህርት ቤት ይቆጥሯቸው ነበር:: ቴዎፍሎስ በኦፊሴላዊ ወቅት ካልሆነ በስተቀር የተራ መነኩሴ ቆብና ፈረጅያ ስለሚለብሱ ፈረንጆች በተሳሳ ተ እንዲተርጓቸው አድርጓል:: ይህ ስብስ ናቸውም እሳቸውን ሳይሆን ቤተ ክርስቲያኒቱ ክብርና ሞገስ እንድታገኝ አድርጓታል:: እሳቸውም በሚያደር ጉት ውይይት ሁሉ የሌሎች አብያተ ክርስቲያናትን አደረጃጀት በቅርብ እንዲያውቁ አስችሏቸዋል በዚህ ዕውቀታቸው በአሜሪካ የታወቀው "ኒውዮርክ ታይምስ" የተሰኘው ትልቅ



አቡነ ቴዎፍሎስ ከዐፄ ኃይለ ሥላሴና ከእንግሊዟ ንግሥት ኤልሳቤጥ ጋር

ቲውን በጎበኙበት ጊዜ ባደረጉት ንግግር "... ፓትርያርክ ከሆኑም ወዲህ ጥረት የሚያደርጉ የሕዝባቸውንና የካህናቱን ሃይማኖታዊ ትምህርት ዘመናዊ ለማድረግና በቤተ ክርስቲያን ሥራ ውስጥ የምዕመናንን ተሳትፎ ለማሳደግ..." /ገጽ 54/ በማለት፣ የተባ በረችው የሚቶዲስት ቤተ ክርስቲያን ጳጳስ ዋሽንግተን ላይ ባደረጉት ንግግር "... በመጀመሪያ ቅዱስነታቸው ጠንካራ ክርስቲያናዊ መሪ ናቸው:: ለቤተ ክርስቲያናቸው ወሳኝ እርምጃዎች በሚወስዱበት ጊዜ እግዚአብሔር በአመራሩ ቁንጮ ላይ ጠንካራ እጅ እንዲኖር አድርጓል::... ቅዱስነታቸው የክርስቲያን እምነት ተቋሽ ናቸው... ታላቋ ቤተ ክርስቲያና ቸው ለመላው አፍሪካ ልታበረክት የምትችለውን ጠቃሚ ድርሻ በሚገባ ያውቃሉ ገጽ 62 ሲሉ መስክረዋል::

ቴዎፍሎስ ብዙ ዓለም አቀፍ ጋዜጣ ያለ ጊዜያቸውና ያለ ቦታቸው የተፈጠሩ ካሉበት ሀገር/አህጉር የላቁ ለማለት መሆኑ ነው/ The Black Pope /ጥቁሩ ፖፕ/ አሜሪካንን ይጎበ ኙሉ በማለት ጽፏል::

ቅዱስነታቸው በአሜሪካ ለአንድ ወር ያህል ተዘዋውረው የጎበኙት ዩኒቨርሲቲዎችን፣ አብያተ ክርስቲያና ትን፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ ታላላቅ የከበሩ እርሻንና ወተት ማዘጋጃ ድርጅቶችንና የማምረቻ ኢን ዱስትሪዎችን ነበር:: ከተጎበኙት ኢን ዱስትሪዎች አንዱ የፎርድ ተሽከርካሪ ማምረቻ ድርጅት ነበር:: ይህ ሁሉ ጥረት አገልጋዮቿ ካህናት በዘመና ዊ ዕውቀትና ክሂሎት ዳብረው በኅብ ረተሰቡ ውስጥ የነበራቸውን ተሰሚነት የበለጠ ከፍ ለማድረግና የልማት ሐ ዋርያት ለመሆን እንዲችሉ የልማት ኮሚሽንን በኃላፊነት ጋዜጣ

በሕይወት... ወደ ገጽ ፲፰ ዞሯል





# ግብረ ቴዎፍሎስ ቀዳማዊ ሰማዕት ጻድቅ ዘኢትዮጵያ

ማንም ያልቀደመው ማንነቱን በአደባባይ በእውነት ሥራ የመሰከረ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ሥራ ዘመንን ተሻጋሪ፣ ቤተ ክርስቲያንን አኩሪ፣ ስንፎችን አሳፋሪ፣ ህያው ምስለ ሕያዋን መንቅሌ መታን መሆኑን የተለየ ጭንብልካላበሰቁ በተር በግልጽ ይታያል:: ቴዎፍሎስ ማለት ፍቁረ እግዚአብሔር አርከ እግዚአብሔር፣ ተላዊ አምላክ ማለት ነውና::

እኒህ አባት በስማቸው ወደ ፈጣሪአቸው ተስበው ዓለምን ያስደነቀ ልሣነ ቀናዕያንን ያሳነቀ ተግባር ፈጽመዋል:: የሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ጽ በዘመድ የሚሸርጎደጎደውን የወሬ ወንጭፍ ሳይፈሩ ቅድስት ቤተ ክርስ ቲያንን የታደጉ ሐዋርያዊ ሰማዕት ናቸው:: ቅድስት ቤተ ክርስቲያን አግኝታ ያጣቻቸው እጅግ ውድ ሀብት ግብረ ቴዎፍሎስ ቀዳማዊ ነው::

በትንሽ ቀን ዘላቂ ስንቅ የቋጠሩላት፣ ግርማ ሞገስ በተቸረው አንደ በት መተዳደሪያዋን ያጸደቁላት፣ እራስ ዋን ችላ እንድትጓዝ በትረ ሃይማኖት ያስጨበጧት የመሪዎችዋን መወለጃ መሩረ አእምሮ ት/ቤት ያነጹላት የሃይማኖት ?፡፡ን መንፕረው መነጣጥ



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለጋዜጠኞች መግለጫ ሲሰጡ

ተግባር በሥራቸው ከብዙ በጥቂቱ የፈጣሪያቸውን የመምህራቸውን የኢየሱስ ክርስቶስን ፍኖተ ወንጌል ተከትለዋል:: መምህራቸው ኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌልን አስተምሮ፣ ተከታዮቹን መርጦ፣ የትዕግሥት ዝናር አስታጥቆ፣ ስንፍናን መለየትን ከመካከላቸው አርቆ፣ በመጨረሻም ዘርአ አዳምን በራሱ መሥዋዕትነት አስታርቆ መንገድ እኔ ነኝ በዚህ ሂዱ ብሎ እንደሚመለስ አስጠንቅቆ ጨርሷል:: ዮሐ.14÷6፤ የሐዋ.ሥራ 1÷9

ከሥራቸው እስከ ዕለተ ሞታቸው የአባቶቻቸውን ተግባር የከለሱት ጥቡዕ ሰማዕት ቴዎፍሎስ ዘመን የወለ ደውን፣ ጊዜ የወደደውን መስዬ ልኑር ሳይሉ ደመ ፍጡራንን በማፍሰስ የታወቀውን ጨካኙን የደርግ መንግሥትን ሳይፈሩ በግራ በቀኝ፣ በውስጥ በአፍአ፣ በቅርብ በሩቅ፣ በባሕ ረው ግልጽ ያደረጉላት እኚህ ምትክ የሌላቸው ሰማዕት ናቸው::

ቴዎፍሎስ እንደ ነቢያት ዘመና ትን ጥሰው ጠምሰሰው ያዩ ነቢይ ናቸው:: እንደ ሐዋርያትም በቶራጥ ተግባራቸው ታርደው፣ ተንቀው፣ ታን ቀው፣ ሟች በሆነው ምድራዊና ጊዜአዊ በሆነው እጅግ ጥቂት ዘመን ኢሳ. 33÷17 ዘለዓለማዊ ሥራ የሠሩ፣ ፈጣሪያቸውን መስለው ያለፉ፤ ድንቅ አባት ናቸው:: ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ እውነተኛ አባትዋን ያጣችበት ዘመን ቢኖር የሰማዕቱ ቴዎፍሎስ መሞት ነው:: ይህ ሲባል ግን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባል አድርገዋ ታል፤ ከማንም ተጽዕኖ ነጻ ሆና እንድትኖር ዓይነጥላዋን ገፈውላታል::

በመጨረሻ በሰማዕትነት መንገድ እጅግ ጠባብ በሆነው በር አልፈው አጽንተዋታል ይህም ጉዞ ያኮራታል፣ ያስመካታል፤ ማንነቷን ያስመሰክር ላታል፤ ቀና ብላ እንድትሄድ ያደር ጋታል:: ብዙዎቻችን ወደዚህ ዓለም ሳንፈቅድ እንመጣለን፤ ሰውኛ ኑሮአችንን እንቀጥላለን ግድ ነውና:: በእንስሳዊ ባሕርያችን እንመላለሳለን፤ የተሰወረን ነገር ቢኖር እንዴት መጣን? ከየት መጣን? ለምን መጣን? ብሎ አስቦ ሰጦታን ፈልጎ በስጦታው ተሰማርቶ እራስን፣ ወገንን፣ ሀገርንና በመጨረሻም በሕገ ልቡና በሕገ መጻሕፍት ተመራምሮ ያገኙትን እግዚአብሔርን ማገልገል ነው::

ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ከብዙ ኢትዮጵያዊውያን ተለይተው ይህን የግል ምሥጢር የተቸሩ ልዩ ፍጡር ናቸው:: እድገታቸውን በገዳም ቤት፣ ቀጣቸውን በትዕግሥት፣ ሥራቸውን በአስተዋይነት፣ ታሪካቸውን በዘላቂነትና ሕይወታቸውን በሰማዕትነት የደመደሙ እውነተኛውና የመጨረሻ ሐዋርያዊ አባት ናቸው::

ግብራተ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጋር አስተዋውቀው አባል በማድረጋቸው፣ በየቦታው የካህናት ት/ቤት ማሠራታቸው፣ የካህናት ማሠልጠኛ በየቦታው ማቋቋማቸው፣ የሀገር ውስጥ ካህናትና መምህራን ወደ ውጭ ሔደው የተለያዩ ቋንቋዎችና ሙያዎች ተምረው በመመለስ ቀልጣፋ ሥራ እንዲሠሩ ማድረጋቸው፣ ካህናት በአንስተኛ እደጥበባት እን ዲበለጽጉ ማበረታታቸው፣ በሕገ ቤተ ክርስቲያን ቃለ አዋዲ ቤተ ክርስቲያን እንድትመራ ማድረጋቸው፣ ራሳቸው ትሉ መዝሙረ ዳዊትን ተርጉመው ከማኅተም ጋር የተለያዩ መምህራን የሚያውቁትን ተርጉመው እንዲያሳትሙ ማነቃቃታቸው ወዘተ ናቸው::

የሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ሞት የጎዳው ቤተ ክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያንና ዓለምን ጭምር ነው:: ምክንያቱም ይህ ዓለም የሥራ ገበያ ነው:: የገበያው ሚዛን የሥራም ፋና ወጊ የዓለምም አቀራራቢ ነበሩና:: የሰው ልጅ ሞቱ በሦስት ዓይነት ይከፈላል፡- የሥጋ ሞት፣ የነፍስ ሞት፣ የታሪክ ሞት ይባላሉ::

ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ የመጀመሪያውን ሞተ ሥጋ ለታሪክ አስደሳች በሆነ ፈጣሪያቸውን መስለው በፈጣሪያቸው ትእዛዝ ሞተዋል::

ግብረ...ወደ ገጽ ፴፫ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# የማይረሳ ታሪክ



ወደ ጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ከተዛወርኩበት ቀን ጀምሮ ባለኝ የሥራ ኃላፊነት ስመለከት፦

- ❖ የካቴድራሉ ማኅበረ ካህናት፣
- ❖ የካቴድራሉ የአስተዳደር ሠራተኞች፣
- ❖ የአካባቢው ምእመናንና ምእመናት፣
- ❖ የሰንበት ት/ቤቱና የአካባቢው ወጣቶች በኅብረት ቤተ ክርስቲያኑና አካባቢውን በልማት ለማበልጸግ የሚያደርጉት ከፍተኛ እንቅስቃሴ እጅግ በጣም የሚያኮራ ነው።

እኔም እግዚአብሔር ፈትዶልኝ በተለይም የሰማዕቱ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ስም በየዕለቱ በሚጠራበት ቦታ ላይ ተገኝቼ በስማቸው በታነጸው ዝክረ ቴዎፍሎስ ት/ቤት የሥራ ሂደት ላይ በመሳተፌ ምን ጊዜም የማይረሳኝና ውስጣዊ እርካታን ያገኘሁበት ዕድል ነው።

ሌላው ሳልጠቅሰው የማላልፈው ቁምነገር፦ እንደ አለቃ ሳይሆን እንደ ጓደኛ፣ እንደ አዛዥ ሳይሆን እንደ ታዛዥ እራሳቸውን ዝቅ በማድረግ "ምን ልታዘዝ ወዳጄ" ከሚሉት ከመልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መለኮት ይሄይስ ጋር አብሮ መሥራት እጅግ የአስተዳደር ብልሐትን ያስተዋልኩበትና የተማርኩበት ከመሆኑም ባሻገር በእሳቸው ምክንያት በቦታው ላይ የማይረሳ ጥሩ ትዝታ እንዲያድርብኝ አድርጓል።

ለማጠቃለልም ያህል ዝክረ ቴዎፍሎስ ት/ቤት ሥራ ሲጀምር ተማሪዎቹ በመንፈሳዊና በዘመናዊው ትምህርት ጉልምሰው ነገ ቤተ ክርስቲያናቸውንና ሀገራቸውን የሚጠቅሙ ብቁ ዜጎች እንደሚሆኑ ምንም ጥርጥር የለኝም። ይህንንም ለማየት ያበቃን ዘንድ ለሁላችንም እግዚአብሔር አምላክ ረጅም ዕድሜን እንዲሰጠን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን።

የሰማዕቱ ቴዎፍሎስ በረከት በላያችን ላይ ይደርብን አሜን።

ሊቀ ሥዩማን ፍቅሩ መስፍን
የካቴድራሉ ዋና ጸሐፊ

---

## በሕይወት... ከገጽ ፲፮ የዞረ

አቋቋሙት። የወደፊት ሀገር ተረካቢዎች መሆናቸውን ቅድሚያ በመስጠት የሕጻናት ማሳደጊያ ድርጅት መሠረቱ።

### ታዲያ ቴዎፍሎስ እስከ ዛሬ በሕይወት ቢኖሩ ኑሮ፣

*ቤተ ክርስቲያን በልማት ዘርፍ የምታደርገው ተሳትፎ በሞዴልነት ብቻ ሳይሆን እንዴት ውጤታማ ይሆን ነበር? ስንት መቶ ሺህ ሕፃናት ከጎዳና ተዳዳሪነት ወጥተው ጠቃሚ ዜጋ እንዲሆኑ፣ ስንትስ ሕፃናት ማሳደጊያዎች ይቋቋሙ ነበር?*

አቡነ ቴዎፍሎስ ቤተ ክርስቲያኒቱ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የሚኖራትን ሚና ወደ መሪነት ደረጃ በማሸጋገራቸው እንደኛው ግብ የደረሰ ቢሆንም ይህንን ውጤት በአንድ እጅ እንደማጨብጨብ ነበር የተመለከቱት። የእኅት አብያተ ክርስቲያናት (Oriental Orthodox Churches) በየሀገራቸው በነበሩባቸው ችግሮች ተውጠው ምዕመናንን ለመጠበቅ እንቅፋቶች እንደተደቀኑባቸው በአንዳንድ ሀገሮች እንዲያውም እምልኮተ እግዚአብሔር ለመፈጸም መብታቸውን ተገፍፈው ሲጠራጥሩ ቴዎፍሎስ አንድ መድረክ ለማዘጋጀት ተንቀሳቀሱ። ከእነዚህ እኅት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ቴዎፍሎስ ያለብት ዓይነት ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ ለማዘጋጀት እንዳቸውም አቅም አልነበራቸውም። ቅዱስነታቸው ይህ በየስብሰባው ይቀርብላቸው የነበረውን ጉትጎታ እውን ለማድረግ የንጉሡን ፈቃድ ለማግኘት ሁለት ዓመታት ፈጅቶባቸዋል። "ተኮናኙ ኮናኝ" /በዓለማየሁ ዓለምነህ ገጽ 85/። ሲፈጠሩም የትዕግሥት ባለቤት ሁነው እንጂ የተመኙት የማይሞከረውን ነበር። እነዚህ እኅት አብያተ ክርስቲያናት በየራሳቸው ጎጆ ተወስነው ሳይገናኙ 1500 ዓመት አሳልፈዋል። ይህም ለመጨረሻ ጊዜ የተሰበሰቡት በኒቂያ ቴዎን ጉባኤ መሆኑ ነው። /ዓለማየሁ ዓለምነህ ገጽ 84/

እንግዲህ ቴዎፍሎስ ይህን ጉባኤ ማዘጋጀት ለምን ፈለጉ የሚለውን ለማወቅ ለአቶ አቤ ጉበኛ ከሰጡት ቃለ ምልልስ ከአንደበታቸው የተሰሙት ምክንያቶች፦

- ❖ ከጊዜ በኋላ የእስልምና ሃይማኖት በመስፋፋቱ የእነሱ አቅም በመዳከሙ አንድ የተባበረ ድምጽ ለመፍጠር፣
- ❖ በዓለም አቀፍ መድረክ በተናጠል ከመፍጨርጨር ይልቅ በኅብረት መንቀሳቀስ በማንኛውም ሊኖራቸው የሚችለው ተሰሚነት ከፍ ለማድረግ፣
- ❖ በግብፅ ቤተ ክርስቲያን አማካይነት ጉዳይ ማስፈጸም የሚለውን የኖረ አስተሳሰብና ትዕቢት ለመጨረሻ

በሕይወት... ወደ ገጽ ፳፮ የዞረ





# የዝክረ ቴዎፍሎስ ት/ቤት አመሠራረት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለትምህርት ቅድሚያ የሚሰጡ ታላቅ አባት ነበሩ። "ማንኛውም አገልግሎት የተሻለ የሚሆነው በእውቀት ላይ ሲመሠረት ነው" የሚል እምነት ነበራቸው። ይኸንኑ እምነታቸውን በተግባር በመተርጎም በሕይወት ዘመናቸው የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የሚሰጥባቸው ከአንደኛ ደረጃ እስከ ኮሌጅ አስገንብተዋል፣ በርካታ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ነፃ የከፍተኛ ትምህርት ዕድል እያገኙ ወደ ውጭ አገር በመሄድ እንዲማሩ የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል።

አባታችን ባሳነጹት የጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ይዞታ ላይም ካህናት በዕደ ጥበባት ሙያ የሚሰለጥኑበት የተሟላ ማዕከል አቋቁመዋል። ሕይወታቸው ለሰው ልጅ ክብር ግድ ባልነበራቸው ግፈኞች እጅ ባታልፍ ኖሮ በዚሁ ቦታ ላይ ሞዴል የሚሆን መንፈሳዊ ትምህርት ቤትም ለመክፈት ራዕይ ነበራቸው።

ቅዱስ አባታችን መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት የሚሰጥበት ትምህርት ቤት ለማሳነጽ የነበራቸውን ሐሳብ ከፍጻሜ ሳያደርሱት ቢለዩም የመንፈስ ልጃቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት ራዕያቸውን እውን ለማድረግ ሐምሌ 4 ቀን 1994 ዓ.ም. የሠረት ድንጋይ አኖሩ።

ዋናው ችግር ለትምህርት ቤቱ ግንባታ የሚውለውን ገንዘብ ከማግኘቱ ላይ ነበር። ይልቁንም የቅዱስነታቸው አጽም በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ካረፈ በኋላ መታሰቢያዎቻቸውን ለማሠራት ከፍተኛ ወጪ ተደርጎ ስለነበረ ሥራውን በራስ አቅም ለመጀመር ተስፋ ሰጪ ሁኔታ አልነበረም። በዚሁ የተነሳ በተለያዩ ጊዜያት ደብሩን በአስተዳዳሪነት ያገለገሉት አባቶች ከምኞት ያለፈ ተግባር ሳይፈጽሙ ዓመታት አለፉ።

ቢሆንም ሐሳቡ ከሰው አእምሮ እንዳይጠፋ የካቴድራሉ አስተዳደር በሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ስም አፀደ ሕፃናት ከፍቶ በመጠነኛ ክፍያና እንደ ሁኔታው በነፃም ለአካባቢው ኅብረተሰብ አገልግሎት ሲሰጥ ቆይቷል።

እያንዳንዱ ቀን ምን ይዞ እንደሚመጣ አይታወቅም። ስለሆነም ምን ጊዜም ቢሆን ዝግጁ ሆኖ መጠበቁ ጠቃሚ ነው። የደብሩ አስተዳዳሪ የነበሩት ሊቀ ሊቃውንት አባ ላዕከ ማርያም አየለ ይሕንኑ የሕይወት እውነታ በመገንዘብ የትምህርት ቤቱ ዲዛይን ተዘጋጅቶ እንዲቆይ ሐሳብ አቀረቡ።

በዚሁ መሠረት በደብሩ የሰበካ ጉባኤ አማካይነት በልማት ክፍል ሥር የተደራጀው የቴክኒክ ንዑስ ክፍል በሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ስም የሚሠራውን ትምህርት ቤት ጉዳይ እንዲከታተል ኃላፊነት ተሰጠው። ይህም ንዑስ ክፍል በውስጡ ባሉት ባለሙያዎች አማካይነት የሚሠራውን ሕንፃ የአርክቴክቸር ንድፍ በአጭር ጊዜ ውስጥ በነፃ አዘጋጅቶ አቀረበ። ንድፉም ለአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቀርቦ የካቲት 2/1996 ዓ.ም. የግንባታ ፈቃድ ተገኘ።

የቴክኒክ ንዑስ ክፍሉ ያዘጋጀው ዲዛይን በገንዘብ የሚሠራ ቢሆን ኖሮ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ወጪ ይጠይቅ ነበር። ንዑስ ክፍሉ ከዲዛይኑ ጋር የአንደኛ ደረጃና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የሚሰጥባቸው የአራት ብሎክ ሕንፃዎችን የመሠረት /ሰብ ስትራክቸር/ ወጪ ግምት አቅርቧል። የወጪውም ግምት በወቅቱ ገበያ መሠረት ብር 498,372.60 (አራት መቶ ዘጠና ስምንት ሺ ሦስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከ60%) ማንቲም ነበር።

የደብሩ አስተዳደር ያቀደው የትምህርት ቤቱ መሠረት ሐምሌ 4/1994 ዓ.ም. ከተጣለ በኋላ ማስጨረሻውን ገንዘብ በተለያዩ መንገዶች ለማሰባሰብ ነበር።

ይሁን እንጂ ለመሠረቱ እንኳን የሚሆን ገንዘብ ስላልነበረ ሥራውን በተፈለገው ፍጥነት ለመጀመር አልተቻለም። ወጪው የማይደፈር መስሎ በመታየቱ ሕንፃው ሳይሆን ዲዛይኑ ብቻ እየታየ ወራት አለፉ። ይህ ደግሞ ባለድርሻ አካላትን ሁሉ አስጨንቋል።

በመጨረሻ ግን ጊዜው ሲደርስ የደብሩ አስተዳዳሪ ካህናትና ሠራተኞች ጉዳዩን ለዕድል መስጠቱ መፍትሔ እንደማይሆን በገንዘብ የተቻላቸውን ያህል እየተፍጨረጨሩ የድረሱልን ጥሪ ለማሰማት ወሰኑ።

ጊዜው ጥቅምት 1997 ዓ.ም. ነበር። የደብሩ ማኅበረ ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች ከሐምሌ 1996 ዓ.ም. እስከ መስከረም 1997 ዓ.ም. የሦስት ወር የደመወዝ ጭማሪ ጸድቆላቸው ለመቀበል በዝግጅት ላይ ነበሩ። "ለምን የሦት ወር የደመወዝ ጭማሪያችንን ለት/ቤቱ ግንባታ ማስጀመሪያ አናውለውም?" በማለት ስምምነት ላይ ደረሱ።

እነዚህ ፍቅረ ቴዎፍሎስ ያገበራቸው ለግል ጥቅማቸው ሳይጓጉ ሀገራዊውን ዓላማ በደስታ በመቀበል የሦስት ወር የደመወዝ ጭማሪያቸውን ለት/ቤቱ ግንባታ ማስጀመሪያ እንዲውል ፈቀዱ። በዚህ ሁኔታ 25,380.00(ሃያ አምስት ሺ ሦስት መቶ ሰማንያ) ብር ተገኘ። የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን ራዕይ እውን ለማድረግ ፈር ቀዳጅ የሆነው እርምጃ የተወሰደው በዚህ ሁኔታ ነበር።

የት/ቤቱን የግንባታ ሥራ ለመጀመር ቦታው መዘጋጀት ስለነበረበት ከካቴድራሉ ካህናትና ልዩ ልዩ ሠራተኞች በተገኘው ገንዘብ ቦታው ተጠረገበት። በዚሁ ዝክረ ቴዎፍሎስ ት/ቤትም ለመገንባት የተስፋ ጭላንጭል መታየት ጀመረ።

ነገር ግን የተገኘው ገንዘብ ቦታውን በማስጠረጉ ሥራ ብቻ ስላለቀ የግንባታውን ሥራ ለመጀመር አልተቻለም። በዚሁ ምክንያት ያለምንም ሥራ ብዙ ጊዜ አለፈ። የተጠረገውም ቦታ ዳዋ ወደ መልበሱ ተቃረበ። "ችግር የፈጠራ እናት ናት" እንደሚባለው ችግርን ለማሸነፍ መታገሉን በመምረጥ ገቢ ለማስገኘት ስለሚቻልበት ዘዴ በመመካከር የገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ ተደረገ።

ከእንቅስቃሴዎቹ አንዱ ከካቴድራሉ እስከ ላፍቶ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ድረስ የእግር ጉዞ በማዘጋጀት ቲ-ሸርት፣ ኮፍያ፣ ለስላሳ መጠጥ በመሸጥ ገቢ ማሰባሰብ ነበር። ይህም ተደርጎ መጠነኛ ገቢ ተገኘ። በዚሁ የእግር ጉዞ ወቅት ቅጽ አዘጋጅቶ በመበተን ምዕመናን ለት/ቤቱ ግንባታ ሥራ ምን ያህል ገንዘብ



www.ethiopianorthodox.org

መለገስ እንደሚችሉ ቃል እንዲገቡ ተጠየቀ። በዚህም መጠነኛ ገንዘብ ተገኘ።

ይህ ብቻ በቂ ስላልነበረም በካቴድራሉ የምዕራብ በር በኩል ሱቆች ተሠርተው እንዲከራዩ ተደረገ። በዚህ ሁኔታ የተገኘው ገንዘብ የት/ቤቱን ሕንፃ ግንባታ ሥራ ለማንቀሳቀስ ቢችልም ይህም በቂ አልነበረም። ስለዚህም ተጨማሪ ገንዘብ ለማግኘት በካቴድራሉ ይዞታ ላይ የነበረው የባሕር ዛፍና ሣር በጨረታ እንዲሸጥ ተደረገ። ከዚህ በተጨማሪ ለት/ቤቱ መሥሪያ ብቻ የሚውል በካቴድራሉ ግቢ ውስጥ የሙዳየ ምጽዋት ሣጥኖች ተሠርተው እንዲቀመጡ ተደረገ።

ከምዕመናን የተገኘው ምላሽም ተስፋ ሰጭና አበረታች ነበር። እጁ የማይነጥፈው ሕዝበ ክርስቲያንም ሙዳየ ምጽዋቶቹን በገንዘብ ሞላቸው። ምዕመናን በግንባር እየቀረቡ የገንዘብ እርዳታ አደረጉ። የግንባታ መሣሪያና ለግንባታው የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን በነፃ ሰጡ። ባለሙያዎችም ዕውቀታቸውን በነፃ አበረከቱ።

በመሆኑም ሕዝበ ክርስቲያኑ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስና ለነበራቸው ራዕይ ያለውን ፍቅርና አክብሮት የገለጸው በዚህ ሁኔታ ነበር። ምንም ዓይነት ምስጋና ሳይጠብቁና ዋጋ ሳይጠይቁ ለት/ቤቱ ሕንፃ ግንባታ የተረባረቡትን ሁሉ ከዚህ ላይ ለመዘርዘር ከቁጥሩ አያሌነት የተነሳ አስቸጋሪ ይሆናል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤልን ካቴድራል ለማሳነጽ በገዙት ቦታ ላይ የልማት ሥራ የጀመሩት የባሕር ዛፍ በማስተከል ነበር። ይህም ባሕር ዛፍ በሽያጭ መልክ ለት/ቤቱ ሕንፃ ግንባታ የገቢ ምንጭ ከመሆኑም በተጨማሪ ለማገርና ለወራጅ እንዲሁም ለመወጣጫ መሰላል መሥሪያ አገልግሎት ውሏል። ለግንባታው ሥራ የዋለው አብዛኛው ድንጋይም ተቆፍሮ የወጣው ከዚሁ የካቴድራሉ ቦታ ላይ ነው።

በወቅቱ ማንነታቸውን ሳይገልጹ ድንጋይ፣ ጠጠርና አሸዋ እየመጡ በግንባታው ሥፍራ ላይ የሚያፉ ምዕመናን ብዛት ደግሞ ቀላል አልነበረም። ዝክረ ቴዎፍሎስ ት/ቤትን እውን ያደረጉትም እነዚህ ሁሉ ተዳምረው ነው።

ከታኅሣሥ 1997 እስከ ግንቦት 30/2002 ዓ.ም.
ለት/ቤቱ ግንባታ የገቢና የወጪ ዝርዝር

| ገቢ፤ | ብር |
|---|---|
| 1. ከሙዳየ ምጽዋት | 2,188,036.44 |
| 2. ከቅ/ገ/ማኅበርተኞች | 75,000.00 |
| 3. በውጭ ሀገር ከሚኖሩ ዘንᵔ አድራጊዎች | 77,632.43 |
| 4. ከባሕር ዛፍና ሣር ሽያጭ | 30,000.00 |
| 5. ከቲ-ሸርት፣ መጽሔት፣ ስዕላትና ቪዲዮ ካሴት ሽያጭ | 55,245.00 |
| ድምር | 2,425,913.87 |


| ወጪ፤ | ብር |
|---|---|
| 1. ለግንባታ ቁሳቁስ መግዣ | 1,402,485.33 |
| 2. ለሙያተኛና የጉልበት ሠራተኛ | 429,723.85 |
| 3. ለልዩ ልዩ አገልግሎት | 231,096.05 |
| ድምር | 2,063,305.23 |

በገንዘብ ተተምነው ያልተካተቱ ወጪዎች:-

1. ምዕመናን ማንነታቸውን ሳይገልጹ ያበረከቱት ጠጠርና አሸዋ።
2. ለወራጅ ማገርና መወጣጫ መሥሪያ ከካቴድራሉ ይዞታ ላይ የተገኘው የባሕር ዛፍ።
3. ከካቴድራሉ ይዞታ ላይ ተቆፍሮ የተገኘው የግንባታ ድንጋይ።
4. የት/ቤቱ ዲዛይን የተሠራበትና
5. በነፃ የተበረከተው ሚክስርና ፎርም ወርክ ናቸው።

የነዚህ ግብአቶች ግምት በገንዘብ ቢሰላ ከ2,063,305.23 ሊበልጥ እንደሚችል ግልጽ ነው።

ከላይ የተመለከተው ገቢና ወጪ ሲመዛዘን ብር 362,608.64 ይቀራል። ነገር ግን ከዚሁ ገንዘብ ላይ ከት/ቤቱ ውጭ ለሆኑ ሌሎች የልማት ሥራዎች ብር 128,202.51 ወጪ የተደረገ በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ በባንክና በእጅ ያለው ገንዘብ ብር 234,406.13 ብቻ ነው።



ዝክረ ቴዎፍሎስ ትምህርት ቤት ሕንፃ ሁለት ብሎክ

ይህን ት/ቤት ለመገንባት ተይዞ የነበረው እቅድ ሁለት ብሎክ ያሉት የ1ኛና 2ኛ ደረጃ ሕንፃ ለመገንባት ነበር፤ ነገር ግን በተገኘው ገንዘብ

የዝክረ... ወደ ገጽ ፳፬ ዞሯል





# ፓትርያርክ ቴዎፍሎስና የውጭ ግንኙነት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ 2ኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ የነበሩት በአረመኔው ፋሽስታዊ የደርግ መንግሥት በአሰቃቂ ሁኔታ ያለምንም አበሳ ሰማዕትነትን ተቀብለው ማረፋቸው ተደጋግሞ ተገልጿል።

ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ልዑል እግዚአብሔር እውቀቱን፣ ጥበቡን፣ እርቆ ተመልካችነቱን፣ ትዕግሥቱን በሰፊው የቸራቸው ሲበዛ ታላቅ መንፈሳዊ አባት ነበሩ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በረጅም ጊዜ ታሪኳ ካፈራቻቸው ታላላቅ መንፈሳዊ አባቶች አንዱ መሆናቸው እሙን ነው። ይህ ብቻ አልነበረም የተሰጣቸው ተውህቦ፣ አካላዊ ለዚህ አባባል ማጠናከሪያ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌን በዋቢነት ይጠቅሳሉ። ፕሮፌሰር ጌታቸው ገና ተማሪ ሳሉ ቅዱስነታቸው ያቀርቧቸው ስለነበረ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን ሲጎበኙ፣ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ስብሰባዎች ላይ ሲሳተፉ ያጀቡአቸውና ያማክሯቸው ስለነበር ቅዱስነታቸውን በሚገባ ያውቋቸዋል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ቤተክርስቲያንን ለማጥፋት ድብቅ አጀንዳ ይዞ በእነ ኮሎኔል አጥናፉ የተቋቋመው ኮሚቴ አባል ስለነበሩ ስለ ኮሚቴው ስውር ዓላማ ሲገልሁ እግረ መንገዳቸውን ስለፓትርያርክ ቴዎፍሎስ ሲጽፉ "በእኔ ፓትርያርክነት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አትደፈርም" ሲወጣበት ነው እንጂ መሬቱ ብቻውን አይደለም" በማለት ጽፈዋል።

ፕሮፌሰር ጌታቸው ቀጠል አድርገው፣ ሲናገሱ "እስመ አኮ መካን ዘይቄድሶ ለሰብእ አላ ሰብእ ይቄድሶ ለመካን፤ (ሰው ቦታን ይቀድሰዋል እንጂ ቦታ ሰውን አይቀድሰውም)" የሚለው ይህንኑ ለማስተማር ነው። አቡነ ቴዎፍሎስ ከግርማቸው እና ከጀግንነታቸው ሌላ እውቀታቸው የተትረፈረፈ ነበረ። በተገናኘን ቁጥር አዲስ ትምህርት ሳላገኝ የቀረሁበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። ግርማቸው ተራሩን ድብሽት ያደርጋል" ሲሉ በሚገባ ገልጸዋቸዋል።

ከኢጣሊያን ፋሽስት ወረራ በኋላ የአዲሲቷን ኢትዮጵያ ማንነት ለዓለም ኅብረተሰብ ለማስተዋወቅ ከጣሩት



ሰማዕቱ ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴና ከሩማንያው ፓትርያርክ ጁስቲንያ ጋር

ቅርጻቸው፣ ገጽ ሰብእናቸው፣ ርቱዕ አንደበታቸው በቆመቡት ዓውደ ምሕረት፣ በተካፈሉበት ጉባኤ ሁሉ በመንፈሳዊ ግርማ ሞገስ ተሞልተው፣ ልቀውና ጎልተው እንዲታዩ አድርጉአቸው ነበር።

ስለዚህም ተወያይተው የሚያሳምኑ፣ ተከራክረው የሚረቱ፣ የነገረ መለኮት አስተምህሮን በሚመለከት ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ፈጥነው የማያዳግም መልስ የሚሰጡ በዘመናቸው ተወዳዳሪ ያልነበራቸው አባት ነበሩ። በማለት በጀግንነት መነከሳቱን አጸጸሷ ቸው። ከዚህ በኋላ የሆነውን የማያውቅ የቤተ ክርስቲያን ሰው ያለ አይመስለኝም። ቅዱስ ፓትርያርኩም አዲስ የተሾሙት ጳጳሳትም ታሠሩ። ቅዱስ ፓትርያ ርኩ እንደ አባቶቻቸው እንደ እነ አቡነ ጴጥሮስ በጀግንነት፣ በሰማዕትነት ሕይወታቸው አለፈች።" ብለዋል። አያይዘውም "የአባታችን ሰማዕትነት ያኩራን እንጂ በሳቸው ሞት ቤተ ክርስቲያኗ አንድ ትልቅ ሰው አጥታለች። እንድን አገር ትልቅ የሚያደርገ ገው የሚደኑት ሰው ግንባር ቀደም ምሁራን መካከል አንዱ ቴዎፍሎስ ነበሩ። ገና መምህር መልዕክቱ እየተባሉ ከ1938 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ንና ሀገራቸውን በመወከል በዓለም አቀፍ መድረኮች እየተካፈሉ የኢትዮጵያን ማንነት አስተዋውቀዋል።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባዔ ሲመሠረት በጉባዔው ላይ ተገኝተው በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስም ቻርተሩን በመፈረም መሥራች

ፓትርያርክ... ከገጽ ፳፰ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org

# ብሂለ ቴዎፍሎስ

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አንድ ነገር እንዲብራራላቸው ሲፈልጉ "እስ እንዴት?" ማለት ልማዳቸው ነበር። አስደንጋጭ የሆነ ድንገተኛ ነገር ሲያጋጥማቸው ደግሞ "የሥላሴ ባሪያ" ይላሉ። ይህ ለእሳቸው "ዘራፍ የጠቅል አሽከር" ብሎ እንደመፎከር ነው። የሚታወሱባቸው ሌሎች በርካታ አባባሎችም አሏቸው። እነዚህ አባባሎች በአንድ በኩል ትምህርታዊ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ ሰውን ሳያስቀይሙ ቅሬታን መግለጫዎች ናቸው። የሚከተሉትን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡ እነዚህ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ አባባሎች ወደፊት ከሚታተመው መጽሐፍ የተወሰዱ ናቸው።

## የታየው ነገር ሁሉ አይነገርም

ከዕለታት አንድ ቀን አቡነ ቴዎፍሎስ ካሳደጓቸው ወጣቶች መካከል አንዱ የሆነው አቶ መሐሪ አምባው ከትምህርት ቤት መልስ አራት ኪሎ መኖሪያቸው ወደሆነው ወደ አቡነ ቴዎፍሎስ ቤት ሲመጣ ግቢው ጭር ብሎ ያገኘዋል። ለወትሮው አቡነ ቴዎፍሎስ እቤት ካሉ በግቢው ሞቅ ሞቅ ይላል፤ ሰው ይተረማመሳል። ዛሬ ግን ግቢው ጭር ስላለ መሐሪ አቡነ ቴዎፍሎስ እቤት የሉም ብሎ ደምድሟል። ከዚህም በላይ በአብዛኛው እቤት ስለመኖራቸው ምልክት የሆነችው ዶጅ መኪናቸው ግቢው ውስጥ አልነበረችም። ስለዚህም ግቢውን አቋርጦ አቡነ ቴዎፍሎስ ከሚኖሩበት ከዋናው ቤት ደርሶ ሳያንኳኳ የሳሎኑን በር በርግዶ ሲገባ የማይታመን ነገር ይመለከታል። ሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ከአቡነ ቴዎፍሎስ እግር ላይ ተጠምጥመው ተነሥ አልነሣም ሁለቱ ግብ ግብ ገጥመዋል። መሐሪ በዚህ ትእይንት ይደናገጥና የሳሎኑን በር ግጥም አድርጎ ዘግቶ ወደኋላው ይመለሳል።

አባ ሀብተ ማርያም ጉዳያቸውን ጨርሰው እንደወጡ አቡነ ቴዎፍሎስ የጥሪ ደወል ያስማሉ። መሐሪም ሲፈራ ሲቸር በሩን ከፍቶ ይገባል። "አንተ! አንተ የማትረባ ሞኝ! በር እንደዚህ ገልብጠህ ነው የምትገባው? አሉት አቡነ ቴዎፍሎስ። የቤት ልጆችን ሲቆጡ እንዲሁ ነበር።

"መኪናዋ ስለሌለች አባታችን የሉም ብዬ ነው" አለ መሐሪ እየተቅለሰለሰ።

"ብኖር ባልኖር በር እንደዚህ ገልብጠህ ነው የምትገባው?...ለማ፤ ለመሆኑ ምን አየህ?"

"ምንም አላየሁም" አለ መሐሪ እየተቅለሰለሰ።

"ትክክል ነህ፤ አሁን ጥሩ ነገር ተናገርክ። የታየው ነገር ሁሉ አይነገርም... ግባ... በል ሂድ አሁን" አሉት።

አባ ሀብተ ማርያም በአቡነ ቴዎፍሎስ እግር ላይ ተጠምጥመው የተማጸኗቸው አማልዱኝ ኃማለት እንደሆነ የታወቀው ከጊዜ በኋላ ነው። በደህናው ጊዜ አቡነ ቴዎፍሎስን ለዓይናቸው እንኳን የሚጠሏቸው ሰው ነበሩ። መስሎቻቸውንም እያሰባሰቡ ያሳድሙባቸው ነበር ይባላል። እንደ ሌሎች ሰዎች እንኳን ከቤታቸው መሄድ ኃጢአት መስሎ ይታያቸው ነበር። የጭንቅ ሰዓት ሲመጣ ግን የሚጠሏቸውን አቡነ ቴዎፍሎስን መለማመጡን አማራጭ የሌለው መፍትሔ ሆኖ አገኙት።

አባ ሀብተ ማርያም በምር እንደሚጠሏቸው ቢያውቁም አቡነ ቴዎፍሎስ ሆደ ሰፊ ስለነበሩ ችግራቸውን ተቀበሉት። አብልጠው የሚያስቡት ለግለሰብ ሳይሆን ለቤተ ክርስቲያን ክብር ስለነበረ፤ "የቤተ ክርስቲያን ችግር አደባባይ መውጣት የለበትም። ካህናት ቢያጠፉ እንኳን ጉዳዩ ታይቶ እርምጃ መወሰድ ያለበት በቤተ ክርስቲያን ደንብ መሠረት ነው። ስለዚህ ባሊቀ ሥልጣናት ላይ የቀረበው ክስ የቤተ ክርስቲያን ችግር ስለሆነ ወደ እኛው እንዲመለስ ይደረግልን" በማለት ተመሥርቶባቸው የነበረው ክስ እንዲቋረጥ እንዳደረጉ በወቅቱ በሰፊው ተነግሯል።✦

## ሰው ወደታች እንጂ ወደላይ ያድጠዋል?

አቡነ ቴዎፍሎስ የፓትርያርክ የአቡነ ባስልዮስ እንደራሴ ሆነው ይሠሩ በነበረበት ጊዜ አንድ ሰውየ ሊያጋግራቸው ወደ ቢሮአቸው ይመጣል። ሰውየው በአቡነ ባስልዮስ ላይ ቅሬታ ስለነበረው ይኸንኑም ቅሬታውን ለአቡነ ቴዎፍሎስ ሲገልጽ ኃይለ ቃል እየተጠቀመ ነበር። አቡነ ቴዎፍሎስ ግን በአነጋገሩ ስላልተደሰቱ ሰውየው ተናግሮ ሳይጨርስ፤ "ተው እስ፤ እንዴት እንዲህ ትናገራለህ? አንተ ጤና የለህም እንዴ? ቅዱስ አባታችንን ነው እንዲህ የምትላቸው?" በማለት ይቆጡታል።

ሰውየው ከአቡነ ቴዎፍሎስ የዚህ ዓይነቱን አነጋገር አልጠበቀ ኖሮ ደንግጦ፤ "አባታችን ይቅርታ ያድርጉልኝ። እንዲህ ማለት እንኳን አልነበረብኝም። እንዲያው አድጦኝ ነው" ይላቸዋል።

እሳቸውም መልሰው፤ "ታዲያ ሰው ባይሆን ወደታች እንጂ ወደላይ ያድጠዋል?" አሉት ይባላል።

## በሰንበት አይታረምም ብለህ ነው?

አቡነ ቴዎፍሎስ የዕረፍት ጊዜያቸውን ጎፋ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ባስተከሉት የባሕር ዛፍ ተክል መካከል መዘዋወር ይወዱ ነበር። ሰዎችም ካዩዋቸው ይከተሏቸዋል። እንደተለመደው አንድ እሁድ ቀን በባሕር ዛፎቹ መካከል በመንቀሳቀስ ላይ ሳሉ ከሚከተሏቸው ሰዎች መካከል የቅኔ ሊቅ የሆኑት የኔታ ይኩኖ አምላክ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ቅኔ ሲሰጡ ከአንድ ቦታ ላይ ዜማ ይሰብርባቸዋል። በዚህን ጊዜ አቡነ ቴዎፍሎስ፤ "እስቲ ይመልሱት!" ይሏቸዋል።

የኔታ ችግሩ ከምን ላይ እንደሆነ ስላልገባቸው ያንኑ ስሕተት ደገሙት። አቡነ ቴዎፍሎስ ወደፊት እየተራመዱ አሁንም፤ "እስቲ እንደገና ይበሉት!" አሏቸው። የኔታ ይኩኖ አሁን ግራ ገብቷቸው ዝም አሉ። በዚህ ጊዜ አቡነ ቴዎፍሎስ ወደኋላ ዞረው በሙቅም ይከተሏቸው ከነበሩት ሰዎች መካከል አንዱን ካህን በስም ጠርተው "ስሕተት የለም ነው የምትለው?" አሉት።

ካህኑ ስሕተት መኖሩን ተገንዝቧል። ይሁን እንጂ የኔታ ይኩኖን

ብሂለ...ወደ ገጽ ፳፬ የዞረ



www.ethiopianorthodox.org



# ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ለትምህርት መስፋፋት ያበረከቱት አስተዋጽኦ

### መግቢያ

ትምህርት አዕምሮንና ሥነ ባሕርይን የማነፅ፤ ዕውቀትንና ጥበብን የማሳደግ የማበልጸግ፤ ሂደት ነው። የሰው ልጅ በዚህ ሂደት ማለፉ ለራሱ ሕይወት ብቻ ሳይሆን ለሀገር ዕድገትና ሥልጣኔ እጅግ አስፈላጊ በመሆኑ በዘመናችን ከሙዐለ ሕጻናት ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ያሉ የትምህርት ተቋማት ተስፋፍተው ይገኛሉ። ዛሬ ሙዓለ ሕፃናት የምንለው በቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓተ ትምህርት ንባብ ቤት ይባላል። ከንባብ ቤት እስከ ትርጓሜ መጻሕፍት ቤት የነበረውና አሁንም ያለው ት/ቤት የተጀመረውና ሲካሄድ የኖረው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ነው። ልጆቻቸው ለዚህች ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንዲሆኑ ወይም ማንበብና መጻፍ እንዲማሩ የሚፈልጉ ወላጆች መጀመሪያ የሚያስገቧቸው ከንባብ ቤት ነው። የዚህ ጽሑፍ ባለቤት የሆኑት ሰማዕቱ ቴዎፍሎስም ለሹመት፤ ለሽልማት ከበቁ በኋላ በሥልጣን ላይ በቆዩባቸው ዓመታት ሲያስፋፉት የኖሩትን ትምህርት ራሳቸው መቅሰም የጀመሩት ባደጉበትና በታላቁ ደብረ ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን የንባብ ቤት ነው።

### ያስፋፉትን ትምህርት እንዴት እንደተማሩት፤

በልጅነት ስማቸው መልዕክቱ ይባሉ የነበሩት ታላቁ አባት መጀመሪያ የንባብ ቤቱን ትምህርት ተጥሉም ጸዋትወ ዜማን ካጠናቀቁ በኋላ ቅኔ ትምህርት ቤት ገብተው ይህንኑ ትምህርት ከነአገባቡ ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል። መልዕክቱ ቅኔ ቤት ሳሉ በዚሁ ትምህርት ጥልቅ ዕውቀት በመቅሰማቸው የእርሳቸውን ቅኔ ለመስማት ይጓጉ የነበሩ ጓደኞቻቸው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ቅኔ በሚቀኙበት ጊዜ መልዕክቱ ካሉና ትክ ብለው ከተመለከቷቸው በድንጋጤ ቅኔው ስለሚጠፋባቸው "መልዕክቱ እባክህ አትመልከተኝ" ይሏቸው ነበር ይባላል።

ተማሪ መልዕክቱ በትምህርታቸው ለመግፋት ብርቱ ፍላጎት ስለነበራቸው በ1920 ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሳለ በትርጓሜ መጻሕፍት ታዋቂ የነበሩት ንቡረ ዕድ ሐዲስ ተክሌ (በኋላ ብፁዕ አቡነ በዮሐንስ) መሆናቸውን ስለ ሰሙ እርሳቸው ወደ ነበሩበት ወደ አዲስ ዓለም ቤተ ክርስቲያን በመሄድ የሐዲሳትንና የፍትሐ ነገሥትን ትርጓሜ ጠንቅቀው በማጥናት በእነዚህ የትምህርት ዓይነቶች መምህር መሆን ብቻ ሳይሆን በሐዲሳት ምስጉን ሰባኬ ወንጌል፤ በሕገ ቤተክርስቲያን ደግሞ ተጠቃሽ ለመሆን በቅተዋል። ይህም ሊቅነታቸው በበለጠ ሁኔታ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ስለሳባቸው በ1930 ዓ.ም በደብረ ሊባኖስ ገዳም ሥርዓተ ምንኩስናን ፈጽመው አባ መልዕክቱ ተብለዋል።

ዘመናዊ ትምህርትን በተመለከተም ባሊያን ድል ሆኖ ከሀገራችን ከጠጣና በዒ. ኃይለሥላሴ ከስደት ከተመለሱ በኋላ አባ መልዕክቱን ለማሳየት በቅተዋል ስለሆነም ለዘመኑ ተስማሚና ተፈላጊ ካህን ያደረጋቸው ይህ ትምህርት ቀደም ሲል ከቀሰሙት የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ጋር ተዳምሮ ነው።



በዘመኑ አሉ ከሚባሉ 20 ሊቃውንት እንደ አንዱ አድርገው በመምረጥ በገነተ ልዑል ቤተ መንግሥት በከፈቱት ዘመናዊ ትምህርት ቤት ያስገቧቸዋል እርሳቸውም በዚህ ወርቃማ ዕድል በመጠቀም ትምህርቱን በንቃት ስለተከታተሉ በተለይ እንግሊዝኛ ቋንቋን ከሌሎች ጓደኞቻቸው በላቀ ሁኔታ ለማጥናትና ችሎታቸውን

### በሰጡት አመራር ትምህርትን እንዴት እንዳስፋፉ

በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ት/ት ቤት መማር ለአመራር፤ መማር ለማመሥጠር ነውና ትምህርት ለመሪነት ምሥጢራትን አፍታቶ ለማስረዳት ያስችላል። ከዚህ አኳያ አባ መልዕክቱ በ1935 ዓ.ም በመካነ ሥላሴ ገዳም መምህር ተብለው ለአመራር ሲበቁ ከአባልነት ወደ መምህርነት ተሸጋገሩ። በዚህ ጊዜ መምህር መልዕክቱ ባላቸው የትምህርት ችሎታና አስተዋይነት የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስቴር የቦርድ አባል ሆነው ተመረጡ። ይህ ቦርድ ትምህርትን በየዘርፉ ለማስፋፋት ባለው ዓላማ ሲሠራ መንፈሳዊውን ከዘመናዊ ትምህርት ጋር አቀናጅቶ ማስተማር የሚችል ትምህርት ቤት አስፈላጊውን ኮሚቴ አቋቁመው በማስጠናት ባለ ሰባት

ሰማዕቱ....ወደ ገጽ ፳፮ ዞሯል

**ብሂለ**... ከገጽ ፳፪ የዞረ

የሚያህል ሊቅ ለማሪያም ከበደው። ስለዚህም እንገቱን አቀርቅሮ ዝም ብሎ ቆመ። በዚህን ጊዜ አቡነ ቴዎፍሎስ ፈገግ ብለው፤ "በል ተወው፤ በሰንበት አይታረምም ብለህ ነው?" አሉት ይባላል።♦

## ማን ሊጎዳ?

አንድ የውጪ አገር መንግሥት መሪ ኢትዮጵያን ለመጎብኘት መጥቶ በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል እሁድ በሚደረገው ሥነ ሥርዓት ላይ መገኘት እፈልጋለሁ ስላለ ፕሮግራም ተይዞለታል። ነገር ግን ፕሮግራሙ የተዘጋጀው በሁለት በኩል ነበር። በአንድ በኩል በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ትእዛዝ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ተዘጋጅቷል። በሌላ በኩል ደግሞ የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳዳሪ በነበሩት በሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም በኩል ተዘጋጅቷል።

እንግዳው ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ረጅም ሰዓት እንዳይቆይም ሥነ ሥርዓቱ ቀደም ብሎ እንዲጀመር ለሊቀ ሥልጣናት አባ ሀብተ ማርያም ከቤተ መንግሥት ትእዛዝ ተላልፎላቸዋል። በዚሁ መሠረት ሊቀ ሥልጣናት ሥነ ሥርዓቱ ቀደም ብሎው አስጀምረዋል። አቡነ ቴዎፍሎስ ለሊቀ ሥልጣናት ስለተሰጠው ትእዛዝ የሚያውቁት ነገር አልነበረም። ከንጉሡ ቀደም ብለው በቤተ ክርስቲያን መገኘት ስለነበረባቸው ወደ ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሲገቡ ሥነ ሥርዓቱ መገባደዱን ይገነዘባሉ። በዚህ ቅር ተሰኝተው ጃንሆይ ከእንግዳው ጋር እስኪመጡ ድረስ ሥነ ሥርዓቱ እንዲቆም ያዛሉ።

ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ንጉሡ ከእንግዳቸው ጋር ደረሱ። ከዚያም ሥነ ሥርዓቱ ቀጥሎ እስከሚጠናቀቅ ቆመው አስቀደሱ። ሥነ ሥርዓቱ ከተጠናቀቀ በኋላ አቡነ ቴዎፍሎስ ንጉሡንና እንግዳውን ለመሸኘት ተከትለው ወጡ። ንጉሡ ወደ መኪናቸው እየሄዱ ከአቡነ ቴዎፍሎስ ጋር ይነጋገሩ ነበር።

"እንግዳውን ይሰለቸዋል ብለን ሥነ ሥርዓቱ አጠር እንዲል አዘን ነበር። ለምን ተራዘመ?" አሉ ንጉሡ።

"ግርማዊ ጃንሆይ፤ ሥነ ሥርዓቱን እኮ ያስረዘምነው እኛ አይደለንም። ያስረዘመው ሥነ ሥርዓቱ ነው" አሉ አቡነ ቴዎፍሎስ።

ጃንሆይ በአቡነ ቴዎፍሎስም መልስ አልተደሰቱም። ወደ መኪናቸው ከገቡ በኋላ መስታወቱን ዝቅ አድርገው፤ "ብፁዕ አባታችን፤ እንግዳ ህ እንዲህ ከሆነ እዚህ ቤተ ክርስቲያን ተመልሰን አንመጣም" አሉ።

አቡነ ቴዎፍሎስም፤ "ግርማዊ ጃንሆይ፤ ማን ሊጎዳ?" በማለት መለሱላቸው ይባላል።♦

**ያን ጊዜም እኛው ነበርን፤ አሁንም እኛው ነን**

አንድ ጊዜ ጃንሆይ ዐጼ ኃይለ ሥላሴ የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅን እንዲጎበኙላቸው አቡነ ቴዎፍሎስ ይጋብዟቸዋል። በጉብኝቱ ወቅት ሊቃውንት ለጃንሆይ ቅኔ እንዲያበረክቱ ፕሮግራም ተይዟል። ፕሮግራሙን የሚመሩት የኮሌጁ አስተዳዳሪ የነበሩት መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ ናቸው። መልአከ ሰላም ቅኔ የሚያበረክቱትን ሰዎች ተራ አስይዘዋል። ቅኔ ከሚያበረክቱት ሰዎች መካከል አንዱ በኮሌጁ ውስጥ በወቅቱ ተማሪ የነበሩት አቶ ዜና ማርቆስ እንዳለው ናቸው።

በዚሁ መሠረት ሰዓቱ ሲደርስ የተሰየሙ ሰዎች በተራቸው ቅደም ተከተል መሠረት ለጃንሆይ ቅኔ ሲያበረክቱ ቆይተው የአቶ ዜና ማርቆስ ተራ ሲደርስ መልአከ ሰላም ሳሙኤል፤ "በቃ፤ በቃ" ብለው አስቆሙ። አቶ ዜና ማርቆስ ይህን የመልአከ ሰላም ሳሙኤልን ድርጊት ከአድልዎ ቆጥረውት ቅሬታ ስለተሰማቸው ጃንሆይ ጉብኝታቸውን ጨርሰው ከሄዱ በኋላ፤ "አባታችን፤ ይኸውና መልአከ ሰላም እኔ ቅኔ እንዳልሰጥ ከለከሉኝ" በማለት ለአቡነ ቴዎፍሎስ አቤቱታ አቀረቡ።

አቡነ ቴዎፍሎስ አቶ ዜና ማርቆስን በጎን ቁልቁል እየተመለከቷቸው "እኮ'በል አምጣው! ያን ጊዜም እኛ ነበርን፤ አሁንም እኛው ነን" አሉ ይባላል።♦

## ከተማረ አይሳደብም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ የተማረ ሰው ይወዱ ነበር። ስለሆነም በርካታ የቤተ ክርስቲያን ልጆች ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጪ አገር እየሄዱ እንዲማሩ አድርገዋል። አንድ ጊዜ ተማሪዎች የነፃ ትምህርት ዕድል አግኝተው ወደ ውጪ ሲላኩ እሳቸውን የማይወድ፤ እየዞረ ስማቸውን የሚያጠፋና የሚሳደብ አንድ ተማሪም ዕድሉን አግኝቶ ወደ ውጪ አገር ለመሄድ ተፍ ተፍ ይላል። ይህ ተማሪ ለአቡነ ቴዎፍሎስ በጎ ነገር የማያስብ መሆኑን የሚያውቁ ተቆርቋሪ ሰዎች ይቀርቧቸውና የተማሪውን ስም እየጠቀሱ፦

"እንዴት እሱን ወደ ውጪ አገር ልከው ያስተምሩታል?" ይሏቸዋል።

"እኮ እንዴት? ለምንድን ነው የማይሄደው?" በማለት ይጠይቃሉ።

"እርሱ እኮ ለእርስዎ የማይተኛ፤ እየዞረ ስምዎን የሚያጠፋ፤ የሚሳደብ ነው?" ይሏቸዋል።

"የሚሳደበው እኮ ስላልተማረ ነው። ይሂድና ይማር፤ ከተማረ አይሳደብም" አሉ ይባላል።♦

በታምራት አበራ

**ትምህርተ**... ከገጽ ፲ የዞረ

"እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ ነው" /ዕብ.11፥1 ተብሎ እንደተጻፈ. እኛ አምነን እግዚአብሔርን ተስፋ እናደርጋለን።

ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በግሪክ አቴና ከተማ ተገኝተው ሃይማኖትን በተመለከተ እንዲህ ብለው ነበር።

"እኛ የሰው ልጆች እምነታችን በሚቀዘቅዝበት ጊዜ እግዚአብሔርን ማሳዘናችን አያጠራጥርም እግዚአብሔርን በመርሳት ከእምነት ውጭ የሆነ ሰው የሕይወት ሰላምና የመንፈስ ጸጥታ አይኖረውም። ውጤቱም ከንቱና ተስፋ ቢስነት ሲሆን እግዚአብሔርን የሚያምን ሰው ግን በዚህ ዓለም በሚኖርበት ጊዜ የሕይወት ሰላምና የመንፈስ ጸጥታ ከማግኘቱም በላይ በወዲያኛው ዓለም የዘለዓለም ሕይወትን ይወርሳል።"

እኛም ይህን አባታዊና መንፈሳዊ መልዕክት በመከተል እግዚአብሔርን ለምድራዊም ሆነ ለሰማያዊ ሕይወታችን ተስፋ በማድረግ እግዚአብሔር የለም ወይም መኖሩም አለመኖሩም አይታወቅም የሚሉትንም አጥብቀን እንቃወማለን፤ ከእነርሱም እንርቃለን። እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።♦

መምህር አእመረ አሸብር
በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ የሊቃውንት ጉባኤ አባል





# የአደባባዩ ርክክብ

እንጋፋዋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንደሚታወቀው ከሥልጣኔ በፊት የሥልጣኔው ፈር ቀዳጅ ሆና በሥነ ጽሑፍ፤ በትምህርት፤ በሥነ ሥዕል፤ በኪነ ሕንፃና በመሳሰሉት ለአንድ ሀገር ዕድገት ወሳኝ ሚና ባላቸው ቁም ነገሮች ሁሉ የላቀ አስተዋጽኦ ስታበረክት ቆይታለች።


ለታላቋ ሀገራችን ለኢትዮጵያም የሕዝቡን የአኗኗር ባሕል፤ የነበረውን ቁስና የነገሥታቱን ቅርስ የከበሩ ታላላቅ ሕንፃዎችን ሳይቀር ለዚህ ትውልድ ያበረከተች ቤተ ክርስቲያናችን መሆኗ ዛሬም ያለነው አገልጋዮችና የእምነቱ ተከታዮች ያለ እረፍት እንድንሠራና ከመንግሥት ጐን ሆነን ሀገራችንን እንድናለማ ቀስቃሽና አነሣሽ ሆኖ ያስገድደናል።

በመሆኑም የሀገራችን መንግሥት ለልማት በሚታትትበት የታላቋ ሀገራችን የኢትዮጵያ ሕዝቦችም ጠላታቸው ድኽነትን ለማሸነፍ በአንድነት ለልማት በዘመቱበት በዚህ መልካምና ታሪካዊ ወቅት ከመንግሥታችን ጐን ሆነን ለማልማትና በአካባቢያችን ያለውን አደባባይ ውበት ለመስጠት በባለቤትነት በመረከባችን ታላቅ ደስታ ይሰማናል።

በአለፈው አረመኔያዊ አገዛዝና ሥርዓተ መንግሥት በግፍ በተገደሉት ኢትዮጵያዊ አባት በ2ኛው ፓትርያርክ በሰማዕቱ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በመሆኑ አሁንም ያሉት 5ኛው ፓትርያርካችን ዓለማቀፋዊና ቆራጥ ልማታዊ አባት መሆናቸው የነበረውን ልማታዊ መንፈስ ለማስቀጠል አንዳችም ችግር እንደማይገጥመን በተለይም በቅዱስ ፓትርያርካችን የተጠየቀው የስም፡ የሐውልተ ስም ጥያቄ ፈጣን መልስ ያላቸው የሰንበት ት/ቤት ልጆቻችንና እና ቀና አመለካከት ያለውን የአካባቢ ኅብረተሰብ ይዘን ቅን አመለካከት ካላቸው የቀበሌያችን አመራሮች ጋር በመመካከር ልማታዊ ከሆነው መንግሥታችን ጐን በመሆን የላቀ ውጤት እንደምናስመዘግብና በአለው የሀገራችን የቱሪዝም ሀብት ላይ ተጨማሪ የሚሆን፤ ለቀጣዩ ትውልድ የሚተላለፍ፤ የሚስብና ውበት ያለው ሀብት ሠርተን እንደምናበረክት ላረጋግጥ እወዳለሁ።



በአደባባዩ ርክክብ ወቅት ንግግር ሲያደርጉ



በመጨረሻም ይህን ሐሳብ ያመነጩትን የአካባቢ ወጣቶች በየትኛውም የልማት ጥያቄ ቀና ትብብርና መልስ የሚሰጡንን የክፍለ ከተማውን የሥራ ኃላፊዎች፤ የቀበሌውን ሥራ አስፈጻሚ፤ የቀበሌውን ሥራ አስኪያጅ እንዲሁም የአመራር አካላት አደባባዩን ለማልማት በውሳኔው ላይ ያለ ማመንታት በአንድ ድምፅ በአንድነት ለልማት የተነሡትን የካቴድራሉን የሰበካ ጉባኤ አባላት በካቴድራሉና በእምነቱ ተከታዮች ስም ከልብ አመሰግናለሁ።

ሐሳባችንን ለማሳካት ሀገራችንንም ለማልማት ሁሉ የሚቻለው እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።♦

እንጋፋው ካቴድራላችንም የተመሠረተው በአርቆ አሳቢውና በሀገር ወዳዱ፤ በሀገር ወዳድነታቸውም እንደሚያገኝ/እንደሚሰጠው/ በመተማመን ሐሳቡን ያመነጩትን የአካባቢ ወጣቶቻችንን፤ በቴ አትም

መልአከ ፀሐይ
አባ ኃይለ መለኮት ይሄይስ
የካቴድራሉ ዋና አስተዳዳሪ
ሚያዝያ 17/2002 ዓ.ም.



www.ethiopianorthodox.org

**ሰማዕቱ**... ከገጽ ፳፫ የዞረ

ነጥብ የጥናት ሀሳብ ለንጉሡ ነገሥቱ አቀረቡ። ንጉሡም የቀረበላቸውን ጥናት ከተመ ለከቱ በኋላ ትምህርት ቤቱ በአስቸ ኳይ እንዲቋቋም ለትምህርት ሚኒስቴር ትእዛዝ አስተላለፉ።

በትእዛዙ መሠረት ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ እና ዘመናዊ ትምህርት ቤት ሲቋቋም መምህር መልዕክቱ የበላይ አስተዳዳሪና የቦርድ ሰብሳቢ በመሆን በሰጡት የላቀ አመራር ትምህርት ቤቱ ከአንደኛ ደረጃ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ከሁለተኛ ደረጃ ወደ ኮሌጅነት ከፍ እንዲል አድርገዋል። በኋላም የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሲመሠረት የዩኒቨርሲቲው አካል በመሆን በሥነ መለኮት ትምህርት የቲዎሎጂ ዲግሪ እንዲሰጥ አስችለውታል። ከመምህርነት ወደ ሊቀ ሥልጣናትነት፣ ከሊቀ ሥልጣናትነት ወደ ጳጳስነት ወደ ፓትርያርክነት በተሸጋገሩባቸው ዓመታት ሁሉ ለዚህ ኮሌጅ የጣሉት መሠረትና የሰጡት ምሁራዊ አመራር ኮሌጁን በየጊዜው እያሳደገውና እያስፋው መጥቷል።

ይህ ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ፀረ ሃይማኖት አቋም በነበረው በደርግ መንግሥት ዘመን ለ17 ዓመታት ያህል ተዘግቶ ከቆየ በኋላ የሰማዕቱ የመንፈስ ቅዱስ ልጅ የሆኑት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፣ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ም/ቤት ፕሬዚዳንትና የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት ባደረጉት ብርቱ ጥረት እንደገና ተከፍቶ በአሁኑ ጊዜ በርካታ ወጣቶችን በዲግሪና በዲፕሎማ እያስመረቀ ለትምህርተ ወንጌልና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በማሠማራት ላይ ይገኛል።

## በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ

ከሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር ታሪክ እንደምንረዳው በ1951 እና ከዚያም በፊት ባሉት ዓመታት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የነበሩ የውጭ ሀገራት መምህራን ተማሪዎች የእነርሱን ሃይማኖት እንዲከተሉ የሚያደርግ ዘዴ ቀይሰው መንቀሳቀስ ሲጀምሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ተከታዮች የሆኑ ተማሪዎች የመምህራኑን እምነት እስለ ዋጭ ተንኮል መቋቋም እንዲችሉ ስለ ኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖታቸው የሚያስ ተምራቸው መምህር እንዲመደብላቸው ለቤተክህነት ጥያቄ ሲያቀርቡ በዘመኑ ምስጉን ሰባኬ ወንጌል የነበሩት ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በወቅቱ የሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ቢሆኑም በእንደራሴነታቸው ከፓትርያርኩ ከብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ተጥለው የቤተ ክህነት መሪ ስለነበሩ ከተማሪ ዎች ለቀረበው ጥያቄ አፋጣኝ መልስ በመስጠት በየሳምንቱ ዓርብ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አዳራሽ እየተገኙ የሃይማኖት ትምህርት በመ ስጠት ኦርቶዶክሳውያኑን ተማሪዎች በእምነታቸው እንዲጸኑ ከማድረጋቸው ም ሌላ በዚህ መነሻነት ሃይማኖተ አበው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር በ1951 ዓ.ም በግንቦት ወር ተመ ሥርቶ ለወጣቱ ትውልድ ትምህርተ ሃይማኖት ሲሰጥ ኖሯል። ይህም ታሪካዊ ድርጊት ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ በቤተክርስቲያን አካባቢ ብቻ ሳይሆን በመንግሥታውያን የትምህርት ተቋማት ሳይቀር ትምህርትን እንዳስፋፉ አጉልቶ ያሳያል።

## በሐረርጌ ሀገረ ስብከት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ትምህርትን ያስፋፉበት ሌላው ቦታ የሐረርጌ ሀገረ ስብከት ነው። በዚህ ሀገረ ስብከት በጵጵስናና በሊቀ ጵጵስና ደረጃ ባገለገሉባቸው ዓመታት በሐረር ከተማ በልዑል ራስ መኮንን ስም የሚጠራ አንደኛ ደረጃ መንፈሳዊና ዘመናዊ አዳሪ ት/ቤት አቋቁመው ከጠቅላይ ቤተ ክህነትና ሀገረ ስብከቱ በተመደበ በጀት እየተዳደረ ከዚያው አካባቢ ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም አህጉረ ስብከት መንፈሳዊና ዘመናዊ ትምህርት ፈልገው የመጡ ወጣቶችን እንዲ ቀበልና እንዲያስተምር በማድረጋቸው ዛሬ አገርንና ቤተ ክርስቲያንን በልዩ ልዩ የሥራ መስክ ለሚያገለግሉ በርካታ ምሁራን ካህናትና ሊቃውንት መፍለቂያ ሊሆን ችሏል።

እንደዚሁም በዚሁ ሀገረ ስብከት በቁልቢ ቅዱስ ገብርኤል ገዳም ሌላ አንደኛ ደረጃ ት/ቤት እንዲቋቋም አስደርገው ብዙኃን የአካባቢው ኅብረ ተሰብ ልጆች እንዲማሩበትና ከድንቁርና እንዲላቀቁ አስችለዋቸዋል። እነዚህ ሁለት ት/ቤቶች በደርግ ዘመነ መንግሥት ቢወረሱም ታላቁ አባት በዘመናቸው ትምህርትን ለማስፋፋት ያደረጉአቸውን በጎ ጥረቶች አጉልተው የሚያሳዩ ናቸው።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በሐረርጌ ሀገረ ስብከት ትምህርትን ያስፋፉት ት/ቤቶችን በመክፈት ብቻ አይደለም። ከቦታ ወደ ቦታ በመንቀሳቀስና የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማርም ብዙኃንን ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከገቢረ ኃጢአት ወደ ገቢረ ጽድቅ በመመለስ እውነተኛውን ትምህርት አስፋፍተዋል። ለምሳሌ ያህል በ1949 ዓ.ም ያን ጊዜ በሐረርጌ ሀገረ ስብከት ሥር በነበረው በባሌ ጠቅላይ ግዛት ወረዳዎች እና አውራጃዎች እየተዘዋወሩ በማስተማር 24,000 የእዋማንና የልዩ ልዩ እምነት ተከታዮችን አሳምነው በማጥመቅ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተከታዮች አድርገዋቸዋል።

## ብዙኃን ወጣቶችን ወደ ውጭ በመላክ

ሰማዕቱ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ለትምህርት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያደረጉበት ሌላው መስክ የውጭ ሃገር እስኮላርሺፕ ወይንም ነፃ የትምህርት ዕድልን በማስ ገኘት አያሌ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ወጣቶችን ወደ ውጭ እየላኩ እን ዲማሩ ማድረጋቸው ነው። ይ ህንን ዕድል ሊያስገኙ የቻሉት በውጭ ቋንቋ ችሎታቸው በልዩ ልዩ የዓለም ክርስቲያናውያን ጉባኤያት ላይ በመገ ኘት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በማስተዋወቃ ቸው ነው።

ለምሳሌ ከታሪካቸው እንደምንረዳው በ1938 ዓ.ም በእንግሊዝ ሃገር በበርሚንገሃም ከተማ በተካሄደው የሰንበት ት/ቤቶች ጉባኤ ላይ፣ በ1940 ዓ.ም በዓለም አብያተ ክርቲያናት ምክር ቤት በሆላንድ አመስተርዳም ከተማ ውስጥ ሲቋቋም፣ በ1944 ዓ.ም ቅዱስ ጳውሎስ ወደ ግሪክ ሃገር የገባበት 19 መቶኛ ዓመት በዚያው በግሪክ ሲከበር በ1954 ዓ.ም በህንድ ኒውደልሂ፣ በ1960 ዓ.ም በስዊድን ኢ ኡፕሳላ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባኤ ሲካሄድ የኢትዮጵያን መልክዕክተኞች በመምራት ተገኝተዋል።

በእነዚህ ጉባኤያት ከተገኙ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጋር ባደረጉት ትውውቅ ለቤተ ክርስቲያና ችን አገልጋይ ወጣቶች የነፃ ትምህርት ዕድል በመጠየቅ እና በማግኘት በርካታ ወጣቶችን ወደ ግብፅ፣ ግሪክ፣ ሩሲያ፣ አውሮፓ፣ አሜሪካና እስያ በመላክ በከፍተኛ የሥነ መለኮት፣ የታሪክ፣ የቋንቋ፣ የማኅበራዊ ሳይንስ ወዘተ የትምህርት ዓይነቶች በቢ. ኤ፣ በማስትሬት እና በዶክትሬት ዲግሪዎች ደረጃ እንዲሰለጥኑ በማስቻላቸው ወደ እናት ሃገራቸው ሲመለሱ በክህነት ብቻ ሳይሆን በመንግሥታዊ አስተተዳደር ሥራ እየተመደቡ ውጤታማ አገልግሎት ስጥተዋል።

ከነዚህም አንዱና ዋናው ከላይ ከነሙሉ ማዕረጋቸው የተጠቀሱት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ሲሆኑ ከሌሎችም መካከል ጥቂቶችን ብንጠቅስ ወደ ግብፅ ከተላኩት ውስጥ

**ሰማዕቱ**....ወደ ገጽ ፴ ዞሯል





**በሕይወት**... ከገጽ ፲፰ የዞረ

ጊዜ በማኅተም በመዝጋት የበላይ ነት አለኝ የምትለው ግብፅ እት ሚን እንድታውቅ ለማድረግ ነው ሲሉ ዘርዝረዋል። /ዓለማየሁ ዓለምነት ገጽ 85/

ምንም እንኳን የኃይለ ሥላሴ መንግሥት ያልደፈረውን ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርሲያን ከግብፅ የበላይነት ነፃ ለማድረግ ለዓመታት በነበረው እልክ አስጨራሽ ክርክር ስላሸነፉ ግብጾች ቢጠሏቸውም ፓትር ያርክ ሺኖዳ በቴዎፍሎስ በግፍ መታ ሰርና ጳኛ /ፍትሕ/ መጥፋት አዘው ትረው እንደሥሁ ነበር። ያም ሆኖ ቴዎፍሎስ ለግብፅ ቤተ ክርስቲያን ጭምር መከታም ስለ ነበሩ ፓትር ያርክ ሺኖዳ በትርቡ ወደ ኢትዮጵያ በመጡበት ጊዜ መጀመሪያ የጎበኙት የፓትርያርክ ቴዎፍሎስን መቃብር እንደነበር ይታወሳል።

## ታዲያ ቴዎፍሎስ እስከ ዛሬ በሕይወት ቢኖሩ ኖሮ!

*የእኃት አብያተ ክርስቲያና ትን መቀራረብ አጠናክረው የኢ ትዮጵያ ቤተክርስቲያን ማዕከል ያደርጉ ነበር። በተለያዩ ምክንያ ቶች በእኃት አብያተ ክርስቲያናት ላይ የሚደርሰውን ችግር በአንድ ነት በመቋቋም የተዋሕዶ እምነት በዓለም ሁሉ እንዲሰበክና እንዲጠ ናከር ያደርጉ ነበር።*

በወጣቶች ያልተገነባ ድርጅት ዘላቂነት የለውም። ይህ የቴዎፍሎስ እምነት ነበር። ቴዎፍሎስ አዲስ ነገ ርን ሲያስቡ እንደመጣላቸው አይተገ ብሩትም ዘለቄታው ያሰጋቸው ነበርና። ወጣቶችን በቤተ ክርስቲያ ን ዙርያ የማደራጀት ቀዳሚ ዕቅዳቸው እንደነበረ ይታወቃል። ይህንንም ለመ ፈጸም በአንድ ሂራ ደብዳቤ የሰንበት ትምህርት ቤቶች እንዲቋቋሙ የሚል ትዕዛዝ ማስተላለፍ ምን ያግዳቸው ነበር? ሐሳባቸውን ለመፈተን መጻሕ ፍትንና የሌሎች ድርጅቶችን ልምድ ይመረምራሉ። ሌሎች አብያተ ክርስ ቲያናት ስለ ወጣቶች አደረጃጀት ያላቸውን ሥርዓት ከመመርመር በተጨማሪ የሰንበት ትምህርት ቤቶ ችን አደረጃጀት በሚመለከት እንግሊ ዝ በበርሚንግሀም ከተማ በ1938 ዓ.ም የተሳተፉበት ስብሰባ ለዚህ ራዕያቸው እንዱ/ሌላው ምዕራፍ/ ነበር።

የሰንበት ትምህርት ቤቶችን ጥንስስ በተማሩ ሰዎች እንክብካቤ በትምህርት ቤቶች ለመጀመር እንዱ የመረጡት ቅድስት ሥላሴ ትምህርት ቤትን ነበር። ሌላው የቀድሞው በአዲ ስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች የቀረበላቸውን ጥያቄ ተቀብለው ዘወ ትር ዓርብ በስብሰባ አዳራሻቸው እየተገኙ ይሰጡት የነበረው ትምህርት አንድ አገር አቀፍ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መንፈሳዊ ማኅበር እንዲ ቋቋም በማድረግ. የወሰዱት እርምጃ ነው። ማኅበሩን በማቋቋም ብቻ አልተ ወሰኑም ወጣቶች እምነታቸውንና ማኅ በረሰቡን በሚመለከት ሰፊ ዕውቀት እንዲኖራቸው በቅዱስ ሲኖዶስ አስወ ስነው የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን ቋሚ አባል እንዲሆን በማድረግ ለኦርቶዶክስ ወጣቶች ዓለም አቀፍ መድረክ ከፍተውላቸው ነበር።

ከዚህም አልፈው በብዙ ሀገሮች የሚገኙ ተማሪዎች በኮሚዩኒስት ርዕዮተ ዓለም በመጠመቅ መንግሥቶ ቻቸውን ለለውጥ ባፋጠጡበት ዘመን ቴዎፍሎስ ምንም ሳይሰቀቁ በአፍሪካ ምድር የመጀመሪያው የሆነውን የፌዴ ሬሽኑን 24ኛውን ጠቅላላ ጉባዔ በቤተክርስቲያን ጋባዥነት እንዲካሄድ አድርገዋል።

እንግዲህ ከዚህች አጭር ማስታ ወሻ የምንረዳው. የኦርቶዶክስ ወጣቶ ችን በሥነ ምግባር ለማነጽ የቤተ ክርስቲያንንና የሀገር መሪዎችን ለማፍ ራት ቤተ ክርስቲያኒቱ የሰጠቻቸውን አደራ ለመወጣት ያደረጉትን ጥረት ነው።

## ታዲያ ቴዎፍሎስ እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወት ኖረው ቢሆን ኖሮ!

*የነበሩት የወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበራት ተጠናክረውና አብበው እንዲሁም አያሌ አዳዲስ ማኅበራ ት ተደራጅተው ለቤተ ክርስቲያ ናቸው ጋሻ መከታ እንዲሆኑ የነበራቸውን ምኞት ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደርጉት ነበር።*

ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ የተዋሕዶ ትምህርትን ለማስፋፋት በመገናኛ ብዙኃን መጠቀም አመቺ መሆኑን ከተገነዘቡ ቆይተዋል። ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን የራሷ ሬድዮ ጣቢያ እንዲኖራት ዕቅድ ተለሙ። ከጣቢያው ጋር የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች ማሰልጠኛ እንዲኖርም በዕቅዱ በዝር ዝር ተተንትኗል። የሚተገበረ ውም ከብርሃ ንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ጀምሮ እስከ ናዝሬት ትምህርት ቤት ድረስ በነበረው የራሷ መሬት ላይ ኮምፕሌክስ ሕንጻ በማሠራት ነበር።

አዲስ ነገርን መቃወም የተለ መደ በመሆኑ ነቀፋው አጠገባቸው በነበሩ አበው ተጀመረ ንጉሡ ዘንድ ተጠሩ ዕቅዳቸውን ለንጉሡ አስረዱ። ንጉሡ በቴዎፍሎስ አካሄድ ቅር ቢ ሰኙም ያለ ቴዎፍሎስ ከንድ ቤተ ክርስቲያኒቱን ይህ መራመድ እንደማይ ሆንላቸው ስለሚያውቁ ማስከረፍ አልደፈሩም።

በሌላ በኩል ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ያቀዱትን እንዲተገብሩ መፍቀድም ቤተ ክርስቲያንን ቀስ በቀስ ከቁጥጥራ ቸው ውጭ ልትሆን እንደምትችል ስግተዋል። "... አባታችን የኢትዮጵያ ሬድዮ ማንን ሊያገለግል ነው የተቋቋ መውና ነው እርስዎ ሌላ ሬድዮ ጣቢ ያ ለማቋቋም የሚደክሙት?" ብለው መጠየቅ አስመሰሉና ንጉሡ "... ከአሁን ጀምሮ በየዕለቱ የግማሽ ሰዓት ፕሮግራም በኢትዮጵያ ሬድዮ እንዲ ጀመር ፈቅደናል" አሏቸው።

አቡነ ቴዎፍሎስ ከውስጥና ከውጭ /የሌላ ዕምነት ተከታዮችም/ ተቃውሞ ባይከባቸው ኖሮ በዕቅዳቸው መግፋት ንጉሡን ማንገራገር ይችሉ ነበር። ለዚህች ቤተ ክርስቲያን ሬድዮ ጣቢያ ማቋቋም ለጀመሩት ዕቅድ እራ ሳቸውን ብቻቸውን ቆመው ስላገኙት በኢትዮጵያ ሬድዮ በየዕለቱ የግማሽ ሰዓት የሃይማኖት ትምህርት መስጠት የሚለውን የንጉሡን ሐሳብ የግድ ተቀብለው፣ ሥራው ተጀመረ።

## ቴዎፍሎስ በሕይወት ኖረው ቢሆን ኖሮ!

*ለቤተ ክርስቲያናቸው ያቀዱ ት የመገናኛ ብዙኃን ዓለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀና በተለያዩ ክፍለዓለማት የሚገኙ የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት አንድነት መጠናከሪያ ወጥ የትምህርት ሥር ዓት እንዲሰፍን የሚያገለግል ኃይ ል ያደርጉት ነበር። የተዋሕዶን እምነት ለማስፋፋት፣ የኢትዮጵ ያን ክብር ለመጨመር የማይደፈ ርና የማይገፋ ተዋሕዶን እውነተኛ ሃይማኖት ኢትዮጵያ የነፃነት ብርሃን እንዲሆኑ ቋንቋና ኪነ ጥበብ ዓለም አቀፋዊ ደረጃ እንዲ ኖራቸው ያደርጉ ነበር።*

ቤተክርስቲያን በፀረ ሃይማኖት መንግሥት ተደፍራ ቴዎፍሎስ ከመን በራቸው ተወስደው በአሰቃቂ ሁኔታ ከተገደሉ እነሆ ዛሬ 31 ዓመት፣ አፅ ማቸው ተገኝቶ በክብር ካረፈበትና ሰማዕት ከተባሉበት እነሆ 18 ዓመት ሆነ።

ቴዎፍሎስ ፈተና ገንዘባቸው መሆን የጀመረው ሊቀ ሥልጣናት ተብለው ሲሾሙ ጀምሮ ነው ፈተናው ለቤተክርስቲያን ዕድገት የሚያቅዱትና የሚተገብሩት እንዳይሳካ የሚደረግ እንጂ ለራሳቸው ...የሰማይ አዕዋፍ የራሳቸው መኖሪያ የላቸውም.... ከሚባ ሉት የማይበልጡ እንደነበር በኑሯ ቸውም ከዚያ በኋላ የተመሰከረ ነው።

**በሕይወት**... ወደ ገጽ ፴፩ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## ፓትርያርክ... ከገጽ ፳፩ የዞረ

አባል አድርገዋታል። በዚሁ ድርጅት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በመሆን ብዙ ጊዜ አገልግለዋል። በየሰባት ዓመቱ በሚደረገው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን መልዕክተኞች በመምራት የሚሳተፉት እሳቸው ነበሩ።

በዚህ ረገድ በ1949 ዓ.ም. በኢቫንስተን አሜሪካ፣ በ1954 ዓ.ም ኒውደልሂ ሕንድ፣ በ1960 ዓ.ም. ኡፕሳላ ስዊድን በተደረጉት ጠቅላላ ጉባዔዎች የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን መልዕክተኞችን በመምራት ተሳትፈዋል።

በጉብኝታቸው አገሮችና አብያተ ክርስቲያናት፣ እንዲሁም በተሳተፉባ አቸው፣ ይጎብኟቸውም ነበር።

ከዚህም የተነሳ አያሌ ካህናትና ምእመናን በየጊዜው ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ታላላቅ ገዳማትን ማለትም የላሊበላ አብያተ ክርስቲያናትን፣ አክሱም ጽዮንን፣ ደብረ ዳሞን፣ የደሴተ ጣና ገዳማትን ወዘተ ይጎበኙ ነበር። ታላላቅ መንፈሳዊ ጉባኤዎች፣ ስብሰባዎችም አዲስ አበባ ላይ እንዲካሄድ ያላሰለሰ ጥረት ያደርጉ ነበር። በዚህ ረገድም ቢሆን በዘመናቸው ጥረታቸው ሠምሮ ሦስት ዐበይት ዓለምአቀፍ ጉባዔዎች በአዲስ አበባ ተካሄደዋል። እነርሱም፦

1ኛ. የኦሪየንታል ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት መሪዎች ጉባዔ፤

ውን ድርሻ ወስደው ባደረጉት ያላሰለሰ ትጋት ለአንድነና ለመጨረሻ ጊዜ ከግብፅ ቤተክርስቲያን ጭቁና ማላቀቃ ቸው ነው።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ማንኛውንም ነገር ስፋ አድርገውና አርቀው የሚመለከቱ ከአክራሪነት፣ ከጽንፈኝነት የጸዱ፣ የሚሰጡት ውሳኔ ሁሉ ሚዛናዊነት ያልጎደለው ነበር። በአጋጣሚ ምክንያት የመንፈሳዊ ኮሌጅ ተማሪዎች መማክርት ኅበረትን ጥያቄን ለአስቸኳይ ጉዳይ በቀጠሮ ሁለት ሆነን ወደ ቢሯቸው እንድንገባ በምክትል ሥራ አስኪያጁ ቀደም ሲል በብፁዕነታቸው በተሰጠ መመሪያ መሠረት የዲሲፕሊን ኮሚቴ የሲዳሞ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ብር



ቸው ጉባኤዎች ለሚያገኟቸው ታላላቅ መሪዎችና ምሁራን ሁሉ አገራቸውን ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት በነፃነት የኖረች ባለታሪክ አገር መሆኗን፣ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያንም ከቀደምት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ መሆኗን በርቱዕ አንደበታቸው በማስረዳት አስተዋውቀዋል፤ ለአገራችንም አያሌ ወዳጆችን አፍርተውላታል። ወደ ኢትዮጵያ እየመጡም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የእምነቷ መገለጫ የሆኑትን ታላላቅ በዓላትን ማለትም ልደትን፣ ጥምቀትን፣ ትንሣኤን፣ መስቀልን ሕዝበ ክርስቲያኑ በምን ዓይነት መልኩ እንደሚያከብራቸው ከቦታው ላይ በአካል ተገኝተው በዓይናቸው ተመልክተው ይገነዘቡ ዘንድ ያበረታቱ

2ኛ. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ማዕከላዊ ኮሚቴ ጉባዔ፤

3ኛ. የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን 24ኛ ጠቅላላ ጉባዔ ናቸው። የእነዚህ ጉባዔዎች ተሳታፊዎች በሙሉ ስለ ኢትዮጵያ ድንቅ ድንቅ ነገሮችን በማየታቸው ያደረባቸውን አድናቆት ያለምንም ማመንታት ለተለያዩ ጋዜጦች ሪፖርተሮች ሲገልጡ ተደምጠዋል።

ሌላው በውጭ ግንኙነት በኩል ከፈጸሙት ተግባር ጎልቶ የሚታየው ከግብፅ ኮፕቲክ ቤተ ክርስቲያን ለረጅም ዘመናት ካስቆጠረው ተጽእኖ ለመላቀቅ በተደረገው ትግል የአንበሳ

8,000/ስምንት ሺ ብር/ ለግል ጉዳዮቻቸው ማዋላቸው በኦዲተር ስለተረጋገጠ ከሥራቸው ያሰናበታቸው መሆኑን አስረዱ።

ቴዎፍሎስ ግን "ለመሆኑ ራሳቸውን ያልቻሉ ስንት ልጆች አሏቸው?" ሲሉ ጠየቁ። "እንዳጣራነው ሰባት ናቸው" በማለት መለሱ። "እራሱን ያልቻለ ልጅ በአባቱ እዳ አይቀጣምና በልተውና ተጠልለው የመኖር መብታቸው ሊጠበቅ ይገባል። እንዲያውም እኮ ቤተ ክርስቲያን የእነሱ ሰማውታ አሳድጊ መሆኗን አትርሱ። እዳውን በየወሩ ከደመወዛቸው ተቆራጭ እየ ተደረገ ይከፈሉ። ለማካካሻ በተቆራጩ

ፓትርያርክ... ከገጽ ፴፪ የዞረ





## የዝክረ... ከገጽ ፳ የዞረ

| ተ.ቁ | የክፍሉ አገልግሎት | ብዛት |
|---|---|---|
| 1 | መማሪያ ክፍል | 20 |
| 2 | ምዝገባ ክፍል | 1 |
| 3 | የርዕሰ መምህር ቢሮ | 1 |
| 4 | የም/ርዕሰ መምህር ቢሮ | 1 |
| 5 | የጸሐፊ ቢሮ | 1 |
| 6 | ሒሳብ ክፍል | 1 |
| 7 | የመምህራን ማረፊያ | 1 |
| 8 | ሻይ ቡና አገልግሎት መስጫ | 1 |
| 9 | ክሊኒክ | |
| 10 | ቤተ መጻሕፍት | 1 |
| 11 | ዕቃ ግምጃ ቤት | 1 |
| 12 | የመምህራንና ሠራተኞች መጸዳጃ | 2 |
| 13 | የተማሪዎች መጸዳጃ | 8 |

## የዝክረ... ከገጽ ፳ የዞረ

መሥራት የተቻለው ሁለት ብሎክ ሕንፃ ብቻ ነው። እነዚህ ሁለት ብሎክ ሕንፃዎች የሚከተሉት አገልግሎት መስጫ ክፍሎች አሏቸው።

የእነዚህ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች ግንባታ የተጠናቀቀ ሲሆን ትምህርት የመስጠቱን ሥራ ለመጀመር ለዓመታት ፈጽሞ የማይቻል ይመስል የነበረው ሥራ ከዚህ ደረጃ ላይ ደርሶ ማየቱ የሚያኮራና የሚያስመሰግን ነው። ሰው በጎ ዓላማ ይዞ እግዚአብሔርን አምኖ ከተነሣ የማያከናውነው ተግባር እንደሌለ ዝክረ ቴዎፍሎስ ት/ቤት ምስክር ነው።

ይህ ት/ቤት መንፈሳዊውን ትምህርት ከዘመናዊው ትምህርት አጣምሮ በመስጠት በሥነ ምግባር የታነጸ፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገር አለኝታ የሚሆን ትውልድ ለማፍራት በከፍተኛ ዝግጅት ላይ ይገኛል።

### የትምህርት ቤቱ መሪ ዓላማ፣

ሀ) ከሙዓለ ሕፃናት እስከ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ጥራት ያለው ዘመናዊና መንፈሳዊ ትምህርት መስጠት።

ለ) ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የምርምር ውጤቶችን በማበርከት ለቤተ ክርስቲያንና ለሀገራችን ዕድገት ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያደርግ በዓለም ታዋቂነት ያለው ዩኒቨርሲቲ ማቋቋም።

ሐ) ለጥንታዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት ማስፋፊያ የተለየ ትኩረት በመስጠት ልዩ ማሰልጠኛ ት/ቤት መክፈት።

መ) አጫጭር የሙያ ሥልጠናዎችን ማካሄድ።

እነዚህ አቅም በፈቀደ መጠን በአጭርና በረጅም ጊዜ የሚከናወኑ ተግባሮች ሲሆኑ ለጊዜው ግን ት/ቤቱ አገልግሎት መስጫ ቁሳቁሶችን አሟልቶ በ2003 ዓ.ም. የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ለመስጠት በዝግጅት ላይ ይገኛል።

ከዚሁ ጋር ት/ቤቱ እንደ አባትም እንደ እናትም የሚመለከተው ምዕመናንን በመሆኑ ተጨማሪ የትምህርት መስጫ ቁሳቁሶቹን ለማግኘት ተስፋውን የጣለው በምዕመናን ላይ ነው። ምዕመናን የሠሩት ይህ ት/ቤት እራሱን እስከሚችል ድረስ እንደማይለዩት እምነታችን ነው።

ዝክረ ቴዎፍሎስ ት/ቤት ትምህርት የመስጠት ዓላማውን በ1ኛ ደረጃ ይጀምር እንጂ አቅሙ እየጐለበተ ሲሄድ ወደ 2ኛ ደረጃ ት/ቤትና ኮሌጅ ከዚያም ወደ ዩኒቨርሲቲ ደረጃ ያድጋል። ከዚህም በላይ በታላቁ ሰማዕት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ስም አንድ ከፍተኛ የሕክምና ተቋም እንደሚከፈት ራዕይ አለን። አሁን የተጀመረው ት/ቤት ችግኝ ነው፤ ካህናትና ምዕመናን ውኃ እያጠጡና እየኰተኰቱ ከተንከባከቡት አድጎ ሀገርን የሚያጠግብ ፍሬ እንደሚሰጥ ጥርጥር የለውም።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከጥንት ጀምሮ የትምህርት ማዕከል እንደሆነች ይታወቃል። የሰማዕቱም ራዕይ ቤተክርስቲያን ይህንኑ ሚናዋን በተሻለ ሁኔታ እንድትጫወት ማስቻል ነበር።

የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል አስተዳደር ሰበካ ጉባኤ ለዝክረ ቴዎፍሎስ ት/ቤት እውን መሆን ሐሳብ በማመንጨት፣ የሙያ አገልግሎትና አመራር በመስጠት፣ የቁሳቁስና የገንዘብ እርዳታ በማድረግና በማበረታታት ድጋፍ ላደረጉት ሁሉ ምስጋናውን እያቀረበ፣ የሰማዕቱ የቴዎፍሎስ በረከት አይለየን ይላል።♦

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ታምራት አበራ

## አካባቢያዊ.. ከገጽ ፲፫ የዞረ

ቁርጠኝነት መገለጫ ነው። ከዚህም በተጨማሪ ለበርካታ ዘመናት በሕዝብ እና በመንግሥት ልብ ውስጥ የገነባ ችውን ተዓማኒነት እና በጎ ተጽእኖ ፈጣሪነት ይዛ እንድትቀጥል የሚያስች ላት መሟ ሪያም ጭምር ነው። በመሆ ኑም የቤተ ክርስቲያን ሃይማኖታዊ ሉዓላዊነት እንዲሁም ያላት ክፍታ ተጠብቆ እንዲቆይ የሚሻ ምእመን ሁሉ ከጎና ሊቆም፣ አለሁልሽ ሊላትም ይገባል።

የካቴድራላችን ሰበካ ጉባኤ አደባባዩን መገንባት የጀመረ ሲሆን በከተማ ደረጃ እንኳ ቢታይ ቀዳሚ የሚያስኘውን የአደባባይ ዲዛይን አሠርቷል። ከዚህም በተጨማሪ ለሥራው የሚያስፈልጉ ዝርዝር ጥናቶች በባለ ሙያዎች የተከናወኑ ሲሆን አጠቃላይ ወጪውም ታውቋል፤ ግንባታውን እና የበጎ አድራጊዎችን ስጦታ የሚያስተ ባብር ዐቢይ ኮሚቴም ተቋቁሟል፤ ኮሚቴውም የድጋፍ ማሰባሰቢያ እቅዶችን በመንደፍ እንቅስ ቃሴውን በይፋ ጀምሯል።

ከዚህ በኋላ የሚቀረው ሰማዕቱ ፓትርያርክ ለቤተ ክርስቲያናችን ያደረ ጉትን አስተዋጽዖ፣ በስማቸው እንደ ሚጠራ ለሚጠበቀው የአደባባይ ሥራ ድጋፍ በማድረግ እውቅና መስጠት ብቻ ነው።♦

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ

ኤርምያስ ዘመነ
የጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል ሰንበት ት/ቤት
ሊቀመንበር



www.ethiopianorthodox.org

## ሰማዕቱ... ከገጽ ፳፮ የዞረ

ዶክተር ጌታቸው ኃይሌ እና ብፁዕ አቡነ ጴጥሮስ፣ ወደ ግሪክ ከተላኩት ቀሲስ ዶክተር ምክረ ሥላሴ ገብረ አማኑኤል እና ረዳት ፕሮፌሰር ሉሌ መላኩ፣ ወደ ሩሲያ ከተላኩት ብፁዕ አቡነ ጢሞቴዎስ እና ብፁዕ አቡነ ገብርኤል፣ ወደ አውሮፓ ከተላኩት ዶክተር ጸጋዬ ሃብቴ እና ፕሮፌሰር በዕደ ማርያም ጸጋ ይገኙበታል።

ከላይ እነዚህን ጥቂቶች የጠቀስ ነው በወጣትነታቸው በታላቁ አባት ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ቡራኬና ጸሎት ተልከው ለዶክተርነት እና ለጳጳስነት የሚያበቃ ከፍተኛ ትምህርት መቅሰማቸውን ለማሳየት እንጂ በጳጳስነት፣ በሊቀ ጳጳስነት እና በፓትርያርክነት ዘመናቸው የላኳቸው እና ለከፍተኛ ትምህርት ያበቋቸው ወጣቶች እጅግ ብዙዎች ናቸው።

### ለጎፋ አካባቢ ሕዝብ የነበራቸው ትምህርት ቤት የማሠራት ራዕያቸው እውን መሆን

ዘመን የታሪክ እና የሃሳብ ማከማቻ መሆኑ ትውልድ ከትውልድ የሚወርሰው ቅርስ እና ባህል በየጊዜው እየጨመረ ይሄዳል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና ያለባት ኃላፊነት ክርስትናን ማብሰር ሆኖ ሳለ አዕምሮ ማነጽንም ተጨማሪ ኃላፊነት አድርጋ በመውሰድ ትምህርት ቤትም ሆነች። የኢትዮጵያን ልጆች አዕምሮ ለማነጽ እና ኢትዮጵያን ትምህርት የተስፋፋባት ሃገር ለማድረግ አድባራቷን እና ገዳማቷን በጠቅላላው አብያተ ክርስቲያናቷን ሁሉ ትምህርት ቤት አደረገቻቸው።

ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ይህንን ጥቅስ የተናገሩት በ1967 ዓ.ም ለመስቀል በዓል ባስተላለፉት መልዕክት ነው።

ይህም ጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ከመመረቱ አንድ ወር ቀደም ብሎ ነው። ይህ ቤተ ክርስቲያን ሲሠራ አሁን ለምርቃት የተዘጋጀው ት/ቤት የተሠራበትን ቦታ አኪፉ ሲሆን በቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የትምህርት ቤት ማሠሪያ ቦታ እንዲኖር ማድረጋቸው ከላይ በቀረበው ጥቅስ መሠረት በቅዱስ ስንታቸው አስተሳሰብ ያለምንም ጥርጥር የትምህርት ቦታ መሆኑን ያሳያል።

በርግጥ አምላክ ቅዱስ ገብርኤል ረዥም ዕድሜ ሰጥቷቸው ትምህርት ቤቱን ካቀዱት ቦታ ላይ እንዲሠራ ቢያደርጉ ኖሮ እጅግ መልካም ይሆን ነበር። ይሁን እንጂ 'ሰው ያስባል እግዚአብሔር ይፈጽማል' እንደሚባለው የአምላካቸው የቅዱስ እግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ከሊቀ ሊቃውንት ሳዕለ ማርያም አየለ ጀምሮ በተከታታይ በመካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል በአለቅነት የተመደቡ የመንፈስ ልጆቻቸው መምህር አባ ብርሃነ ሥላሴ /አቡነ ዲዮስቆሮስ/፣ አባ ገብረ ማርያም ገብረ ሥላሴ እና መልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መለኮት የትምህርት ቤቱን ሕንፃ በመቀባበል አሳንፀው ለምርቃት በማብቃት ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ለጎፋ አካባቢ ህዝብ የነበራቸውን ራዕይ እውን በማድረጋቸው ሊመሰገኑ ይገባቸዋል።

በተለይም መልአከ ፀሐይ አባ ኃይለ መለኮት የታላቁን አባት የሰማዕትነት ክብር በሁሉም ዘንድ እንዲታወቅ ለማድረግ የሚያሳዩት ያልተቆጠበ ጥረት አምላካችን እግዚአብሔር እንዲባርከው እና ከአሁን ቀደም በመውጣት በመውረድ ባስፈቀዱት የቴዎፍሎስ አደባባይ ሐውልታቸውን ለማሠራት እያደረጉ ያሉት እንቅስቃሴ የካቴድራሉ ካህናት እና ምዕመናን ከልብ ሊደግፉት እና አብረው ሊንቀሳቀሱ ይገባል እላለሁ።

### ማጠቃለያ

ከዚህ በላይ በቀረበው ጽሑፍ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ከራሳቸው ትምህርት ጀምሮ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት አመራር እየሰጡ፣ በሐረርጌ ሀገረ ስብከት ትምህርት ቤቶችን በማቋቋም እና ወጣቶችን ወደ ውጭ በመላክ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ተመልክተናል። ስለ አስተዋጽኦቸው የሚያውቅ ሰው ቢመሰክር ማጠቃለያው በእጅጉ እውነታውን ያስጨብጣል በማለት የመንፈስ ልጃቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ የተናገሩትን እንደ ሚከተለው እጠቅሳለሁ።

"ታላቁን አባት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስን እኔ እስከማውቃቸው ድረስ ገና ከገጾም እንደመጣሁ እንዲሁ ተመልክተው እንድማር ያደረጉኝ እርሳቸው ናቸው። የነበር ኩበት ገዳም አስተዳዳሪ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሊወስዱኝ ሞክረው ነበር። "እርሱን እኛ እንጠብቀዋለን፤ ከዚያ ያሉትን ጠብቅ" ነው ያሏቸው። ከእናት ከአባቴ የተለየሁት በ15 ዓመቴ ነው፤ በዚያ ዕድሜዬ ነው የእርሳቸውን ዝና መስማት እና ማወቅ የጀመርኩት። ይከቧቸው የነበሩት ትምህርት ፈላጊ ወጣቶች ብዙዎች ነበሩ። ታዲያ እር ሳቸው ማምት ያውቁ ነበር። ወይም መገመት ይችሉ ነበር፤ የሚወጣውን እና የማይወጣውን ተማሪ ለይቶ ለማወቅ ሙሉ ጸጋ ነበራቸው። ጥሩ ተማሪ ነው ተብሎ ከተነገራቸው በዚያ ላይ ከፍተኛ ትኩረት ያደርጋሉ።'

/ዝክረ ቴዎፍሎስ ሰማዕት መጽሔት ገጽ 5 ይመልከቱ/

ሊቀ ህሩያን ጌታቸው ኅይሌ

## ራዕየ... ወደ ገጽ ፲፱ የዞረ

ምዕዋት ተብሎ ተጽፎበት እንዲቆም ሆኖ በሙዳየ መባዕ የገባው ገንዘብ ለቤተ እግዚአብሔር በሙዳየ ምዕዋት የገባው ገንዘብ ለነዳያንና ምስኪናን ምጽዋት እንዲውል ይህንንም የሰበካው አስተዳደር ጉባኤ በየገቢው መዝገቦ ወደ ባንክ በየአርዕስቱ እያስገባ ለሰበካ ጉባኤ መዋጮ ምዕመናን ከሚከፍሉት ገንዘብ የድሆች ድርሻ እየወጣ ከሙዳየ ምዕዋቱ ገንዘብ ጋር ድኾች የሚረዱበት እንዲሆን የርዳታውም ሥርዓት ድኾችን በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ ኮልኩሎ ሣንቲም ማደል ሳይሆን ለሙት ልጆች የሕፃናት ማሳደጊያ በማቋቋም በድርጅት መርዳት ነው። የሚረዱት ሰዎችም በሰበካቸው እየተመዘገቡ እንዲሆን የሌላ ሰበካ ተረጂም ሳይቀላቀል ሁሉም በየአጥቢያው በሥነ ሥርዓት እንዲረዱ ለማድረግ ራዕይ ነበራቸው።

### ማጠቃለያ

ከላይ በዝርዝር የተገለጡት የሰማዕቱ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ራዕያት አንዳንዶቹ በ3ኛው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አብዛኞቹ ደግሞ በ5ኛው ፓትርያርክ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ምክር ቤት ፕሬዝዳንትና የዓለም ሃይማኖቶች ለሰላም የክብር ፕሬዝዳንት በሥራ ተተርጉመዋል። በሥራ ላይ ያልዋሉትም ወደፊት ይፈፃማሉ ብለን በተስፋ እንጠብቃለን።

የሰማዕቱ የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ በረከትና ረድኤት አይለየን።

ሊቀ ካህናት ከንፈ ገብርኤል አልታዬ በመምሪያ ኃላፊ ማዕረግ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ አባል

> "ሰማዕታትም የዚችን ዓለም ጣዕም በእውነት ናቁ ደቸውንም ስለ እግዚአብሔር አፈሰሱ ስለ መንግሥተ ሰያትም መራራ ሞትን በታገሡ።"
>
> የሐሙስ የእመቤታችን ምስጋና



www.ethiopianorthodox.org



## በሕይወት... ከገጽ ፳፯ የዞረ

ታዲያ ቴዎፍሎስ ከመሸሸ ይልቅ መስዋዕት ለመሆን መፍቀዳቸውና መምረጣቸው ምን ያስተምረናል?

- ❖ 48 /አርባ ስምንት/ ቀናት እህል ሳይቀምሱ በጸሎት ተግተው ያሳዩትን ጽናት ከታደልን ለእየእንዳንዳችን ቋሚ ምሳሌ ናቸው።
- ❖ ቤተ ክርስቲያናቸውንና ምዕመናንን በአባትነታቸው አለማሳፈራቸው እግዚአብሔር ከፈቀደልን ለሁላችንም አስረ ፍኖታቸውን ለመከተል እንድንበቃ ነው።
- ❖ በስቃያቸውና በግፍ በመገደላቸው ለእኛ ለክርስቲያኖች የጥንካሬ የእውነተኛ በጎች እረኞች ሆኖ መገኘትን እንዲመርጡ ያመለክተናል።
- ❖ በሞታቸው ፀረ ቤተ ክርስቲያን አቋም ያላቸው እኩያን ተጋልጠው እንዲያፍሩ በማድረጋቸው የዛሬ እና የነገ አበውም ለዚህ እንዲቆሙ ያስተምራሉ።
- ❖ በተቀበሉት መከራና ሞት ለተተኪ የቤተክርስቲያን መሪዎች አርአያነትንና ጥንካሬን ዘወትር ቀስቃሽና ወቃሽ እንዲሆንባቸው በቤተ ክርስቲያን ታሪክ መዝግበዋል።
- ❖ ፀረ ቤተ ክርስቲያን እና ፀረ ሕዝብ መሪዎች ሕዝብን መግዛት ቀርቶ መፈጠር እንደሌለባቸው ከአባቶቻቸው ሐዋርያት የተቀበሉትን አደራ መወጣታቸውን በአደራ /በቃለ መሐላ የተረከቧትን ቤተ ክርስ ቲያን ክብር ላለማስደፈር የከፈሉት መሥዋዕትነት ለዘመናት መታሰቢያና በመንገዳቸው ለሚቀጥሉት አበው ድግም ኩራት፣ ከለላና መኩሪያ እንዲሆናቸው ተልዕኳቸውን በመፈጸም አረጋግጠዋል።

ሰማዕቱ ቴዎፍሎስን በአንድ ቀበሌ እና በአንድ ቤተ ክርስቲያን ትጽር ግቢ ብቻ መወሰን በትዕቢት ያስጠለፏቸውንና በግፍ የገደሏቸውን እኩያን ድርጊት መባረክ ይሆናል። አቡነ ቴዎፍሎስ በአገልግሎት ዘመናቸው የዕውቀት ብርሃናቸው ለዓለም እንደተረፈ ሁሉ ዛሬም ብርሃኑ እንዲቀጥል የሚያስችል ደረጃ ሊሰጣቸው ይገባል።

አባ ቴዎፍሎስ ዛሬ ከተወለዱ አንድ መቶ ዓመት ሆናቸው። ገና ፋቅ በሚያስቡትና ብዙ በሚተገብሩት አፍላ ዕድሜ ላይ እያሉ ከመንበረ ፕትርክናቸው በግፍ ታፍነው የታሰሩ ከሰላሳ ዓመት በፊት የካቲት 9 ቀን በ1968 ዓ.ም ነበር። ይህ ይፈጸም ዘንድ የደርግን አካሄድ አስቀድመው ያውቁት ነበር። ሲወስዷቸው እንደማ ይመለሱም በመረዳት ይዘው የሄዱት የወርቅ መስቀላቸውንና የጸሎት መጻሕፍቶቻቸውን ነበር።

በግፍ ከመገደላቸው ቀደም ብሎ ፊታቸው እስኪደማ ጸፍተዋቸዋል፣ ከብረት አልጋ ጋር ለቀናት አስረዋቸዋል፣ በባዶ እግራቸው እንዲሄዱ አድርገዋቸዋል፣ የክርስቶስን መጎናጸፊያ እንደተካፈሉት ሁሉ በሃያኛው ክፍለ ዘመንም ልብሳቸውን ከልክለው ተቀራምተውት እንዲታረዙ አድርገዋቸዋል። የደርግ መንግሥትም በበኩሉ የእጃቸውን የወርቅ መስቀል እንደ ድርሻ ቆጥሮ ቀምቶ ወስዶታል።

በመጨረሻም በልዩ ኮማንዶዎች እጅ በገመድ አንቀው ገድለው አስከሬናቸው እንዳይገኝ ድንጋይ እና ትቢያ እንዲከመር በት አድርገዋል።

ሰማዕቱ ቴዎፍሎስ ለዓለም ሰላም ባደረጉት ጥረት በአሜሪካ የሚገኘው የቅዱስ ዮሐንስ ዩኒቨርሲቲ "ፓክስክሪስቲ፤ የክርስቶስ ሰላም" የተባለውን ሽልማት ሲሸልም በተጨማሪ በአመራራቸው ተጠልቶ በማያልቀው ዕውቀታቸው የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያንና ኢትዮጵያ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በማስተዋወቃቸው ከዚሁ ተን ዩኒቨርሲቲ የዶክትሬት ዲግሪ አግኝተዋል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሀገራቸው ግን እጃቸው ከተያዘበት እ ጽማቸው እስከ ተገኘበት ዓመት ድረስ ሮቶ ግራፋቸው ካገለገሉባቸው ቢሮዎች እና አዳራሾች እንዲነሡ ስማቸውም የመንፈስ ቅዱስ ልጃቸው ፓትርያርክ ጳውሎስ በመንበራቸው እስኪተኩበት ዕለት ድረስ በቤተ ክርስቲያን ጸሎት ላይ እንዳይነሣ ተደርጎ ቆይተዋል።

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበርና የግብፅ ቤተ ክርስቲያን "በፓትርያርክ ላይ ፓትሪያርክ አይሾምም" የሚለው ሕገ ቤተ ክርስቲያን መከበር አለበት በማለት ከእሳቸው ቀጥለው በየተራ ለተሾሙ ፓትርያርኮች ዕውቅና ከልክለው በዕኑ ታግለዋል።

የቤተ ክርስቲያናችን የሲመት ሥርዓት ተከበረ ብሎ ዓለም የተቀበለው በሕጋዊው ፓትርያርክ ቴዎፍሎስ እጅ ተቀብተው ማዕረገ ጵጵስና ያገኙት ጳውሎስ ፓትርያርክ ሲሆኑ ነው። ይህም ለዓመታት በተፈጠረው ችግር ምክንያት ተቋርጦ የነበረው ሥርዓት ወደ ነበረበት ተመለሰ ማለት ነው።

እንግዲህ ንብ አውራ ከሌለው ይበተናል የቤተ ክርስቲያን አባቶችም ራሳቸው ተባብረው ምዕመናንን በማስተባበር የደርግን ግፍ ቢቋቋሙ ኖሮ ደርግም የልብ ልብ ተሰምቶት በቤተ ክርስቲያን ሥልጣን እናት ላይ ዘሎ አይከመርም ነበር። ቤተ ክርስቲያንም የበለጠ አለኝታነቷን በማስመስከር የተፈጠረውን ጥቁር የታሪክ እድፍ



እንዳይደርስ ለማድረግ ትችል ነበር።

እንግዲህ እነዚህን አባት ቤተ ክርስቲያን ሰማዕት ከማለት አልፋ ዓበይት ብሔራዊ መታሰቢያዎችን ብታቆምላቸው፦

- ❖በወቅቱ ቤተ ክርስቲያን መናገር ባልቻለችበት ጊዜ የሚቆምላቸው አጥተው አብረዋቸው ለወደቁ ብዙኃን፤
- ❖በተመሳሳይ ምክንያት በግፍ ለተሰውት ሕፃናት፣ እናቶች፣ ምሁራን፤
- ❖እንደሳቸው ሁሉ የነበረው ሥርዓት እንዲሻሻልና እንዲጠናከር ጥረት ላደረጉና ለሚያደርጉ፤
- ❖ተመሳሳይ አባቶች እንዲኖሩ አሠረ ፍኖታቸውን እንዲከተሉ ክብር ይሆን ዘንድ እንጂ ለሳቸውማ ምን ይረባቸዋል?

እንግዲያው ፓትርያርክ ሰማዕት ቴዎፍሎስ ዛሬ ይህች ቤተ ክርስቲያን፣ ምዕመናንና ወጣቶች የሚገኙበትን ሁኔታ ለማየት ቢታደሉ ምን ይሉን ይሆን?

በመጨረሻም ሁሉን ቻይ፣ ይቅር ባይ፣ ስጥቶ የማይልቅበት ቸሩ ፈጣሪያችን የሰማዕቱ ቴዎፍሎስን ዕውቀት፣ ትዕግሥት፣ ጥበብ፣ የመንፈስ ጥን ካሬ... ያካፍለን አሜን።❖

በአዳም መልአኩ

**ፓትርያርክ...** ከገጽ ፳፰ የዞረ

መጠን ጨዋምሩላቸው" በማለት ውሳኔውን አሻሽሉት።

ቴዎፍሎስ ማንኛውም ባለሙያው በሙያው ማንም ሰው ሰብአዊ መብቱ መከበር እንዳለበት በተግባር አሳይተዋል። እንደሚታወቀው የዕደ ጥበብ ባለሙያ የነበረው በደለበ የዘረኞች ባህል ምክንያት ቤተ መቅደስ ገብቶ እንዲቀድስ ስለማይፈቀድ ሥልጣነ ክህነትም አይሰጠውም ነበር። ወዲያው የጵጵስና መአርገ ክህነት እንደተቀበሉ ወደ ተወለዱበት ወደ ደብረ ኤልያስ በመሄድ ሸማ ለሚሠሩ ባለሙያዎች ሥልጣነ ክህነት በመስጠት ቤተ መቅደስ ገብተው እንዲቀድሱ አድርገዋል።

በሀገረ ስብከታቸው በሐረርጌ አጋዴንን ሲጎበኙ በጅጅጋ አውራጃ አንድ የብርጌድ አገርኘ ጦሩን እንዲጎበኙና ቃለ ምዕዳን እንዲሰጡለት ይጋብዛቸዋል። እሳቸውም ግብዣውን ተቀብለው ወደ ጦሩ ሠፈር ይሄዳሉ። እንደደረሱም ወታደሮቹ ወደ መሰብሰቢያው አዳራሽ በመግባት ላይ ነበሩ። ነገር ግን ጥቂት ወታደሮች በጾም ወራት ፍሪዳ አርደው ሲቃረጡ በጨረፍታ አይተው ያላዩ በመምሰል ወደ አዳራሹ ይገባሉ። ወታደሮቹ ግን ይደነግጣሉ። ሆኖም እንዳላዩአቸው ይገምታሉ። በአስቸኳይ እነሱም ወደ አዳራሹ ይገቡና የተሰጠውን ትምህርት ያዳምጣሉ። ትምህርቱ በጦርነት ላይ መግደልም ሆነ መሞት ያለ መሆኑን ነገር ግን ሰራስም ወገን ሆነ ለሌላው ሰብዓዊ ርኅራኄ የተመላበት ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን አንዳንድ ምሳሌዎችን በመጥቀስ አጥብቀው ይመክሯቸዋል።

ምንም እንኳን በሙያ ቢለያዩም በጦር ሜዳ ላይ ያለ ወታደርና በበረሃ የሚኖር ባሕታዊ አንድ ናቸው። በአካባቢያቸው ያገኙትን ቀምሰው ሥጋቸው ከነፍሳቸው እንዳትላቀቅ ያደርጋሉ። አንድ በበረሐ ወድቆ ይኖር የነበረ ባህታዊ የዕለት ምግቡን ያገኝ የነረው በበኣቱ አካባቢ ወጥመድ አጥምዶ በየዕለቱ አንድ ቆቅ ገባለት እንደነበረና ጦሙን እየዋለ በቀን አንድ ጊዜ ከተሲአት እሷን ጠብሶ ይበላ እንደነበረ እያብራሩ አስተማሯቸው።

እያደዘውም አንድ ቀን እሱን መሰል እንግዳ ሲጎበኘው መጣና ለእግዳው ሲባል ሌላ ተጨማሪ ቆቅ በወጥመዱ ወስጥ ገባች። ሁለቱን ቆቆች ጠብሶ አንዷን ለራሱ ሌላዋን ለንደኛው አቀረበለት። ንደኛው ግን እንዴት በጾም ቆቅ ታቀርብልኛለህ ብሎ አልበላም አለው። ለመበላት ቀርባ የነበረችው ቆቅም በራ ሄደች። ቅድም ቅርጫ ስትቃረጡ ስለአየኋችሁ ቅር አይበላችሁ። እኔና ቤተ ክርስቲያናችሁ እንጸምላችኋለን። እያሉ መጽሐፍ እየጠቀሱ የጾምን ረቂቅ ምሥጢር አስተማሯቸው ቅዱስነታቸው ለማን ምን ዓይነት ትምህርት መስጠት እንዳለበት ቅዱስ መንፈስ የሚአ ቀብላቸው አባት እንደነበሩ ከዚህ ትምህርታቸው መገንዘብ ይቻ ላል።

በመጨረሻም ላስታውስ የምፈልገው አብያተ ክርስቲያናት ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ ዓላማቸው ላይ አንድነት ፈጥረው ጸረ ክርስትና ኃይላትን መመከት እንዳለባቸው አልመው ነበር። ያን ሕልማቸውን በሲመተ ፓትርክናቸው ላይ በአስሙት ቃለ ሃይማኖት ከሰጡት የማጠቃለያ ሐሳብ መገንዘብ እንችላለን።

"ካለፈው ጊዜ ይልቅ ይህ የምንኖርበት ዘመን የክርስትናን እምነት ለማዳከም ልዩ ልዩ ዓለማዊ ኃይል የተነሣበት ጊዜ ነው። በእናንተ ጸሎትና እርዳታ ይህን ፈተና ለመቋቋም በመላው ዓለም ካሉት ክርስቲያኖች ጋር በመተባበር የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን ለመጠበቅ በሚበጅ መንገድ የማያቋርጥ ጥረት አድርጋለች።

በዓለም ሁሉ ሰላም እንዲሰፍን፣ ተንኮልና ክፋት እንዲጠፋ፣ እንዲሁም በሰዎች መካከል የዘርና የወገን ልዩነት እንዲወገድ የተቻለኝን ያህል እጥራለሁ። ይህንን ከባድ ሥራ ለማከናወን ተዘጋጅቻለሁ። ለዚሁም የልዑል እግዚአብሔርን እርዳታ እለምናለሁ።" ይሁን እንጂ ይህን የመሰለው ሕልማቸውና ራዕያቸው በአረመኔው ደርግ ባጭሩ ተቀጨ።✦

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
በዓለማየሁ ዓለምነህ

**ግብረ...** ከገጽ ፲፯ የዞረ

ማቴ.10፥28 ከነፍስ ሞትና ከታሪክ ሞት ግን ሕያው ናቸው።

በቅዱስ ቴዎፍሎስ ፓትርያርክ ላይ ሰባቱ ሀብታት ያደሩባቸው መሆናቸውን እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ ያሳዩት ፍጹም ገድላቸው ያሳያል። እነሱም፦

1ኛ. መንፈስ ሰብዎ፣
2ኛ. መንፈስ አእምሮ፣
3ኛ. መንፈስ ጥበብ፣
4ኛ. መንፈስ ምክር፣
5ኛ. መንፈስ ኃይል፣
6ኛ. መንፈስ ረድኤት እና
7ኛ. መንፈስ ፈሪሃ እግዚአብሔር ናቸው።

❖<u>መንፈስ ሰብዎ፤</u> ስጦታን መመርመር፣ ሰውና እግዚአብሔርን ለይቶ ማገልገል፣ እዝነ ሥጋን ለእዝነ ልብ፣ ዓይነ ሥጋን ለዓይነ ልብ ማስገዛት ወዘተ ናቸው።

❖<u>መንፈስ አእምሮ፤</u> ክፉና በጎን፣ እውነትና ሐሰትን፣ ጥቅምንና ጉዳትን፣ ለይቶ ማወቅ የተሻለውን መያዝ የተሻለውን መከተል ናቸው።

❖<u>መንፈስ ጥበብ፤</u> በሥጋዊና በመንፈሳዊ ጥበብ መበልጸግ መጻሕፍትን እንብቦ ተርጉሞ የተመሰሰውን አፍታቶ ርቱዕ በሆነ አቀራረብ ምዕመናንን ማስረዳት የሚሠሩትን ሥራ ሁሉ በፈሪሃ እግዚአብሔር መፈጸም።

❖<u>መንፈስ ምክር፤</u> ምክርን የሚገልጥ መክሮ አስተምሮ ማስታረቅ ለልቡና የሚስማማ በመንፈሳዊ ፈሊጥ ሰዎችን እርስ በእርሳቸው አስታርቆ ማዛመድ።

❖<u>መንፈስ ኃይል፤</u> ምዕመናንን አስተባብሮ ሥራ ማሠራት ማኅበር ማቋቋም ለካህናት ለመምህራን ለዲያቆናት ጥላ ከለላ የሚሆን ድርጅት ማቋቋም።

❖<u>መንፈስ ረድኤት፤</u> አስቦ መጀመር ጀምሮ መፈጸም ተናግሮ ማሳማን ሰዎች ያጡትን እንዲያገኙ ማገዝ በችሎታ ሁሉ መርዳት።

❖<u>መንፈስ ፈሪሃ እግዚአብሔር፤</u> ሁል ጊዜ ፈሪሃ እግዚአብሔርን ከተግባር አለመለየት ክፉ መንፈስን ክፉ ፈቃደ ሥጋን በፈሪሃ እግዚአብሔር ድል መንሳት ናቸው። ኢሳ.11፥1-4፤ 1ኛ ተሰ.5፥14፤ ሲራ.1፥11-14፤ ኢሳ.50፥4፤ ሉቃ.4፥22 እኒህ ሀብታተ መንፈስ ቅዱስ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ስጦታዎች ነበሩና በተግባር ታይተዋል።✦

በረከታቸውን ያድለን አሜን
መምህር ደጉ ዓለም
ቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ዩኒቨርሲቲ
መምህር





# ሥነ ግጥም

በሊቀ ዲ. ተስፋዬ መኩሪያ ገሠሠ

## ተዋሕዶ

የእናት የአባቱ የውል ሰነድ
ጥንታዊቷ መሠረቴ፣
የሕፃንነት ማኅተሜ
ሞገስ ክብሬ ለሕይወቴ።(ለድኅነቴ)
ዘለዓለማዊት ማረፊያዬ
ሁለንተናዬ ፍጥርጥርቴ፣
አንቺ ነሽ ተዋሕዶ
የማንነት ጥያቄዬ የምንነት ምልክቴ።
የጻጻሳት ግርማ ሞገስ
የመነኮሳት አስኬማ፣
የቴዎፍሎስ ቃለ ትንቢት
የስብዕናው ልዩ ዓርማ።
የነቢያት የሐዋርያት
የጻድቃን የደናግል፣
የተጋድሎ የደም ጠብታ
የሰማዕታት የድል አክሊል።
የዮሐንስ ራዕይ
የማቴዎስ ቃለ ወንጌል፣
የቅዱስ ኤፍሬም ውዳሴ
የዳዊት መዝሙረ ቃል።
አንቺ ነሽ ተዋሕዶ
የሊቃውንቱ ጸናጽል፣
የቀሳውስቱ የእጅ መስቀል።
የሕግና የሥርዓት ምንጭ
የበጐ ነገር መፍለቂያ፣
የክርስትና የእንነት ማኅተም
የምዕመናን መታወቂያ።
የንጹሐን የጸሎት ቤት
የቅዱሳን መደበቂያ፣
ስርዝ ድልዝ የሌለብሽ
የፈጣሪ የእጅ ጽሑፍ፣
መናፍቃን የማይዘጉሽ
የማይከፍቱሽ የምስጢር ቁልፍ፣
አንቺ ነሽ ተዋሕዶ
ድኅነተ ነፍስ የእልፍ አእላፍ።
የፍቅር አደባባይ
የአክብሮት ቤት የትሕትና፣
የስግደትና የእስተብርኮት
የንስኃና የቀኖና፣
የነዳያን መጠለያ
የርኁባን ፍተ-መና፣
በአርባ እና በሰማንያ
የቀን ቀመር ተቆጥሮለት፣
በጥምቀት የሚኙብሽ
የሥላሴ ልጅነት፣
አንቺ ብቻ ነሽ ተዋሕዶ
የአብ፣ የወልድ፣
የመንፈስ ቅዱስ አንድነት።
የመምህራን የወንበር ጌጥ
የመተርጉማን እንድምታ፣
የዋሸራ ሰምና ወርቅ
የጉንጅ-ጽላሎ ውስጠዘ
ምሥጢረ ዋድላ ደላንታ፣
አንቺ ነሽ ተዋሕዶ
የአቋቋሙና የድጓው
የያሬድ የዜማ ኖታ።
የዓለሙን እምነት ከንቱ ነገር
ከመከተል በተለምዶ፣
ከአንቺ ጋር ነው የሚሻለው
አብሮ መኖር ተዋሕዶ።

## አይቀርም ተቀብሮ

ደስ ብሎታል ቂራ ደስ ብሏታል ጎፋ
በዚህ በጎ ተግባር ቀድሞስ ማን ሲከፋ
ደስ ብሏታ ጎፋ ደስ ብሎታል ቂራ
ቀድሞስ ማን ሲከፋ በዚህ በጎ ሥራ
የዚያ የታላቁ የቴዎፍሎስ ክብር
በቦታ - በጊዜ ተወስኖ እንዳይቀር
በጳውሎስ ጥረት በመንግሥት ትብብር
ከእንግዲህ ይሆናል የአደባባይ ምሥጢር
ለኢትዮጵያ መንግሥት ምን ያንሰዋል ከቶ
እየመሰከረ የሞተው ተነሥቶ
ልማታዊ መንግሥት መሆኑንም ደግሞ
ገና ይናገራል ቴዎፍሎስ ቆሞ
ጠላት ቢሞክርም ሊያስቀረው ሰውሮ
የሰው በጐ ሥራ አይቀርም ተቀብሮ።

*ወደፊት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ስም የሚሰየመውንና ሐውልታቸው ይሠራበታል ተብሎ የታሰበውን አደባባይ የጎ/መ/ሕ/ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል በባለቤትነት ሲረከብ የቀረበ*

## ያለ ዕድሜው

በአስራ ሰባት ዕድሜው
ገና ሳለ ጨቅላ፡
የሰው ደም ከጠጣ
ሥጋውን ከበላ፣
ደርግ ጻድቅ እንጂ
ምን ሲባል ነው ኋላ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅኔያት ዘሠይፈ ሥላሴ ዮሐንስ

## ጉባኤ ቃና

1. ጳውሎስ ወልድ ወሕንጻ ትምህርት ሐዲስ፤
የዐብዩ ስመ ዘቴዎፍሎስ ቅዱስ፡፡

2. መካነ ሕያዋን ርእየት ይእዜ÷
ቴዎፍሎስሃ ዐቢየ፤
ቴዎፍሎስሃ ይሬኢ አኮ÷
ጳውሎስሃ ዘርእየ፡፡

3. በጥቃ ቴዎፍሎስ አብ ተደለወ÷
መንበረ ጳውሎስ ወልድ፤
ማእከለ ወልድ ወአብ÷
እስመ ኢይበውእ ባዕድ፡፡

## ሥላሴ

1. አፍርሀ ብዙኃነ÷
ገዳመ ጽጌ ክበር ቴዎፍሎስ÷
እመ አስተርአየ ብከ ጸዊር÷
ቀራንዮሳዊ መስቀሉ፤
ሞትከ ባሕታዊ ዘይጌሥጽ ኵሉ፡፡
ድኅረ እምኒነ ኀበእ አሠር÷
ወኢያስምዐነ ቃሉ÷
እስመ ለዮሐንስ ተመሰሉ÷
ኀዲጎ ገዳመ መንግሉ ሀሉ÷
በገፋዒ ከመ ያርኢ ኃይሉ፡፡

2. ነበረት ባሕቲታ ÷
በዐጸደ መስፍን ቤተ መቅደስ÷
ኀበ ቦ መልእክ ሐራዊ÷
ቅኑተ መጥባሕት ስሁል÷
ፈትል ዘውስተ እዴሃ ሥጋከ ድንግል፡፡
ወድንግል ሥጋከ አሐቲ÷
እንተ ፈተለቶ ፈትል÷
ኮነከ ዮም ልብሰ በዓል፡፡
ኦ ኃያል ወመስተጋድል
ምስለ ኃይል ቴዎፍሎስ ኃይል፡፡

## መወድስ

1. ኢትዮጵያ ኢክህለት ሰሚዐ ዘይቤ÷
ጠ ቢባነ ኩኑ ከመ አርዌ ምድር ቃለ ክርስቶስ፡፡
እመ ከመ አርዌ ተተሥሬት÷
በበትረ ሐዲን ይቡስ÷
አኮ ኢዐቀበቶ÷
ለዘኮነ መካነ ጥበባ÷
ቴዎፍሎስ ርእስ፡፡
ወበቅድመ አሕርው ገጸፈቶ÷
ለቴዎፍሎስ ባሕርያ÷
ዘያበርሃ ለነፍስ፡፡
ኀቡረሂ ያጸንዕዋ÷
ለአረፍተ ሞት ሐዲስ÷
በያመ ገዳም ወልደ ዮና
ወማእሰረ ሐብል ቴዎፍሎስ፡፡
ወመልዕልተ ነዋኅ ደብር÷
ክዋነ ሰማዕት ቅዱስ÷
ቴዎፍሎስ ተለዐለ÷
በተስሕቦ ሐብል ዘበሥሉስ፡፡

2. ፍሬ ቴዎፍሎስ ወይን ዘእስክንድርያ÷
በጠለ ቴዎፍሎስ ይፈሪ
ጳውሎስ ጽጌ ረዳ፤
አስተርአየ ለነ እምድኅረ ዓመታት ዘፍዳ፡፡
በጳውሎስ እምጣነ ተረክበ
ቴዎፍሎስ ቴዳ፡፡
ወበቴዎፍሎስ ወርቀ ጋዳ÷
አክሊለ ጳውሎስ ኮነ÷
ቀይህ ወጸዐዳ፡፡
ኢክህለትሂ ከመ ትባእ÷
ውስተ ቤተ ሳይዳ÷
ሕምምተ አካል ኢትዮጵያ÷
እንተ ደም ይትዋረዳ፡፡
ወዓዲ ረሰየት ዐውደ ጲላጦስ ዐውዳ፤
እስመ ሖሩ ሰብአ ቤታ
በምክረ አኪጦፌል ወይሁዳ፡፡

2. ሥርናየ ተገፍዖ ዘውድቀት በኢትዮጵያ÷
ፈረየት ምእተ ÷ ምስለ ሠላሳ ወስሳ÷
ድኅረ መስተገብር ጴጥሮስ÷
ለገራሕተ ደም ሐረሳ÷
ሚካኤል ከመ ይስትያ÷
ማየ ደም እስመ ተሳተፈ ወኮነ ሞገሳ፡፡
ወድኅረ እሉ ቴዎፍሎስ÷
ከላስስቲሃ አሰረ÷
በማእሰሬት ዘይሚለሳ፡፡
አጽገበትሂ በፍሬ እሉ÷
ቤተ ክርስቲያን ነፍሳ÷
ጳውሎስ እስመ ቆመ÷
ለተልእኮታ ጊዜ ተጽናሳ፡፡
ወበንዘና ኢበልየ÷
ለቤተ ክርስቲያን ሕዋሳ÷
ወልደ ቴዎፍሎስ ጳውሎስ
እስመ ከመ ንስር ይሔድሳ፡፡

4. ቃለ ምሳሌ ተብህለ ለወልደ ምሳሌ÷
ወልደ ወላዲ ይስርገው÷
እንዘ ቦ ወላዴ ወልድ፡፡
ወፍጡነ ይሩጽ÷
በፍና ሩጸተ ገሀድ÷
ዑሓይ እንዘ ቦ በሰማይ ወዱድ፡፡
ዮእዜሰ ተወለጠ
ኵሉ አምሳል÷ ወኵሉ ባህለ ልማድ፡፡
እስመ ቴዎፍሎስ ተሰርገወ÷
በፅንቱ ውዳሴ መረግድ፤
ጳውሎስ ዘወለዶ
እንዘ ቦ በውስተ ዐውድ፤
ወእንዘ ሀሉ ጳውሎስ÷
ፀሐየ ሊቃውንት አዕማድ÷
ቴዎፍሎስ ይረውጽ÷
በመርኅበ ስሙ ሕንጸ ማሕፈድ፡፡

በመጋቤ ብሉይ ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ
የሊቃውንት ጉባኤ መምሪያ ኃላፊ





# ቅኔያት

## ሥላሴ

ተመየጥ መንገሌሃ
ለኢትዮጵያ እምደማስቆ
ይቤሉ ለሳውል እግዚኡ እንዘ ይነብር ሰማየ
መቅድመ እስመ ረሰይኩከ ንዋየ ኅሩየ
ከመ ታስተራትዕ ሕገ ነፍሳዊ ወከመ ትፁር ስምየ
በውስተ አሕዛብ መዋርሥትየ
ጳውሎስኒ አውቅየ ወማዕምርየ
ሐናንያ ይንግርከ ቃልየ

## መወድስ

ኃይለ መለኮት ንዕልተ በይነ ዘረስያ
ለዛቲ መካን ዑጽፍተ ገቦሃ ድዮስተያቡ
እመ ለዓይነ ሰብእ ይሴኒ ለሡራሪሃ ክበቡ
ላኀቃነ ክህነቱ ለጳውሎስ
ጳጳሳት እንበለ ይብልዑ በዓይኖሙ ጸግቡ
እንዘ ይሬእዩ ኅብረ ገጻ
ለጽርሐ ቴዎፍሎስ አብ ወለጳውሊ በወርኃ ምግቡ

## ለዓለም

ለቅዱስኒ ቴዎፍሎስ መካነ ሕያዋን ምኩራቡ
ተብሕለት ዘሐነጸ እግዚአብሔር በጥበቡ
አእጻዳተ ቤታ አውያን እስመ ፍሬ ጸጋ ሐንበቡ
እስከ ይትፌሥሑ ምዕመናን እለ ጽድቀ ይርኅቡ

## ኵልክሙ

መካነ ሕያዋን መሰለት ወይነ ሰማርያ
እንዘ ፍሬሃ ሠናይ ወእንዘ ጼናሃ ምዑዝ፡፡
እምጣነ ላቲ ያበርህ ከመ ሠርቀ ቤዝ፡፡
ኮከብ ጽባሐዊ
መምህርን ኃይለ መለኮት ዘሥኑ ሐዋዝ፡፡
እምጉባዔ ቤቱ ለጳውሎስ
በይነ ወለደቶ ቤቴል በአብራኪ መንፈስ እዚዝ፡፡
ጳውሎስኒ ዕጸ ዘገባ ወእፀ ዘገነት አርዝ
አጽለልነ በታኅቴከ እንዘ ሥልጣንከ ንትኤረዝ
ለዘሐንካሳን ፍኖት ወለዘሥውራን ምርጉዝ
ሕስመ አንተ መሴስይ ወአንተ መናዝዝ
በይነ ዘተቀትለ ለከ አርዌ አመጻ ወኅምዝ

በሊቀ ኅሩያን ዘርዓ ዳዊት ደለለ
የካቴድራሉ የድጓ መምህር

## መወድስ ቅኔ

1. ዝጉባነ መንግሥት ሠረቅት ኖሎተ አመዓ
በዘቴዎፍሎስ እክል ዘያስተፌስህ ማእረሩ
ዘእንበለ ክርዳድ በቆለ በገራህተ ጠበብት ሀገሩ
ስርናየ መሥዋዕት ቴዎፍሎስ
በግብርከ ወይነ አስተፍስሆ ኢይስትዩ ሰከሩ
ወእምድህረ ሰክሩ በግብርከ
ወይነ ቤተ ቃና ጥዑም
ቅድመ ዘርእዮሙ ሐፍሩ

### ለዓለም

ለብርሃንሂ ቴዎፍሎስ መልዕልተ እንጦጦ ጠፈሩ
ከመ ያብርህ ዓለማተ ይስቀልዎ ተማከሩ
በውስተ ጽልመት ቅንዓት እምጣነ እሉ ነበሩ
ወደቂቀ ጸሐፍት አማዕያን ግብረ ቀደምቶሙ ይገብሩ

### ሕንዜሃ

ቴዎፍሎስ ላህም ዘኢይትሄየል በቀርኑ
ምስለ ሰዋኢሁ ወአለ አኮኑ

## ጉባኤ ቃና

ቴዎፍሎስ ይግበር ውስተ ዓውዱ ፃሰለ ጳውሎስ
ትፍሥሕተ
ዘርዓ ገራህቱ ልደት እምጣነ ፈረየ ምዕተ፡፡

### ዘአምላኪየ

ራዕየ ቴዎፍሎስ ኮነ እንተ ርእይዎ እርምሞ
ጴጥሮስ በናህሰ ኢዮጴ ወዮሐንስ ፍጥሞ፡፡
እንዘ ተርጓሚሁ ጳውሎስ ቀዋሚ ለቴዎፍሎስ ምቅዋሞ፡፡

### ዘይዕዜ

ደብረ ታቦር ኮነ ዓውደ ገበርከ
ቴዎፍሎስ አብ ዘተገፋዕከ በሐማ
እምጣነ ተከሥተ ወተርእየ
ግሩም ኃይለ መለኮት በዓቢይ ግርማ፡፡
እስከነ ይመጽእ ቃል ዘሀለወ ውስተ ራማ፡፡
ወንበውእ ኵልነ በፈቃደ ፌማ
ለመንግሥተ ሰማይ ዓውድከ በብዝኃ ድካም ወፃማ
ወንበውእ ኵልነ በፈቃደ ፌማ

### መወድስ

በዓውደ ቴዎፍሎስ ደምፁ በከመ ሰማዕነ
እመዝሙረ ዐቢይ ዳዊት ዘኪሩቤል ይዜምሩ
በቃለ አሚን በዓለ እንዘ ይገብሩ
ሐዋርያ ወንጌል ፍልሰተ ዓጽም
ወነቢይ በዓለ ልደት ዘበአለ ሐብሩ
ዓዲ በውስተ ዓውዱ
ለቴዎፍሎስ ክቡረ ስመ ቴዎፍሎስ ያከብሩ

### ለዓለም

ልደትሂ ወፍልሰት አዝማደ ቴዎፍሎስ ሰከሩ
በዝክረ ቴዎፍሎስ ወይነ ቃና ዘሠናይ ጣዕመ ነገሩ
እስመ ፓትርያርክ ጳውሎስ ዝክረ ቴዎፍሎስ ዝክሩ
አዘዞሙ ለገዛዕት ምስሌሁ ከመ ይንበሩ

በብፁዕ አቡነ ማርቆስ
የአዊ ዞን ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስና
የቅዱስ ሲኖዶስ አባል



www.ethiopianorthodox.org



የካቴድራሉ ማኅበረ ካህናት በከፊል



የካቴድራሉ ሰበካ ጉባኤ አባላት



የካቴድራሉ የአስተዳደር ሠራተኞች



የካቴድራሉ የጥበቃ ሠራተኞች



የመጽሔት ዝግጅት ኮሚቴ አባላት





ለማዕቱ አባ ቴዎፍሎስ ለዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች መንፈሳዊ ትምህርት ሲሰጡ



የካቴድራሉ ሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች





መልአከ ፀሐይ አባ ወልደገብርኤል ...
ካቴድራሉ የጸበል ቤት ...



አቡነ ቴዎፍሎስ ከቆጵሮስ ፕሬዝዳንትና ሊቀ ጳጳስ ከነበሩት መቃርዮስ ጋር

www.ethiopianorthodox.org